መግቢያ

እግዚአብሔር አምላካችን እርሱ ለፍጥረቱ ከገለጠባቸው *መንገዶች* መካከል *መጽሐፍ* ቅዱስ አንዱ ነው። እግዚአብሔርን ታላቅነት፣ መጋቢነት፣ አዳኝነት ወዘተ ቅዱሳት *መጽሐፍት* ይመሰክራሉ። ቅዱሳት *መጽሐፍትን መማር* (ማጥናት) ሰውን ከስህተት የሚጠብቅ በመሆኑ ስለ ቅዱሳት *መጽሐፍትን መማር* አሰፈላጊ ነው። ‹‹ህግ ለእግሬ *መብራት* ለመንገዴም *መብራት* ነው።›› (*መዝ* 118፤105)

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት በቤ/ክስቲያን ከሚሰጡ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች አንዱ እና ዋነኛው ነው:: ቅዱሳት *መጽሐፍት* በእግዚአብሔር *መንፈስ* ቅዱስ *መሪነት* ቅዱሳን አባቶቻችን የጻፏአው ናቸው።ከሁሉ በላይ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔርን *መማር* ወይም ማጥናት የነፍስ ምግቧ ነውና *መጽሐፍ* ቅዱስን ማጥናት አስፈላጊ ነው።የቀደሙት አባቶቻችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ተወዳጅተው በመጽሐፍ ቅዱስ *መሠረት* ህይወታቸውን *መረተው* ገነትን ለመውረስ በቅተዋል።እኛም እንደ አባቶቻችን በቃለ እግዚአብሔር ልንመራ ይገባል።የዚህ ትምህርት ዓላማ ስለ *መጽሐፍ* ቅዱስ ምንነት፤ አከፋፈል፤ አቆጣጠር ወዘተ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። ወደ ተማሪዎች በዚህ ክፍለ ትምህርት በቅዱስት *መጽሐፍት* ማለትም በሁለቱ ኪዳን የተሰበከው የመለኮት *መገለጠ*፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅም፣ በእነ ማነ በምን ዘመን ተጻፈ የሚሉት *መንፈሳዊ* ሀሳቦች እንማራል።

ወደ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች በየምዕራፉቱ ማጠቃለያ የተሰጡት መልመጃዎች እንደተሰሯቸው እያሳሰብን። በእግዚአብሔር አጋዥነት ትምህርታችን እንጀምራለን።

የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት

የእመቤታችን አማላጅነት

የቅዱሳን *መላዕክት* ተራዳይነት አይለየን አሜን።

ምዕራፍአንድ

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ትርጉም

ውድ ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስንል እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያ አስተምህሮ መሰረት በሰማንያ አንዱ ቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የተገለጠው እግዚብሔር ለፍጥረቱ ያለውን ድንቅ ዓላማ እና ፍቅር ማጥናት ማለታች ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክ እስትንፋስ ያረፈበት የተቀደሰ መጽሐፍ በመሆኑ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት ዘርፈ ብዙ የሆነ ጥቃሚ ጥበብ መቀሰም ያስችላል።

ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች በዚህ ምዕራፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው፣ ከሌሎች መጽሐፍት በምን ይለያል፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናታችን የምናገነው ጥቅም ምንድ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ በማን፣ መቼ፣ በምን ቋንቋ ተጻፈ የሚሉ መስረታዊ ሀሳቦችን እንዳስሳለን።

1.1 የመጽሐፍቅዱስጥናትማለትምንማለትነው?

መጽሐፍማለት-በአንድ ጥራዝ ውስጥ የተካተቱ (የተከማቹ) ጽሐፎች ስብስብ ማለትነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ቅዱሳት መጽሐፍት በአንድ ላይ ተሰበስበው የሚገኙበት የመጽሐፍት መድብል ነው።

ቅዱስማለት-የተለየ፣የተከበረ፣የተቀደሰ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ምድራዊያን መጽሐፍት በዘመን የሚወሰን በሰዎች የሚሻሻል ሳይሆን እንደ ዘመናት የማያልፍ፤አንባቢውን የሚቀድስ የተለየ፣የተቀደሰ መጽሐፍ ነው።

ጥናት-አንድን ነገር በጥልቅት መመልከት በነገሩ ላይ በቂ ግንዛቤ መያዝ እና ማስጨበት መቻል ማለት ነው።

1.2 መጽሐፍ ቅዱስ የማጥናት ጥቅም

ወደ ተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ከአምላኩ ጋር እንዲገናኝ እና ክፉን ከደጉ በመለየት እግዚአብሔር በፈቀደው መንገድ እንድንጓዝ ይረዳል።ሰለሆንም መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ዘረፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው።ከዘርፈ ብዙ ጠቀሜታው የተወሰኑትን እንደ ሚከተለው እንመለከታለን፡-

I. እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅ እና ለመቀደስ

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሰለተጻፉ ጽሑፎች የምንረዳበት ነው።እግዚአብሔር አምላካችን ለፍጥረቱ በስነ-ፍጥረት፤ በመጽሐፍት እና እራሱ በመገለጥ ስለእሱ እንዲውቁ አድርጓል። የስነ- መለኮት ሊቃውንት ምክንያቱን ሲያሰረዱ ፍጹም ኃያል የሆነው እግዚአብሔር በፍጡሩ ሊመረመር የማይችል በመሆኑ በመጽሐፍት እና በስነ-ፍጥረት እራሱን ለፍጡሩ ገልጧል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ኃይሉ፤ ክብሩ፤ ባህሪውን፤ ፈቃዱ፤ አሰራረር ወዘተ ተገልጾል። ስለዚህ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅ እና ለመቀደስ ይጠቅማል።

II. ክፉን ከበጎ ለመለየት ይረዳል

የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ነው።በቃሉ ብርሃንነት ክፉን ከደጉ፤ ደጉን ከክፉ ለመለየት መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ጠቃሚ ነው።"ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው::" መዝ 118፤105 እንዳለ ቅዱስ ዳዊት።

“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።” 2 ጢሞ 3፤ 17

III. ለመቀደስ

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ የሚያነቡትን፤ የሚሰሙትን፤ የሚያጠኑትን እና የሚጸልዩትን ይቀድሳል።‹‹በእውነትህ ቀድሳቸውቃልህ እውነት ነው።››ዮሐ 17፤17 (ኤፌ 5፤26)

IV. ጥበብ ስጋዊ እና ጥበብ መንፈሰዊ ለማግኘት

መጽሐፍ ቅዱስ የጥበባት ሁሉ ምንጭ ነው።መንፈሳዊ ጥበብ እግዚአብሔርን በመፍራት እንደሚገኝ ያስተመረናል። (ምሳ 1፤7)
በተጨማሪም ስጋዊ ጥበቦች ያስተምረናል።

- የምህድስናምንጭነው (ዘፍ 6፤14-16 2 ዜና 3፤3-4 1 ነገ 6፤1-38 ዘጸ 36፤1-40)
- የሕክምናምንጭነው **(**ኩፋ 10፤7 ት.ኢሳ 38፤21 ሉቃ 10፤29-37**)**
- የግብርና ምንጭ ነው(ዘፍ 3፤17-23 ዘፍ 41፤25-36 ዘዳ 23፤10)
- የአስተዳደር ምንጭ ነው (ዘጸ 18፤13- 25 ዘጸ 32፤32 1 ነገ 17፤28)

1.3 መጽሐፍቅዱስ ከሌሎች መጽሐፍት በምን ይለያል

ወድ ተማሪዎችመጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎዎቹ ዓለማዊያን መጽሐፍት በምን የሚለይ ይመስላችሁል?
መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጽሐፍት የሚለይበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። የተወሰኑትን ከዚህ በታች እንመለከታለን። መልካም ንባብ!
ሀ. አስገኘው እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ

መጽሐፍቅዱስ የሚናገርው ስለ ቅዱሱ እግዚአብሔር በመሆኑ ከሌሎች መጽሐፍት ይለያል። ሌሎች መጽሐፍት(አለማዊያን መጽሐፍት) የተገኙት ከሰው ሲሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከቅዱሱ እግዚአብሔር የተገኘ በመሆኑ ቅዱስ ነው። ‹‹እኔ ቅዱስ እንደሆንኩኝ እናተ ቅዱሳን ሁኑ››ዘሌ 19፤2

ለ. በእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳሱ ቅዱሳን አባቶች የጻፉት በመሆኑ

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በቅዱሳን አበው ነው። ‹‹በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣም እና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።›› እንዲል 2 ጴጥ 1፤20-21 (ዘጸ 17፤14 ራዕ 2፤7)

ሐ. ዘመን የማይሽረው በመሆኑ

ዓለማዊያን መጽሐፍት በየጊዜው ከለውጦች ጋር በተገናዘበ መልኩ ሲለወጡ፣ ሲቀየሩ ፣ሲሻሻሉ እና ሲሻሩ ይታያል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በጊዜ ብዛት የሚሻር እና የሚሻሻል ሳይሆን በዘመናት የማይገደብ የህያው የእግዚአብሔር ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የማይሽርው ባለስልጣን በስልጣኑ የማይለውጠው ዘላለማዊ ህግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከላይ ከሰማይ የተሰጠ ሰማያዊ ዓላማ ያለው አምላካዊ መጽሐፍ ነው። ዓላማውም ፍጥረት ሁሉ(የሰው ልጅ) መንግስተ ሰማያትን እንዲወርስ ማስቻል ነው። ስለዚህ በዘመን የማይገደብ

ዘላለማዊ መጽሐፍ ነው።‹‹ ሰማይ እና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም›› ማቴ 23፤35 (ት.ኢሳ 40፤8 1ኛ ጵጥ 1፤25 12፤5 ዘዳ 31፤19)

መ. የሚያነቡትን እና የሚሰሙትን ሰለሚባረክ

መጽሐፍ ቅዱስ የሚመክር፣የሚገስጽ፣ የሚያረጋጋ የሰውን ልጅ ወደ ቅድስና የሚመራ መጽሐፍ ነው። (ዘሌ 19፤21 1ጵጥ 1፤15 መዝ 118፤103-105 22፤4 ሉቃ 4፤14 7፤7 ሐዋ 13፤26)

ሠ. የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት ስለነበር ሁኔታ በእርግጠኝነት ስለሚናገር

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ከአንድ ሺ (1000) ዓመታት በኃላ መጻፍ የተጀመረ ቢሆንም የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት ሰለነበረው የሥነ-ፍጥረት ስራ በእርግጠኝነት ይናገራል።‹‹ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይ እና ምድር ፈጠረ።›› ዘፍ 1፤1 (ዩሐ 1፤1) በሌሎች መጽሐፍት ግን ይህን በመላምት እንጂ እረገጠኝነት በተላበሰ መልኩ ማገኘት አይቻልም።

ረ. ወደፊት ሰለሚመጣው በእርግጠኝነት የሚናገር በመሆኑ

መጽሐፍ ቅዱስ ሰለሚመጣው ዘመን በእርግጠኝነት የሚናገር መጽሐፍ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉ የተፈጸሙ እና እየተፈጸሙ የሚገኙ ናቸው። ለምሳሌ ነብዩ ኢሳይያስ ክርስቶስ በድንግልና ሰለመወለዱ ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት የተነበየ ሲሆን የትንቢቱን ፈጻሜ በሐዲስ ኪዳን በወንጌል ተጽፎ እናገኘዋለን። ‹‹እንሆ ድንግል በድንግልና ተፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ተለዋለች...›› ት.ኢሳ 7፤14 (ሉቃ 1፣25 መዝ 77፤65 46፤5 ማቴ 24)

ቀ. ሰውን ወደ ቅድሳና የሚያደርስ በመሆኑ

በመጽሐፍ ቅዱስ የጠቀሱትን ትምህርቶች፣ ምክሮች፣ተግሳጾች አንዲሁም ትዕዛዞች የሚጠብቅ እና የሚተገብር ሰው በቅድስናን መንግድ ላይ የሚጓዝ ነው። ‹‹ የዚህ መጽሐፍ ትንቢት የሚጠብቅ ብፁዕ ነው›› ራዕ 2፤7

1.4. መጽሐፍ ቅዱስ መቼ በማን ተጻፈ?

1.4.1 መጽሐፍ ቅዱስ በማን ተጻፈ?

መጽሐፍ ቅዱስን ቅዱሳን አባቶቻችን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ጻፉት። በሁሉም አባቶች(ነብያት፣ ሐዋርያት፣ አርድዕት እና ሊቃውንት) ላይ አድሮ ምስጢር የገለጸ፣ የመራ እና ያናገር የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።(ዩሐ 14፤26) ቅዱሳን ሰዎች በገዛ ፈቃዳቸው ተነስተው የጻፉት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ ነው።‹‹ ይህን በመጀመርያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በስው ፍቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት›› 2ኛ ጵጥ 1፤20-21 (ራዕ 1፤11 ት.ኢሳ 8፤1 ት.ኤር 36፤2 ዘጸ 34፤27)

ተማሪዎችመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ከተለያዩ የስራ መስኮች በተጠሩ ቅዱሳን ሰዎች አማካኝነት ነው። ለዚህ ድንቅ አገልግሎት ከተመረጡ ቅዱሳን አበው መካከል የተወሰኑትን ከምን የስራ መስክ እንደተጠሩ እንመለከት፡-

ለምሳሌ

- ከእረኝነት ሙሴ /ዘጸ 3፤1/ - ከቀራጭነት ማቴዎስ /ማቴ 9፣9/
- ከነገስታት ዳዊት እና ሰሎሞን /ዜና 29፤28/ - ከካህናት ሕዝቅኤል /ት.ሕዝ 1፣3/
- ከዓሳ አጥማጅነት ጵጥሮስና ዩሐንስ... /ማቴ 4፣18-22/ - ከሕክምና ሉቃስ /ቆላ 4፤4/

ውድ ተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን ቅዱሳን አበው ከተለያየ የስራ መስክ ተጠረት መጻፋቸው ተመለከተናል። የብሉይ ኪዳን ጽሐፊዎች ይወረዳል ይወለዳል እያሉ ሲጽፉ። የሐዲስ ኪዲን ጽሐፊዎች ወረደ፣ ተወለደ፣ ተጠመቀ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ ተነሳ፣ ዐረገ እያሉ ጽፈዋል።

1.4.2 መቼ ተጻፈ?

ውድ ተማሪዎች በመጀመሪያ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቱ ይስላቹል?

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ቅዱሳን አባቶች ተጽፎል። መጽሐፍ ቅዱስ ከ 1400 ቅ/ል/ክ እስከ 100 ድ/ል/ክ ድረስ እንደተጻፈ ይታመናል። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ከ 1400-400 ዓ.ዓ (ቅ/ል/ክ) በ 32 በሚደርሱ ቅዱሳ አባቶች የተጻፈ ሲሆን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ከ 45-100 ዓ.ም (ድ/ል/ክ) ከ 8 በላይ ቅዱሳን አባቶች ተጽፎል።እንደ ሊቃውንት ቤ/ክ አስተምሮ መሰረት በመጀመርያ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መጽሐፍ ሄኖክ ሲሆን በመጨረሻ የተጻፈው ራዕይ ዮሐንስ ነው።

1.5 መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው ቋንቋዎች

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍቶች በዕብራይስጥ እና በአረማይክ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ደግሞ አብዛኞቹ በግሪክ ቋንቋ ተጽፈዋል። በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ በአራት አገር ቋንቋዎች የተጽፏ። እነርሱም

- ✓ ዕብራይስጥ
- ✓ አረማይክ
- ✓ ሮማይስጥ
- ✓ ግሪክ /ዕር/ ቋንቋዎች ናቸው።

አብዛኞቹ የብሉይ ኪዳን መጸሐፍት በዕብራይስጥ እና በአረማይክ ቋንቋ ተጽፍዎል። ዕብራይስጥ እና አረማይክ ቋንቋ በሲሚቲክ የቋንቋ ምድብ ውስጥ ይመደባል። አብዛኖቹ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት በግሪክ/በጽዕር/ ቋንቋ ተጽፏል። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነሳው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት በተጻፉበት ወቅት የግሪክ ቋንቋ አብዛኞቹ የአለም ሀገራት የሚነገር በመሆኑ ወንጌልን ሁሉም ሰው እንዲሰማው እበዛኞቹ ሰዎች በሚደምጡት/በሚናገሩት/ በግሪክ ቋንቋ እንዲጻፍ ሆኗል።

1.6 የቅዱሳት መጽሐፍት ትርጉም

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል የያዘ በመሆኑ ለተወሰነ ህዝብ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ለመላው አለም እንዲማርበት እና እንዲታረምበት፣አምልኮቱን እንዲገለጥበት፣ስለእግዚአብሔር እንዲያውቅበት ተሰጧል:: ስለዚህ ቅዱሳት መጽሐፍት ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጎም አስፈለገ:: እግዚአብሔር አምላክ በየዘመናቱ የሚጽፉና የሚተረጉሙ ሰዎችን አስነስቷል:: ኢትዮጵያ በዕብራይስጥ ተጽፎ የነበሩትን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ወደ ግዕዝ ቋንቋ በመተርጎም ቀዳሚት አገር ናት:: በ 900 ዓ.ዓ ገደማ ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር የመጡት 318 የአይሁድ ሊቃውንት የግዕዝ ቋንቋን በማጥናት ተርጉመውታል:: በ 284(275) ዓ.ዓ ቅ.ል.ክ(ቅድመ ልደተ ክርስቶስ)

ገደማ 72 ሊቃውንት ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ/ጽዕር/ ቋንቋየብሉይኪዳንመጽሐፍትበበጥሊሞስዘመነ መንግስት ተረጎሙት::የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትም ከዕብራይስጥ ወደ አርማይክቋንቋ ተተርጉሟል::

መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ሰጡ

1. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በልዑል እግዚአብሔር ነው።
   ሀ. እውነት ለ. ሀሰት
2. መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ዓለማዊያን መጽሐፍት በምን ይለያል?
3. መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጉም ለምን አስፈለገ?

ምዕራፍ ሁለት

የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና

ወድ ተማሪዎች በቀደመው ምዕራፍ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምንነት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት የሚሰገኘውን ጥቅም፣ ከሌሎች መጽሐፍት በምን እንደሚለይ እና በማን፣ መቼ፣ በምን ቋንቋ እንደተጻፈ ተመለከትን በስተመጨረሻም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተመለከተናል። በዚህ ምዕራፍ በክርስትናው ዓለም በመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር ላይ ያለውን የልዩነት ምክንያት እንመለከታለን።

<u>ቀኖና</u>፦ ማለት ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙ መቃ፣መለኪያ፣ቀጥተኛ፣ትክክለኛ ማለት ነው:: የቤተ-ክርስቲያን ቀኖና ሲባል የቤተ-ክርስቲያን ህግ ቀጥተኛ እምነት(ዶክትሪን) ማለት ነው:: የቅዱሳት መጽሐፍት ቀኖና የሚባሉት ቤተ-ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትን ለመግለጥና ለማስተማር እንደሚችሉ በጉባኤ የታመነባቸው መጽሐፍት ማለት ነው:: ይህ ስያሜ ለመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው በአራተኛ ምዕተ አመት ገደማ በቅዱስ አትናቴዎስ እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ያስረዳሉ:: የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቀኖናዊያት መጽሐፍት ይይዛል:: ይህም ውሳኔ የተሰጠው የተቀደሰ መጽሐፍት ለመሰብሰብ ተብሎ በሎዶቂያ ጉባኤ በተወሰነው መሰረት ነው:: (Canonical Bible)

ሁለት አይነት ቀኖና መጽሐፍት አሉ እነርሱም፤

- 1ኛ (የመጀመሪያ) ቀኖና መጽሐፍት(protocanonical)
- 2ኛ (ሁለተኛ)ቀኖና መጽሐፍት(deuterocanonical) ይባላሉ።

2.1 1ኛ ቀኖና መጽሐፍት (protocanonical)

1ኛ ቀኖና መጽሐፍት የሚባሉት በክርስትናውዓለም ያለ ልዩነት ተቀባይነት ያላቸውን መጽሐፍት ነው:: ይህ ማለት በኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ፣በካቶሊኮች፣በፕሮቴስታንትና አይሁድ ዘንድ እኩል ተቀባይነት ያላቸው መጽሐፍት ናቸው:: እነዚህም 39(በእኛ አቆጣጠር 46) የሚሆኑት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ናቸው::

2.1.2 2ኛ ቀኖና መጽሐፍት (deuterocanonical)

2ኛ ቀኖና መጽሐፍት የሚባሉት አምላካዊያን መጽሐፍትነታቸው በጥናታውያን አብያተ ክርስቲያን ቦታ ያገኙና ተቀባይነት ያላቸው ሲሆኑ በሌሎች ወገኖች ደግሞ አንዳንዶቹ እንደ አዋልድ መጽሐፍት ተቀባይነት ሲያገኙ አንዳንዶች ጋር ተቀባይነት ያላገኙና መጽሐፍት ናቸው::

2.2 የመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር

ወድ ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር ከላይ በተመለከትናቸው ቀኖና መጽሐፍት አቆጣጠር መሰረት ይለያያሉ።

2.2.1 የአይሁድ አቆጣጠር፦በአይሁድ መጽሐፍ አቆጣጠር ውስጥ የተካተቱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ክፍል ብቻ ናቸው። በሐዲስ ኪዳን የተገለጠው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመቀበላቸው ምክንያት የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት በአይሁድ ቀኖና መጽሐፍት ውስጥ አይካተቱም። የአይሁድ ቀኖና መጽሐፍት የሚባሉት 24 የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ሲሆኑ አከፋፈላቸው እና ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ይቀርባል፦

- ❖ አምስቱ የሙሴ መጽሐፍት - የመዝሙር እና የጥበብ መጽሐፍት
- ❖ የነቢያት መጽሐፍት - የታሪክ መጽሐፍት
  - ኢያሱ፣መሳፍንት 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣1ኛ እና 2ኛ ነገስት
  - ኢሳያስ፣ኤርሚያስ፣ሕዝቅኤል እና 12ቱ ደቂቀ ነቢያት ናቸው::
  - መዝሙረዳዊት፣ምሳሌ፣ኢዮብ፣መኃልየ መኃልየ፣ሩት፣ሰቆቃው ኤርሚያስ፣መክብብ፣አስቴር፣ዳንኤል፣ዕዝራ ነህሚያ(ወይም 2ኛ ዕዘራ) እና 1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕል

2.2.2 የፕሮቴስታንት አቆጣጠር

ከላይ ያሉት አይሁድ የሚቀበሏቸውን በሙሉ ይቀበላሉ:: በአቆጣጠር ለያይተው አይሁድ 12ቱን ደቂቀ ነብያት መጽሐፍት እንድ አንድ ይቆጥሩ የነበረውን ፕሮቴስታንቶች ለየ ብቻ በመቁጠር 39 አድርሰዋል:: ከሐዲስ ኪዳን 27 በአጠቃላይ 66 መጽሐፍት ይቀበላሉ::

2.2.3 የካቶሊኮች አቆጣጠር

39ኙን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ሁሉንም ይቀበላሉ። መጽሐፈ ምሳሌ ከምዕራፍ 25 እስከ 31 ያለው መጽሐፈ ተግሳጽ ተብሎ እንደ አንድ መጽሐፍ ይቆጠራል:: በተጨማሪም 7 የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ማለትም፦

- ✓ መጽሐፈ ጦቢት
- ✓ መጽሐፈ ዮዲት
- ✓ መጽሐፈ ጥበብ
- ✓ መጽሐፈ ሲራክ
- ✓ መጽሐፈ ባሮክ

- ✓ 1 ኛና 2 ኛ መቃቢያን ይቀበላሉ።

ከሐዲስ ኪዳን 27 መጽሐፍ ይቀበላሉ:: በአጠቃላይ 73 መጽሐፍት ይቀበላሉ:: የኢትዮጲያ ኦ/ተ/ቤ/ክ የምትቀበላቸው 81 ቅዱሳት መጽሐፍት ነው:: ከብሉይ ኪዳን 46 ከሐዲስ ኪዳን ደግሞ 35 መጽሐፍትን ትቀበላለች።

መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛው ምላሽ ስጡ

1. ቀኖና ማለት ምን ማለት ነው
2. የቅዱሳት መጽሐፍት አቆጣጠር መሰረት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ----------፣ የካቶሊክ ቤ/ክ ---------- ፕሮቴስታንት----------፣ አይሁድ---------- መጽሐፍትን ይቀበላሉ።
3. የቅዱሳት መጽሐፍት ቀኖና አቆጣጠር በሶስት ይከፈላል።

   ሀ. ሀስት ለ. እውነት

ምዕራፍ ሶስት

የመጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈል

ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች በምዕራፍ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር ምን እንደሚመስል ለመመልከት ችለናል። በዚህ ምዕራፍ የመጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈል እንዴት እንደሆነ እንመለከታለን። የምስጢራት ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ምስጢሩን ይገለጥልን። አሜን።

3.1 የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን አከፋፈል

ብሉይ ኪዳን

<u>ኪዳን-</u> ኪዳን ማለት በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል(ስምምነት) ማለት ነው:: እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያደረገው ውል፣ስምምነት ማለታችን ነው::በዚህ መሰረት ለኪዳን ሁለት ወገኖች ያስፈልጋሉ:: ውል ሰጪና ውል ተቀባይ:: ከዚያም መኃላው(ኪዳኑ) ይኖራል:: እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በኪዳኑ አልተለየውም:: (ዘፍ 1፤26-28)

ብሉይ - ማለት የቆየ፣የጥንት፣የበፊት፣ቀዳማዊና የድሮ ማለት ነው:: ብሉይ ኪዳን ማለት ጥንታዊ፣ቀዳማዊ ውል(ስምምነት) ማለት ነው:: ይህ ውል በሙሴ አማካኝነት እግዚአብሔር ለእስራኤላዊያን የገባውን ኪዳን የያዘ ነው:: ይህ ኪዳን ከፍጥረት ዓለም እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ ያለውን ታሪክ በውስጡ የያዘ ነው:: የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትየተጻፉት ከ1400-400 ዓ.ዓ(ቅ.ል.ክ) ድረስ ባሉት 1000 ዓመታት ውስጥ ነው:: የተጻፈውም ስላሳ ሁለት(32) በሚደርሱ አባቶች ነው:: የተጻፈውም በዕብራይስጥቋንቋ ነው:: ብሉይ ኪዳንን ብሉይ ኪዳን ያሰኘው እግዚአብሔር አምላካችን ከእስራኤል ዘነፍስ ጋር ያደረገው አዲስ ውል ወይም ስምምነት(ሐዲስ ኪዳን) ሲመጣ ነው::(ኤር 31፤31 ማቴ 26፤26-29 1ኛ ቆሮንቶስ 11፤25-26)

ብሉይ ኪዳን ተሸሯል የሚለው አስተምህሮ የተሳሳተ ነው:: ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን መምጣት ጸንታለች፣ከብራለች::(ማቴ 5፤19-20) ጌታችን ወንጌልን ሲያስተምር ከብሉይ ኪዳን እየጠቀሰ ማስተማር ለዚህ በቂ ማሳያ ነው:: ‹‹ህግና ነቢያትን ልሽር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ›› ማቴ 5፤17። በህግና በነቢያት ስለ እርሱ የተነገሩትን ለመፈጸም የወጣ መሆኑን አስተምሮናል:: ስለዚህ ብሉይ ኪዳን የሐዲስ ኪዳን ምስክር ፣ንባብ፣ትርጓሜ፣ፍጻሜ ናት:: ቅዱስ አወግስጢኖስ የተባለው የቤተ-ክርስቲያን ሊቅ ‹‹ሐዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ተሰውሯል። ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን ተገልጧል›› በማለት ተናግረዋል::

የሁለቱ ኪዳናት አንድነት

ሁለቱም ኪዳናት የሚገለጡት(የሚስተማሩት) ስለ እግዚአብሔር ነው::በብሉይ ኪዳን የተገለጠ እግዚአብሔር በሐዲስ ኪዳን የተገለጠው እሱ እራሱ ነው:: ሁለቱምስለተመረጡ ህዝቦች ይናገራሉ::በብሉይ ኪዳን የተመረጡ ህዝቦች የሚባሉት እስራኤላዊያን(ዘስጋ) ሲሆኑ በሐዲስ ኪዳን የተመረጡ ህዝቦች ክርስቲያኖች(እስራኤል ዘነፋስ) ናቸው::ሁለቱም በቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር መሪነት የተጻፉ ናቸው:: የሁለቱን ኪዳናት በምሳሌ ለማስረዳት ይረዳን ዘንድ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡- አንድ ፊልም ሁለት ዲስኮች ቢኖሩት A እና B፤ብሉይ ኪዳን A ስትሆን ሐዲስ ኪዳን B ነች። አንድ ሰው A ወይም B ብቻ አይቶ ሙሉ ታሪኩን መናገር አንዳማይችል ሁሉ ብሉይ ኪዳንን ሳውቁ ሐዲስ ኪዳን መቀበል አይቻለም እንዲሁም ሐዲስ ኪዳን ተቀብሎ ብሉይ ኪዳን መተው አይቻልም።

3.1.1 የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ክፍሎች

ውድ ተማሪዎች የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋህዶ ቤ/ክ አስተምሮ መሰረት ብዛታቸው አርባ ስድስት(46) ሲሆን በ 4 ዋና ዋና ክፍሎች በመከፈል ይጠናሉ:: እነርሱም፡-

1.የህግ ክፍል (ብሔረ ኦሪት) /Tora/

በሙሴ አማካኝነት የተጻፉ 5 የህግ መጽሐፍቶች በውስጡ ይዟል:: እነርሱም ኦሪት ዘፍጥረት፣ኦሪት ዘጸአት፣ኦሪት ዘሌዋዊያን፣ኦሪትዘኁልቁና ኦሪት ዘዳግም፣ ናቸው::

2.የታሪክ ክፍል (ከቱቢም-kethubim)

የታሪክ መጽሐፍት ክፍል በውስጡ 17 መጽሐፍቶችን ይዟል:: እነርሱም-

1.መጽሐፈ ኢያሱ
2.መጽሐፈ መሳፍንት
3.መጽሐፈ ሩት
10. መጽሐፈ ጦቢት
11.መጽሐፈ ዮዲት
12.መጽሐፈ አስቴር

4.1 ኛ እና 2 ኛ ነገስት 13.መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ

5.መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ 14.2 ኛና 3 ኛ መቃብያን

6.1 ኛ ዜና መዋዕል 15.መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን

7.2 ኛ ዜና መዋዕልና ጸሎተ ምናሴ 16.መጽሐፈ ኩፋሌ

8.መጽሐፈ ዕዝራነህምያ 17.መጽሐፈ ሄኖክ

9.መጽሐፈ ዕዝራ ስቱኤል እና መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

3. የመዝሙርና የጥበብ መጽሐፍት

1. መጽሐፈ ኢዮብ 6.መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን
2. መዝሙረ ዳዊት 7.መጽሐፈ ጥበብ
3. መጽሐፈ ምሳሌ 8.መጽሐፈ ሲራክ
4. መጽሐፈ ተግሳጽ
5. መጽሐፈ መክብብ

4.የትንቢት መጽሐፍት

የትንቢት መጽሐፍት በውስጡ 16 መጽሐፍትን ይዟል።ከእስራ ስድስቱ መካከል አራቱ አቤት ነብያት ሲሆኑ 16 ቱ ደግሞ ደቂቀ ነብያት ተብለው ይጠራሉ።

1.ትንቢተ ኢሳይያስ 9.ትንቢተ አብድዩ

2.ትንቢተ ኤርሚያስ 10.ትንቢተ ዮናስ

3.ትንቢተ ሕዝቅኤል 11.ትንቢተ ናሆም

4.ትንቢተ ዳንኤል 12.ትንቢተ ዕንባቆም

5.ትንቢተ ሆሴዕ 13.ትንቢተ ሶፎንያስ

6.ትንቢተ አሞጽ 14.ትንቢተ ሀጌ

7.ትንቢተ ሚክያስ 15.ትንቢተ ዘካርያስ

8.ትንቢተ ኢዩኤል 16.ትንቢተ ሚልክያስ

3.2 የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ብዛት እና አከፋፈል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋህዶ ቤ/ክአቆጣጠር መሠረት የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ብዛት 35 ነው። / ፍትሐ ነገስት አንቀጽ 2/ 35 ቱ የሐዲስኪዳንመጽሐፍትበ 5 ክፍሎች ይከፈላሉ። አከፋፈላቸው እንዲሚከተለው ነው፦

- የወንጌል ክፍል---- 4 ቱ የወንጌል መጽሐፍት (የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስ እና የዮሐንስ ወንጌል ናቸው።)
- የታሪክ ክፍል---- የሐዋርያት ስራ
- የመልዕክት ክፍል---- 14 ቱ የቅዱስ ጳውሎስ፣ 3 ቱ የቅዱስ ዮሐንስ፣ 2 ቱ የቅዱስ ጴጥሮስ፣ 1 ቅዱስ ይሁዳ እና 1 ቅዱስ ያዕቆብ መልዕክታት ናቸው። በአጠቃላይ 21 መልክታት
- የትንቢት ክፍል--- የዮሐንስ ራዕይ

- የስርዓት ክፍል---- ስርዓተ ጽዮን፣ ትዕዛዘ ሲኖዶስ፣ ግጽው፣ መጽሐፈ ኪዳን 1 እና 2 መጽሐፈ አብጡሊስ፣ መጽሐፈ ቀሌምንጦስ፣ መጽሐፈ ዲዲስቅልያ ናቸው። በአጠቃላይ 8 መጽሐፍት ናቸው።

መልመጃ ሶስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛው ምላሽ ሰጡ

1. የሁለቱ ኪዳን አንድነት በምን በምን እንደሆነ ግለጹ
2. የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ብዛት---------- ሲሆን በ---------- ይከፈላል።
3. የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ብዛት---------- ሲሆን በ---------- ይከፈላል።

ምዕራፍ አራት

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ዝርዝር ጥናት

ውድ ተማሪዎችበዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው አርባ ስድስቱ(46 ቱ) የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ዝርዝር ጥናት ይሆናል። መጽሐፍቶቹ በማን ፣መቼ እንደተጻፉ፣ አብይ የመጽሐፍቶቹን አስተምህሮ እንመለከታለን።

4.1 የህግ መጽሐፍት (ብሔረ ኦሪት)

ኦሪት፡- የሚለው ቃል የዕርስት ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም ብርሃን ማለት ነው:: መዝ 118-105 ዕብራዊያን ቶራ ብለው ይጠሩታል:: ትርጉሙም ህግ ማለት ነው:: የህግ መጽሐፍት የሚባሉት አምስት(5) መጽሐፍት ሲሆኑ የተጻፉትም በነቢየ እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ነው:: ሙሴ ከሌዋዊያን ወገን የተወለደ ታላቅ አባት ነው:: የእስራኤልን ህዝብ ከግብጽ ባርነት ያወጣ ዘንድ እግዚአብሔር የመረጠው ታላቅ መሪ ነው:: አስተዳደጉ በፈርኦን ቤት ቢሆንም ልቡ የወገኖቹን ጉዳት ይመለከት ስለነበር በእግዚአብሔር ፈቃድ አስቸጋሪውን የእስራኤል ህዝብ ይመራ ዘንድ ተመረጠ:: ነብዩ ሙሴ እግዚአብሔርን ከ 570 ጊዜ በላይ ቃል በቃል ያነጋገረ፣ በእግዚአብሔር አንደበት እንድ ሙሴ ያለ ትሁት ሰው የለም ተብሎ የተመሰከረለት ታላቅ አባት ነው።

በአጠቃላይ አምስቱ የሙሴ መጽሐፍት ጠቅለል ባለመልኩ የሰው ልጅና የሌሎችን ፍጥረታት አፈጣጠር፣ የእስራኤላዊያንን ስደት እንዲሁም ከስደት መመለስን፣ የተሰፋይቱን ምድር መወረስና ሌሎችንም አቤት ታሪኮች ይዘዋል:: ከ 5 ቱ የኦሪት መጽሐፍት በመጀመሪያ የምንመለከተው ኦሪት ዘፍጥረትን ነው::

4.1.1 ኦሪት ዘፍጥረት

ይህ መጽሐፍ የስነ ፍጥረት ልደት ወይም አጀማመር እንዴት አንደመጣ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው:: የፍጥረታትን ልደት የሚዘክር በመሆኑ ኦሪት ዘልደት ተብሎም ይጠራል:: የመጽሐፍ ቅዱስን የታሪክ ቅደም ተከተል ከመጠበቅ አንጻር በመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ይገኛል:: ዘፍ 1-1 ነገር ግን በመጀመሪያ የተጻፈው መጽሐፈ ሔኖክ ነው።

ነብዩ ሙሴ ስለ ስነ-ፍጥረት የጻፈው በወቅቱ ኖሮ ሳይሆን እንደ ቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ 40 ቀን 40 ሌሊት በጾምና በጸሎት ቆይቶ ህግጋትን ሲቀበል ፍጥረታት ከመፈጠራቸው ጀምሮ እርሱ እስካለበት ዘመን ድረስ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ምስጢር ገለጦለት(አስተምሮት) ጽፎታል:: አንድም ከአባቶቹ በትውፊት የሰማውን ጽፎታል።

የመጽሐፉ ዓላማ ከስነ ፍጥረት አንስቶ እስራኤላዊያን ወደ ግብጽ ምድር እስከወረዱበትጊዜ ደረስ ያለውን የመለኮት መገለጥ ታሪክ በአጭሩ የሚያስረዳ ነው::

የመጽሐፉ አከፋፈል-ኦሪት ዘፍጥረት 50 ምዕራፎች በወስጡ የያዘ ሲሆን ለጥናት ይረዳን ዘንድ አቤት የታሪኮቹ አከፋፈል እንደሚከተለው ይቀረባል:-

ምዕራፍ 1-2 ስለ ስነ-ፍጥረትና ስለ ሰው ነጻ ፍቃድ ይናገራል::

ምዕራፍ 3-4 ስለ ሰው ልጅ ፈተናና ውድቀት፣ ከገነትም ስለመባረሩ ይናገራል::

ምዕራፍ 5-10 የቅዱሳን አበውን ታሪክ ይናገራል::

ምዕራፍ 6-11 ስለ ጥፋት ውሃ፣ ስለ ኖኅ ቤተሰቦች ድህነት፣ ስለ ስናኦር (ባቢሎን)ሰዎች ግንብ መሰረት(በእግዚአብሔር ላይ መነሳት)፣ ስለ ቋንቋ መደበላለቅ ይተርካል::

ምዕራፍ 12-23 ስለ አብርሐም ታሪክ

ምዕራፍ 24-26 ስለ ይስሐቅ ታሪክ

ምዕራፍ 27-36 ስለያዕቆብታሪክ

ምዕራፍ 37-50 ስለ ዮሴፍ ታሪክ ይናገራል።

ውድ ተማሪዎች በአጠቃላይ ኦሪት ዘፍጥረት ብዙ ጠቃሚ ነገሮች ያስተምረናል። የዓለም ፈጣሪ እና መጋቢ እግዝአብሔር ከፍጥረታት ሁሉ አስበልጦ ለፈጠረው ለሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ መሰጠቱ። ይህ ነጻነት የሰው ልጁ ኃጢአትን ለመስራት እንደተጠቀመበት ያስረዳል። እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ፣ ኃጢአተኞችን ደግሞ እንደሚቀጣ፣ ቅዱሳንን በህይወት ሁሉ እንደሚጠበቅ የሚያስተምሩ የብዙ ትምህርቶች እና ቁም ነገሮችን በውስጡ የያዘ መጽሐፍ ነው።

4.1.2 ኦሪት ዘጸአት

ጸአት፡- ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም መውጣት ማለት ነው። ይህንን ስያሜ ያገኘው የእስራኤል ህዝቦች ለ 430 ዘመናት የግፍና የመከራ ኑሮ በኋላ በሙሴ መሪነት ከግብጽ ምድር መውጣታቸው እና የተስፋይቱ ምድርን ለመውረስ የሚያደርጉትን ጉዞ የሚያሳይ በመሆኑ ነው። 70 ሆነው ወደ ግብጽ ምድር የገቡት የያዕቆብ ልጅ ሲወጡ ከ 60000 በላይ ሆነው ወጡ።

መጽሐፉ 40 ምዕራፎች በወሰጡ የያዘ ሲሆን አከፋፈሉ እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

ከምዕራፍ 1-4

- ✓ ግብጻዊያን በእስራኤላዊያን ላይ ስለፈጸሙት ግፍ
- ✓ ስለ ሙሴ ልደትና ስለወንድሞቹ እርዳታ
- ✓ ሙሴ ከፈርኦን ሸሽቶ ወደ ምድያም ስለመሄዱ
- ✓ በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ የሙሴ መጠራት

ከምዕራፍ 5-11

- ✓ ሙሴ እና አሮን ከፈርኦን ጋር መከራከራቸውን ይተርካል
- ✓ በእስራኤለዊያን ላይ የባርነት ቀንበር ስለመጠበቁ
- ✓ በፈርኦን እንቢተኝነት በግብጽ ስለመጡት አስራ አንድ መቅሰፍቶች

ከምዕራፍ 12-15

- ✓ እስራኤላዊያን ከግብጽ ምድር ስለመውጣት
- ✓ ግብጻዊያን እስራኤላዊያንን ከለቀቁ በኋላ እንደገና በመከተላቸው በእግዚአብሔር ድንቅ ስራ እስራኤላዊያን ባህረ ኤርትራ ተሻግረው ሲሄዱ ግብጻዊያን ግን በባህር ውስጥ ሰጥመው መቅረታቸውን ይተርካል።
- ✓ እስራኤላዊያን በመዝሙር እግዚአብሔርን ማመስገናቸው።

ከምዕራፍ 16-40

- ✓ በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት 10 ቱ ትዕዛዛት የተጻፈበትን ጽላት መስጠቱ
- ✓ ለእስራኤል መተዳደሪያ ደንቦች መሰጠታቸው
- ✓ ስለ ደብተራ ኦሪት አሰራር የተሰጠ መመሪያ
- ✓ ስለ አሮን ስልጣነ ክህነት፣ስለ ልብሰ ተክህኖ እና ስለ ስርአተ አምልኮ
- ✓ እስራኤላዊያን የወርቅ ጥጃ ሰርተው ስለማምለካቸውና ሙሴም ለአምላክ ቀንቶ ጽላቱን በጣኦቱ ላይ መሰበሩ እና የቃልኪዳኑ ህግ ድጋሚ መሰጠቱ ይተርካል።
- ✓ የእስራኤል ልጆች ወደ ከነአን በሚያደርጉት ጉዞ ከሰማይ መና እየወረደላቸው እየተመገቡ ስለመጓዛቸው
- ✓ እግዚአብሔር አሮንን እና ልጆቹን መርጦ መቅደስ እንዲሰሩለት ማዘዝ

- ✓ በሲና ተራራ እንደተገለጠው የእግዚአብሔር ማደሪያ መስራታቸው

ውድ ተማሪዎች ኦሪት ዘጸአትን ጠቅለል ባለመልኩ መልኩ ስንመለከት የሰው ልጅ ከህገ ልቦና ዘመን ወደ ህገ ኦሪት ዘመን(ከልቦናዊ ህግ ወደ የጽሑፍ ህግ) የተሸጋገረበት ሂደትን የሚያሳውቅ መጽሐፍ ሲሆን የበደል ውጤት ምን እንደሆነ እና እግዚአብሔር ህዝቡ በመከራ ጊዜ እንደማይረሳ ያስተምረናል። በተጨማሪም በዚህ መጽሐፍ የተጻፈው ታሪክ ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ምሳሌ ነው። ግብጽ የሲኦል ፈርኦን እና ሰራዊቱ የዲያቢሎስና የጭፍሮቹ፣ሙሴ የክርስቶስ፣የሙሴ በትረ የመስቀል፣እስራኤል የክርስቲያኖች፣ከነአን የመንግስተ ሰማያት፣ባህረ ኤርትራ የጥምቀት፣በረሐውና መቀቱ በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ፈተና፣የበጉ ስጋ እና ደም የክርስቶስ ስጋ እና ደም(ቅዱስ ቁርባን) ምሳሌ ናቸው።

4.1.3 ኦሪት ዘሌዋውያን

በብሉይ ኪዳን ህዝበ እስራኤል ኃጢአት ሲሰሩ የሚያስታርቋቸውና ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቧቸው የሌዋዊያን ካህናት ነበሩ። ይህ መጽሐፉ ዘሌዋውያን የሚለው ስያሜ ያገኘው ከእስራ ሁለቱ ነገደ አንዱ በሆነው በሌዊ ነገድ ስም ነው። መጽሐፉ ለእግዚአብሔር ስለሚቀርቡ የመስዋዕት አይነቶች ይገለጻል።በተጨማሪም ስለበዓላት አከባበር፣ ለእስራኤላዊያን ስለተሰጡ ማኅበራዊ እና ግለሰባዊ ህጎች ይተርካል። ኦሪት ዘሌዋውያን የቅድስና ህይወት የሚገኝበት መጽሐፍ ነው።ስለቅድስና ብዙ ጊዜ ስለሚነገር የቅድስና መጽሐፍ ተብሎ ይጠራል።ይህ መጽሐፍ 27 ምዕራፎች በውስጡ ይዟል።በዘሌዋውያን ውስጥ ከሚገኙት አቤት ትምህርቶች መካከል የመስዋዕት አይነቶች እና የበዓላት አከባበር የሚጠቀሱ ናቸው።

ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች ወደ አከፋፈሉ ከመሄዳችን በፊት የመስዋዕት አይነት እና የበዓላት አከባበር እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፦

4.1.3.1 የመስዋዕት አይነቶች

ሀ.የሚቃጠል መስዋዕት ፦-በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም የመስዋዕት አይነት ነው። (ዘሌ.6፣8-13)

ለ.የደኅንነት መስዋዕት ፦-ህዝቡ ከእግዝአብሔር ጋር የቅድስና ህብረት እንድኖርው የሚቀርብ መስዋዕት ነው።(ዘሌ.3፣1-17)

ሐ.የበደል መስዋዕት ፦-ይህ መስዋዕት የሚቀርበው አንድ እስራኤላዊ እግዝአብሔርን መበደሉን ሳያውቅ ቆይቶ መበደሉን ባወቀ ጊዜ የሚቀርብ መስዋዕት ነው።(ዘሌ.5፣4-7)

መ.የኃጢአት መስዋዕት ፦- 10 ቱን ትዕዛዛት በተላለፈ ጊዜ የሚቀርብ መስዋዕት ነው።(ዘሌ.4፣5-25)

ሠ.የስዕለት መስዋዕት ፦-የተሳለው ስዕለት ሲሰምርለት የሚቀርበው መስዋዕት ነው።(ዘሌ.6፣7-15)

ረ.የፈቃድ መስዋዕት ፦-ይህ መስዋዕት ከሌሎች የሚለየው የግዳጅ መስዋዕት ሳይሆን አንድ እስራኤላዊ ህይወቱ(ቤቱ) የተስተካከለ ሲሆን በፈቃዱ የሚያቀርበው መስዋዕት ነው።

4.1.3.2 የበዓላት አከባበር

እስራኤላዊ እግዝአብሔር ያደረገላቸው ነገር የሚዘክሩባቸው የተለያዩ በዓላት ያላቸው ህዝቦች ናቸው። የሚከተሉት እንመለከታለን፦

1.የሰንበት በዓል፦ ሰንበት ማለት እረፍት ማለት ሲሆን እግዝአብሔር በ 6 ቱ ቀናት ፍጥረታት ፈጥሮ በሰባተኛ ቀን ማረፉን በማሰብ የሚከበር በዓል ነው።የሰንበት በዓል አከባበር እንደ ህግ የተሰጠው በዚህ መጽሐፍ ላይ ነው። እንደ ሊቃውንተ ቤ/ክ አስተምህሮ ሶስት አይነት ሰንበታት ሲኖር ይህ መጽሐፍ የሚዘክር ስለ ሰንበት አይሁድ ነው።በሐድስ ኪዳን በሰንበት አይሁድ በሰንበተ ክርስቲያን (በዕለተ እሑድ)ተተክታለች።

- ሰንበት እግዝአብሔር(ሰንበተ አይሁድ) ወይም 7 ተኛ ቀን
- ሰንበተ ክንዳን (ከግብጽ ምድር የወጡበት ቀን)
- ሰንበተ መንግስተ ሰማያት

2.በዓለ ፋሲካ **(**የነጻነት በዓል**)፦** ከግብጽ ምድር (ከባርነት የወጡበት) የነጻነታቸው ቀን በማሰብ የሚከብሩት ነው ።አይሁዳዊያን ፋሲካ ማክበር የጀመሩት ከግብጽ ምድር ሳይወጡ ነው።ዘዳ 12 በዓለ ፋሲካ የአይሁድ አዲስ ዓመት በገባ በመጀመሪያው ወር(ሚያዝያ) 14 ቀን የሚከበር በዓላቸው ነው።በሐዲስ ኪዳን በበዓለ ፋሲካ በዓለ ትንሣኤ ተተክቷል።

3.የቂጣ በዓል፦የፋሲካን በዓል ካከበሩ ከ 15 ቀን በኋላ ለ 7 ቀናት የሚያከብሩት በዓልነው።በወንጌል የቂጣ በዓል በደረሰ ጊዜ ተብሎም ተተቅሷል።

4.በዓለ ሰዊት /የእሸት በዓል/፦ በዓለ ሰዊት ከ 7 ሰንበታት /49 ቀናት/ ነዶ ሰብስበው በ 50 ኛ ቀን ያከበሩት የነበረ በዓል ነው።በዓለ ሰዊት በበዓል ጸራቅሊጦስ ተተክቷል።

5.ሠርቀ ወር፦ በሰባተኛ ወር በመጀመሪያ ቀን (ጥቅምት 1) መለከት በመንፋት የሚከብሩት በዓል ነው።በሠርቀ ወር መጠቅ እና አበቅቴ ተተክቷል።

6.ዕለተ አስተሰርዮ፦ይህ በዓል የሚከበረው በሰባተኛ ወር በ 10 ኛ ቀን (ጥቅምት 10) ሲሆን ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት የህዝቡ ኃጢኣት የሚያስተሰርይበት ቀን ነው።ይህ በዓል የሚከበረው የዮሴፍ መሸጥን ምክንያት በማድረግ አባቶቻችን ኃጢአት በእኛ ላይ አይሁን በማለት ያቀርቡ ነበር።በዕለተ አስተሰርዮ የጥምቀት በዓል ተተክቷል።

7.በዓለ መጸለት፦ ይህ በዓል ከጥቅምት 15 ጀምሮ ለ 7 ቀናት ያህል የሚከበር ሲሆን ህዝቡ ከቤት ወጥቶ የቅጠል ዳስ በመስራት ያከብረዋል።በበዓለ መጸለት የልደት በዓል ተተክቷል።

የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፉ አከፋፈል፦ ከላይ እንደ ተጠቀሰው መጽሐፉ 27 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን አከፋፈሉም እንደሚከተለው ይቀረባል

ከምዕራፍ 1-7 ስለ መስዋዕት አይነቶች፣ ከእግዝአብሔር ድህነት ስለመለመንና ለምስጋና

ከምዕራፍ 8-10 ለክህነት አገልግሎት አሮን እና ልጆቹ እንደተሾሙ

ከምዕራፍ 11-14 ስለሚበሉ እና ስለማይበሉ እንሰሳት፣ የእስራኤላዊያን ሴቶች ልጅ ሲወለዱ ስላለው ስርዓተ

ከምዕራፍ 15-16 ከወንድ እና ከሴት ስለሚወጡ ፈሳሾች መንጻት ስነ-ሥርዓት

ከምዕራፍ 17-22 ስለተከለከሉ ጋብቻዎች፣ ከጥንቆላ ስራ ስለመከልከል

ከምዕራፍ 23- 27 ስለ በዓላት አከባበር፣ ስለ ትዕዛዛት መጠበቅ የሚሰገኑ በረከቶች ይተረካል።

ማጠቃለያኦሪት ዘሌዋውያን ህዝበ እስራኤል ከእግዘኣብሔር ጋር በቅድስና ለመኖር እንደችሉ የተሰጡ ህጎች እና የተለያዩ መመሪያዎች ይዟል።የተሰጡት መጠበቅ ወደ ቅድስና ህይወት እንደሚድርስ መሆኑን ሲያሳይ በተቃራኒ መተላለፍ ደግሞ እስከ ሞት የሚደርስ ቅጣት እንደሚያሰከትል ያስተምረናል።ኦሪት ዘሌዋዊያን የኦሪት ዘጸአት ትርጓሜ ነው። ምክንያት በዘጸአት ውስጥ የተሰጡት መመሪያዎች እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረጉ ሰለሚያስተምር ነው። (ዕብ 7፣11)

4.1.4 ኦሪት ዘኁልቅ

ውድ ተማሪዎች ኁልቅ ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ቆጠረ ማለት ነው። እስራኤላዊያን ከግብጽ ምድር ከወጡ በኋላ መቆጠራቸው ስለሚተርክ ዘኁልቅ ተባለ። ኦሪት ዘኁልቅ 36 ምዕራፎች ሲኖሩት በውስጡ የሚከተሉትን ፍሬ ሀሳቦች ይዟል፦

ሀ.ምድረ ከነዓንን እንዲሰልሉ የተላኩ ከ 12 ቱ ሰላዮች ከኢያሱ እና ከካሌብ በቀር የምድሪቱን ለምነት ፍሬዎች በማሳየት ከገለጹ በኋላ በምድሪቱ ላይ ሚኖሩህዝቦች ከእነርሱ እንደሚበረቱ በመናገራቸው እስራኤልዊን ሁከት በማስነሳታቸው ምክንያት 40 ቀን ይፈጅ የነበረውን ጉዞ እግዚአብሔር ተቆጥቶ 40 ዓመት በበረሀ እንዲንከራተቱ አድርጓቸዋል።20 አመት ሞልቷቸው ከግብጽ ምድር ከወጡት መካከል ምድረ ርስትን የወረሱት ኢያሱና ካሌብ ብቻ ነበሩ።

ለ.ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን በማግባቱ አሮንና ማርያም በሙሴ ላይ ማመጻቸው በዚህም ምክንያት ማርያም በለምጽ መመታቷን፣ እና በለአም እስራኤልን ለመርገም ጉዞ እንደጀመረ ያትታል።

የመጽሐፉ አከፋፈል

ከምዕራፍ 1-12

- ✓ እስራኤላዊያን በየንገዳቸው መቆጠራቸው
- ✓ ከሲና ተራራ እስከ ቃደስ በረሀ ድረስ ያደረጉት ጉዞ
- ✓ የሙሴ ኢትዮጲያዊቷን ማግባት አሮንና ማርያምን እንዳስቆጣ በዚህም ማርያም እንደተቀጣች

ከምዕራፍ 13-25

- ✓ ከነአንን ይሰልሉ ዘንድ ስለተላኩ ሰላዮች
- ✓ ስለ 10 ሩ ሰላዮች መቀሰፍ
- ✓ ሙሴ ስለህዝቡ ማማለዱ
- ✓ እስራኤላዊያን ለሙሴ ባለመታዘዛቸው ለ 40 ዓመት በምድረ በዳ መንከራተታቸው
- ✓ በለአም እራኤልን ለመርገም ያደረገው ጉዞ

ከምዕራፍ 26-36

- ✓ ህዝበ እስራኤል ወደ ምድረ ርስት(ከነአን) ለመግባት መዘጋጀታቸውን ይተርካል

ውድ ተማሪዎች መጽሐፉን ጠቅለል ባለመልኩ ስንመለከተው ታላቅ ተአምራትን በማደረግ ከግብጽ ምድር ያወጣቸው የእግዚአብሔር ኃይልን በመርሳት የከነአን ሰዎችን ኃይልን በመስጋት በሙሴ ላይ ህዝቡ በማመጹ ምክንያት የ 40 ቀን መንገድ 40 አመት መሆኑና የሙሴ (የቅዱሳን) የማማለድ ስልጣንን እንዳላቸው ያስተምራል።

4.1.5 ኦሪት ዘዳግም

ዘዳግም፦ ማለት በግዕዝ የተደገመ ማለት ሲሆን ሙሴ ከ 40 ዓመት በፊት በተጻፉት በሶስቱ መጽሐፍት(በኦሪት ዘጸአት፣ዘሌዋዊያንና ዘኁልቅ) ላይ የነበሩት የእስራኤላዊያን ታሪክና ህግ በድጋሚ ለአዲሱ ትውልድ የሚያስታመርበትን ትምህርት የያዘ በመሆኑ ይህን ስያሜ አግኝቷል።ይህ የሆነበት ምክንያት 20 ዓመት ሞልቷቸው ከግብጽ ምድር ከወጡት መካከል በህይወት የተገኙት (ህግና ታሪክ የሚያውቁት) ሙሴ፣ ኢያሱና ካሌብ ሲሆኑ አብዛኞቹ በምድረ በዳ በአመጽ ምክንያት አልቀዋል። ስለሆነም ህጉ ሲሰጥ ያልነበረው አዲስ ትውልድ የእግዚአብሔር ድንቅ ስራ እንዲያውቁና የተሰጡ ህግጋት በመጠበቅ የትውልድ ኃላፊነት እንዲወጣ በማሰብ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሴ በሞአብ አገር ኦሪት አስተምሯቸዋል።

የመጽሐፉ አከፋፈል

ኦሪት ዘዳግም በውስጡ 34 ምዕራፎች የያዘ ሲሆን ለማጥናት ይመችን ዝንድ እንደሚከተለው ይከፈላል፦

ከምዕራፍ 1-4 በሙሴ መሪነት የተከናወነ የእስራኤል ህዝብ ታሪክ መደገም

ከምዕራፍ 5-26 ከእግዚአብሔር የተሰጡ ህግጋት እንደተደገሙና ህዝቡ ህግጋቱንእንዲጠብቅ የተሰጡ ምክሮችን

ከምዕራፍ 27-30 ለሰዎች የተሰጡ ምርጫዎች በመታዘዝ በረከት ባለመታዘዝ መርገም እንዳለ ያስተምራል

ከምዕራፍ 31 ወደፊት ስለሚሆኑ አንዳንድ ነገሮች መግለጽ

ሀ. የሙሴ መሞት

ለ. የእያሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሾም

ሐ. የሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት መቀዝቀዝ

መ. የሰዎች በጥፋት ምክንያት መቀጣት

ከምዕራፍ 32-33 የመጨረሻዎቹ የሙሴ መዝሙርና በረከት እና ስለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነበየው ገለጸ ትንቢት፣

ምዕራፍ 34 ሙሴ በናባው ተራራ የተሰፋ ምድርን መመልከቱና ማረፉንይገልጻል።

4.2 የታሪክ መጽሐፍት ክፍል

ውድ ተማሪዎች በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ አከፋፈል ተረታ መሰረት በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የታሪክ መጽሐፍት ክፍል ነው። ከአርባ ስድስቱ መጽሐፍት መካከል አስራ ሰባቱ የታሪክ ይዘት ያላቸው መጽሐፍት ናቸው። እነዚህ አስራ ሰባቱ መጽሐፍትን በዚህ ክፈለ ትምህርት የምንመለከታቸው ይሆናል። መልካም ንባብ!

የታሪክ መጽሐፍት ተብለው የሚጠሩት መጽሐፍት ከእያሱ ወልደ ነዌ እስከ ዮሴፍ ወደ ኮሪዮን ያሉት ሲሆኑ ቁጥራቸው 17 ናቸው። በታሪክ መጽሐፍት ውስጥ የሚናገኘው ጠቅላላ ሀሳብ በእግዝአብሔር እና በእስራኤል መካከል ስለነበረው ግንኙነት ነው። ከእነዚህ መጽሐፍት አንዳንዶቹ በአይሁድ ቀኖና መጽሐፍት ከነቢያት መጽሐፍ ቢመደቡም ከመጽሐፍቶቹ ይዘት አንጻር 72 ቱ ሊቃውንት በታሪክ መጽሐፍት እንዲመደቡ ወስነዋል።እስራኤላዊያን በሙሴና በኢያሱ መሪነት ምድር ርዕስትን ከወረሱ ጀምሮ እስከ ባቢሎን መርኮ እና ከመርኮ በኋላ ስላሉት አመታት የእስራኤላዊያን ታሪኮች ይተርካል።ከ 17 ቱ የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ በሴቶች የተሰየሙት ሁለት ሲሆኑ እነርሱም መጽሐፈ ሩት (ሙኣባዊት) እና መጽሐፈ አስቴር (እስራኤላዊት) ናቸው። ከዚህ በመቀጠል 17 ቱ የታሪክ መጽሐፍት በዝርዝር እንመለከታለን።

4.2.1 መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ

የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ኢያሱ ሲሆን (8 ፣2 24፣26) ሙሴን እየረዳ ከልጅነቱ ጀምሮ የተከተለው ኢያሱ ከሙሴ ሞት በኋላ ህዝብ እስራኤልን እንዲመራ በእግዚአብሔር የተመረጠ ታላቅ አባት ነው።

<u>እያሱ</u>፡-ማለት አዳኝ፣መሪ፣መድኃኒት ማለት ነው።ኢያሱ የእስራኤል ህዝብ ከስጋ ጠላቶቻቸው ስላዳናቸው መድኃኒት ተብሏል።

<u>ኢየሱስ</u>፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ሁሉ ከነፋስ ጠላት ከሞትና ከዲያብሎስ ያደነን በመሆኑ እውነተኛ መድኃኒት ማለት ነው። (ማቴ.2፣21፣ ሉቃ.2፣10)

የመጽሐፉ ዋና ይዘት ኢያሱ ህዝቡን ለማስተዳደር ያደረገው ትግል እና የተሰፋይቱ ምድር መውረሳቸውን ያትታል። በእግዚአብሔርኃይልበኢያሱ መሪነት ህዝብ እስራኤል የዮርዳኖስ ወንዝን ተሻግረው በተስፋይቱ ምድር ላይ ይኖሩ የነበሩ ነገስታት ድል በማድረግ በየነገዳቸው መስፈራቸው ይተርካል።

የመጽሐፉ አከፋፈል፡- መጽሐፈ ኢያሱ 24 ምዕራፎች በውስጡ ይዟል። እንደሚከለተው ይቀርባል፡-

ከምዕራፍ 1-5 የእስራኤል ህዝብየዮርዳኖስን ወንዝ መሻገርና ወደ ከነዓን መግባት

ከምዕራፍ 6-12 የከነዓንን ሰዎች ማሸነፋቸው /የአሞራዊንን እና የአሦርን ነገስታት ድል ማድረጋቸው/

ከምዕራፍ 13-22 ህዝብ እስራኤል ምድር ከነዓንን በየነገዳቸው መከፋፈላቸው

ከምዕራፍ 23-24 የመጨረሻው የኢያሱ ምክር እና ሞት

ውድ ተማሪዎች መጽሐፈ ኢያሱ ጠቅለል ባለመልኩን ስንመለከተው በውስጡ፡- የቅዱሳን መላዕክት ተራዳይነትና ክብር*(ኢያ.5፣13)*፣ የዕምነት ኃያልነት *(6፣15-21)*፣ የዓላማ ጽናትን እና ለታቦት የሚሰጥ ክብርን ያስተምረናል።

4.2.2 መጽሐፈ መሳፍንት

መሳፍንት፡- ማለት መስፍን የሚለው ቃል ብዙ ሲሆን ትርጉሙም ገዢ፣አስተደዳሪ፣መሪ፣ፈራጅ(ዳኛ) ማለት ነው።ዋና ሐሳቡ እስራኤላዊያንዋና ንጉስ እንዳልነበራቸው እና በእግዚአብሔር ተመርጠው ጠላቶቻቸው ድል በሚያደርጉ መሳፍንት መገዛታቸውን በሰፊው ይተርካል።እስራኤላዊያን ለ 300 አመታት (አንዳንድ መጽሐፍት 450 ዓመታት ይላሉ) 13 በሚደርሱ መሳፍንት ተመረተዋል። ከእነርሱም አንዷ ሴት ስትሆን ስሟም ዲቦራ ይባላል።መጽሐፉ በተለይ የጌዴዎንን፣የባርቅና ዲቦራን፣ዮፍታሔንና የሳምሶያን ታሪክ አጉልቶ ያሳያል።(ዕብ.11፣32-35) ከእነዚህ መካከል አቤሜሌክ የተባለው ህግ እግዚአብሔርን በመቃወሙ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል።መጽሐፉ 21 ምዕራፎች ሲኖሩት ጻፊው ነብዩ ሳሙኤል እንደሆነ ሊቃውንተ ቤ/ክ ያስተምራሉ።ሳሙኤል የኖረው በ 1200 እና በ 1020 ዓ.ዓ መካከል በመሆኑ ይህ ዘመን ዘመነ መሳፍንት የሚባልበት ዘመን በመሆኑ የመጽሐፉ ጸሐፊ ነብዩ ሳሙኤል እንደሆነ ያሳያል።(አንዳንድ ሊቃውንት ሳሙኤል የነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር ገልጦለት ጽፎታል ይላሉ።) በቤተ-እስራኤል ተሹመው እስራኤልን ሲስተዳድሩ የነበሩት መሳፍንት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ጎቶሊያል(3፣1-11) የመሶፕታሚያ ጠላቶቻቸው ድል ያደረገው መስፍን
2. ናኦድ (3፣12-31) ሞአባዊያን፣አሞናዊያንንና አማሌቃዊያን ጠላጦቻቸው የነበሩ ሲሆን አዳኛቸው ናአድ ነበር።
3. ሰሜጋር (3፣31)
4. ዲቦራ (4 እና 5)

5. ጌድዎን (6፣8-11)
6. አቤሜሌክ (9፣1-57)
7. ቶላ (10፣1-2)
8. ኢያኡ (10፣3-5)
9. ዮፍታሔ(11፣1)አሞናዊያን ጠላቶቻቸው ሲሆኑ አዳኛቸው ዮፍታሔ ነበር
10. አብዳን (12፣8-10)
11. ኤሎም (12፣11-12)
12. ዓብዩን (12፣13-15)
13. ሶምሶን (13፣16-31) ከፍልስጤማዊያን ጠላቶቻቸው ያዳናቸው መስፍን ነው።

4.2.3 መጽሐፈ ሩት

ውድ ተማሪዎች መጽሐፈ ሩት በአንስት ከተሰየሙት ጥቅት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል አንዱ ነው።

የመጽሐፈ ሩት ጸሐፊ ነቢዩ ሳሙኤል ነው። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በዘመነ መሳፍንት መጨረሻ አካባቢ ነው። ዋና ታሪኩ ሩት ስለምትባል ሙዓባዊት ሴት ይተርካል። በዚህ ምክንያት መጽሐፉ በስሟ ሊሰየም ችሏል። አቤሜሌክ የሚባል እስራኤላዊ ከኑኣሚንና ከሁለት ወንድ ልጆቿ ጋር በመሆን በሀገረ እስራኤል ረሀብ በነገሰ ጊዜ ወደ ሞኣብ ምድር እንደ እንደ ተሰደደ እና ከልጆቿ አንዱ ሩትን አግብቶ በሞኣብ ምድር እንደ ተቀመጡ በዚህም ህይወቱ እንዳለፈ ይተረካል።

ኑኣሚን በሰው ሀገር በብቸኝነት መኖር አቅቷት ወደ ሀገሯ ስትመለስ ሩትም ‹ህዝብሽ ህዝቤ አምላክሽ አምላኬ› ብላ ከኑኣሚን ጋር ወደ እስራኤል መጥታ ቦኤዝ የሚባል ሰው አግብታ የዳዊት አያት የሆነው ዒዮቤድን መውለዷ ይተርካል። በዚህ እምነቷ ከክርስቶስ የዘር ሀረግ ውስጥ ለመቆጠር ብቅታላች። ማቴ 1-15

የመጽሐፉ አከፋፈል

መጽሐፈ ሩት 4 ምዕራፎች በውስጡ የያዘ ሲሆን እንደሚከተለው ይከፈላል፦

ምዕራፍ 1 የአቤሜሌክ ቤተሰብ በሞኣብ ሀገር
ምዕራፍ 2 ሩት በቦኤዝ ማሳ ውስጥ ቃርሚያ እንደቃረመች
ምዕራፍ 3 ሩት እንዲያገባት ቦኤዝን እንዳነጋገረችው
ምዕራፍ 4 ሩት የቦኤዝ ሚስት እንደሆነችና የዳዊትን አያት የእሴይን አባት አብድዩን እንደወለደች ይተርካል።

4.2.4 መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማይ እና ካልዕ

ውድ ተማሪዎች መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ እና ካልዕ እንደ ኢትዮጲያ ኦርቶዶክ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ቀኖና መጽሐፍት አቆጣጠር መሰረት እንደ አንድ መጽሐፍት ይቆጠራል። በቀደሙት ጊዜያት ሁለቱ መጽሐፍት እንደ ሁለት ይቆጠሩ ነበር። 72 ቱ ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ በተረጎሙ ጊዜ ከመጽሐፍቱ ይዘት አንጻር እንደ አንድ እንዲቆጠሩ ወስነዋል። መጽሐፉ የተጻፈው

ከ *1100* ዓ.ዓ-*1000* ዓ.ዓ ገደማ እንደሆነ ይታመናል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊው ነቢዩ ሳሙኤል ነው። *1* ኛ ሳሙኤል በሁለት ይከፈላል፦

ከምዕራፍ 1-24 ነቢዩ ሳሙኤል ጽፎታል

ከምዕራፍ 25-31 ናታንና ጋድ ጽፈውታል

<u>ሳሙኤል፦</u> ማለት እግዚአብሔር ሰማኝ ማለት ነው። የሳሙኤል አባት ህልቃና እናቱ ደግሞ ሐና ይባላሉ። እናቱ ሐና ልጅ በማጣቷ ታዝን እንደነበረ መጽሐፉይናገራል።እግዚአብሔር ወንድ ልጅ ስለሰጣት ስሙን ‹‹እግዚአብሔር ሰማኝ›› ስትል አወጣችለት።

በሊቀ ካህኑ በኤሊ ፊት ያገለግል ነበር።እሱ ሲሞት ነቢዩ ሳሙኤል ሊቀ ካህን ሆኖበእስራኤል ላይ ተሾመ።ሳኦልና ዳዊትን ቀብቶ ያነገሰ እርሱ ነው።በአጠቃላይ የመጽሐፉን ይዘት ስለመለከት የዘመነ መሳፍንት መፈጸሙንና ዘመነ ነገስት መጀመሩን ያትታል።

መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ አከፋፈል

ምዕራፍ 1-7 ስለ ኤሊና ሳሙኤል

ምዕራፍ 8-15 ስለ ሳሙኤልና ሳኦል

ምዕራፍ 16-31 ስለ ሳኦልና ዳዊት በስፋት ይተርካል።

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ አከፋፈል

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ዋና ይዘት አድርጎ የተነሳው የዳዊት አገዛዝን መተረክ ሲሆን ከ 1000 ዓ.ዓ ገደማ በናታንና ጋድ እንደተጻፈ ይታመናል።ይህ ታሪክ በድጋሚ በ 1 ኛ ዜና መዋዕል ከምዕራፍ 11-19 ድረስ ላይ ይገኛል።

ከምዕራፍ 1-4 ዳዊት በይሁዳ ግዛት በኬብሮም ከተማ ለ 7 አመታት እንደነገሰ

ከምዕራፍ 5-10 ቅዱስ ዳዊት ጠላቶቹን አሸንፎ ድል ማግኘቱን፣ መናገሻ ከተማውን ኢየሩሳሌም ማድረጉን እና የታቦተ ጽዮን ወደ ኢየሩሳሌም መመለሱን ይተርካል

ከምዕራፍ 11-19 የንጉስ ዳዊት ችግሮች

ሀ.የንጉሱ ኃጢአትና የደረሰበት ቅጣት (11-12)

ለ. በልጆቹ ከአምኖንና ከአቤሴሎም ጠብ የተነሳ የደረሰበት ችግር (13-14)

ሐ.በዳዊት የመጨረሻ ዘመኖች የሆኑ ልዩ ልዩ አመጻ፣ችግሮችናመከራዎች(20-24)

4.2.5 መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊና ካልዕ

ውድ ተማሪዎች መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊና ካልዕ ልክ እንደ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ ሁሉ ከ *70* ሊቃውንት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በፊት እንደ ሁለት ይቆጠሩ ነበር። ከመጽሐፍቶች በውስጣቸው በያዙት ሐሳብ፣ ምስጢርና በታሪክ የሚመሳሰሉ ስለሆኑ በአንድ እንዲቆጠሩ *72* ቱ ሊቃናት ወስነዋል።

1 ኛና 2 ኛ ነገስት ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን አንስቶ እስከ ይሁዳ መንግስት ማለቂያ ድረስ ያለውን 400 ዓመታት (ከ 1000-590 ዓ.ዓ) የእስራኤልና የይሁዳ ንግስታት ታሪክ ይተርካል። መጽሐፈ ነገስትን ማን እንደ ጻፈ በግልጽ ባይታወቅም አንዳንዶች ኤርምያስ ነው ይላሉ።

የመጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ አከፋፈል

መጽሐፉ 22 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ይቀርባል፦

ከምዕራፍ 1-10

- ሰሎሞን የአባቱን ዙፋን መወረሱን፣ በአባቱ ጠላቶች ላይ የወሰደው እረምጃ፣ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱ ለመስራት የነበረው ትጋትና የሠራው ቤተ መቅደስ ፍጻሜ
- የሰሎሞን ጥበብ ለማየት ንግስተ ሳባ ጉብኝትና በዘመኑ ሰለነበሩት ነብያት ናታን፣ አኪያና ኢዶ ይተረካል።

ከምዕራፍ 11-22

- ሰሎሞን በፍቅረ አንስት ወድቆ ለጣኦት በመስገዱ እግዚአብሔርን ማሳዘኑ፣ ከነገደ ኤፍሬም የነበረው ኢዮርባዓምን በሰሎሞን መነሳቱ
- በሰሎሞን ልጅ በሮብዓም ዘመን የእስራኤል መንግስት ለሁለት መከፈሉንና ሰለ አራቱ የይሁዳን ነግስታት እና ሰለ 8 ቱ የእስራኤል ነግስታት ታሪክ ይተርካል።

የመጽሐፈ ነገስት ካልዕ አከፋፈል

መጽሐፉ 25 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ይቀርባል።

ከምዕራፍ 1-17 በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ታሪክ እስራኤላዊያን በአሶራዊያን እስከተማረኩበት ጊዜ ድረስ የነበረው የይሁዳና የእስራኤል መንግስት ታሪክ ይተርካል።

ከምዕራፍ 18-25 ስለ 16 የይሁዳ ነግስታትና ስለ 11 የእስራኤል ነግስታት በስፋት ይተርካል።

4.2.6 መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ

ዜና መዋዕል ማለት የዕለት ዜና ማለት ነው። ይህም ከአዳም ጀምሮ ያለውን የአይሁድ ታሪክ እስከ ባቢሎን ምርኮ መመለስ ድርስ ያለው ሰለ ሚተርክ ይህንን ስያሜ ሊያገኝ ችሏል። ቀድሞ በአይሁድ ቀኖና መሰረት እንደ አንድ ይቆጠረ ነበር ከሁለት የተከፈለው በሰባ ሁለቱ ሊቃውንት ነው። መጽሐፍ ዜና መዋዕል ሰለሃይማኖት እና ሰለመንፈሳዊ ነገሮች አብዝቶ ያወሳል። መጽሐፍ ነገስት ሰለመንግስት አስተዳደር በይበልጥ ያስረዳል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ እንዳንድ መጽሐፍት ዕዝራ ነው ሲሉ ሌሎች መጽሐፍት ደግሞ ሳሙኤል ነው ይላሉ።

መጽሐፉ ሰለመሲሁ መምጣት ተስፋ ሰለነበረው ይሁዳ ተብሎ ሰለሚጠራው ደቡባዊ መንግስት በሰፊው ይተርካል። በተጨማሪም ሰለእግዚአብሔር ሁሉንቻይነት፣ ባለጠግነት ይገልጣል። (2 ኛ ዜና 2፤6 1 ኛ ዜና 29፤12)

የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ አከፋፈል

ውድ ተማሪዎች መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ በውስጡ 29 ምራፎችን የያዘ ሲሆን አከፋፈሉ እንደሚከትለው ይቀርባል፦

ከምዕራፍ 1-9 ስለ አይሁድ ጥንታዊ መንግስት

ከምዕራፍ 10-12 የሳኦል መሞት እና የዳዊት ታሪክ

ከምዕራፍ 13-16 የታቦተ ጽዮን ወደ እየሩሳሌም መመለስ

ከምዕራፍ 17- 22 ፍልስጤማዊን እና ሶርያውን በእስራኤላዊያንመሸነፋቸውን

ከምዕራፍ 23-26 ንጉስ ዳዊት ሌዋዊያንን መቆጠሩ እና አገለግሎት መመደቡን

ከምዕራፍ 27-29 ጠቢቡ ሰሎሞን ቤተ-መቅደስ እንደሰራ እና ዳዊት ለሰሎሞን አደራ እንደሰጠው ይተረካል።

4.2.7 መጽሐፍ ዜና መዋዕል ካዕል እና ጸሎተ ምናሴ

በቀኖና መጽሐፍት አቆጣጠረ መሰረት መጽሐፍ ዜና መዋዕል ካልይ እና ጸሎት ምናሴ እንደ አንድ መጽሐፍ ይቆጠራሉ።በ 2 ኛ ዜና 33፣18 ላይ የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ የጸለየው ጸሎት ተመዝግቦ ሲለሚገኝ መጸሐፉ (ጸሎተ ምናሴ) ከዜና መዋዕል ካልዕ ጋር አብሮ ኢንዲቆጠር ተወስኗል።

ምናሴ፦ ማለት ማሰረሻ ማለት ሲሆን በ 12 ዓመቱ የይሁዳን ክፍል ለማስተዳደር የነገሠ ሰው ነው። ምናሴ በደግነቱ ከዳዊት ቀጥሎ የሚነሳው የንጉሱ ሕዝቅያስ ልጅ ነው። (1 ነገ 20፣1) ምናሴ ግን አባቱ በሄደበት መንግድ መጓዘን ትቶ በጣኦት አምልኮት እና በተለያዩ በደሎች እግዚአብሔር አሳዘን። ልዑል እግዚአብሔርም በነብዩ በኢሳይያስ አድሮ በ 10 ሩ ነገድ ላይ ያመጣሁትን መከራ አመጣለው በማለት ተናግሮት ነበር። (2 ኛ ነገ 21፣11) የነብዩ ተግሳጽ ከመሰማት ይልቅ በመጋዝ አሰተርትሮ እንዲገደል አድርጎታል። ከዚህ በኃላ የአሶር ንጉስ በብረት ቀፎ አድርጎ ወደ ባቢሎን ወስዶታል። በባቢሎን ሳለ በደሉ በማሰታወስ ንሰሐ ቢገባ እግዚአብሔር ንሰሐውን ተቀብሎት ምሕረት አድርጎለታል። (2 ኛ ዜና 33፣14-26)

ጸሎት ምናሴ ተብሎ የሚጠራው መጽሐፍ አንድ ምዕራፍ እና 13 ቁጥሮች የያዘ ነው። በምናሴ ጸሎት ውስጥ የእግዚአብሔር ፈጣሪነት፣ ኃያልነት፣ ፈራጅነት፣ ይቅር ባይነት እንዲሁ ንሰሐ የተሰጠው ለኃጢአተኞች መሆኑን የሚገለፅ የምስጋና እና የጸሎት መጽሐፍ ነው።

4.2.8 መጽሐፈ ዕዝራ ነህምያ

4.2.8.1 መጽሐፈ ዕዝራ

እንደ ሊቃወንተ ቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ በቅዱስት መጽሐፍት አቆጣጠር መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ እንደ አንድ ይቆጠራሉ። ለዚህ እንደምክንያት የሚጠቀሱ ነጥቦች፦

ሀ. ሁለቱ መጽሐፍት በይዘታቸው ተመሳሳይ በመሆናቸው፣ በመጽሐፈ ዕዝራ ከመጀመሪያዎቹ ከስደት ተመላሾች መካከል የነህምያ ስም መጠቀሱ እና በመጽሐፈ ነህምያ የካህኑ የዕዝራ ስም መጠቀሱ።

ለ. ሁለቱም መጽሐፍት የሚተርኩት አስራኤል ከባቢሎን ምርኮ በኃላ ስለነበረ ሰለይሁዳ መንግስ ነው።

መጽሐፉ የተጻፈው በ 455 ዓ.ዓ ገዳማ ሲሆን በፋርስ ንጉስ በቂሮስ ፍቃድ አይሁዳ ከምርኮ ተመለስው ቤተ መቅድስ ስለመስራታቸው ይተርካል።

የመጽሐፉ አከፋፈል

መጽሐፈ ዕዝራ 10 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ይከፈላል፦

ከምዕራፍ 1-6 በፋርስ ንግሱ በቂሮስ አስራኤላዊያን ወደ ሀገራቸው እንደመለሱ የተነገረው አዋጅ

ከምዕራፍ 7-10 የተቀሩት አስራኤል ነገዶች በዕዝራ መሪነት ወደ ኢየሩሳሌም መመለሰቸው።

በዕዝራ ልመና እና ለቅሶ ከስደት የተመለሱ ወገኖቹ ከአረማዊያን ሚስቶች እንደሚለዩ ቃል መግባታቸው ተዘርዝሯል።

4.2.8.2 መጽሐፈ ነህምያ

ነህምያ ማለት እግዚአብሔር አድነኝ/አዳኝ/ ማለት ነው። ከምርኮ በኃል ከሚጠቀሱ ነብያት መካከል ነው። ነህምያ የፋርስ ንጉስ ለነበረው አርጤክስ በቤተ-መንግስት ጠጅ አሳላፊ የነበረ አይሁዳዊ ነው። ነህ 1፣1-6 መጽሐፉን የጻፈው ራሱ ነህምያ ነው። ነህ 1፣1 በሃሳ ሁለት/52/ ቀናት ውስጥ በንጉሱ ፍቃድ በእርሱ እምነት ጽናት የእየሩሳሌም ቅጥር ተገንብቷል።

መጽሐፈ ነህምያ ይዘቱን ስንመለከት ስለ እየሩሳሌም ቅጽር መገንባት ይተርካል።

የመጽሐፉ አከፋፈል፦

መጽሐፈ ነህምያ በውስጡ 13 ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን ለአጠናን ይመች ዘንድ እንደ ሚከተለው ይከፈላል፦

ከምዕራፍ 1-2 -የእየሩሳሌም ቅጽሮች መፍረስና እንደገና መታነጽ

ከምዕራፍ 3-6 - ነህምያ በተቃውሞ ውስጥ አልፎ ቅጽረ እየሩሳሌምን መስራቱ

ከምዕራፍ 7-13 - እስራኤላዊያን በአምልኮተ እግዚብሔር መጽናታችን ይተርካል።

4.2.9 መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤልና መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

ውድ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ ቀኖና መጽሐፍት አቆጣጠር መሰረት መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤልና መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ እንደ አንድ ይቆጠራሉ።

4.2.9.1 መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

ሱቱኤል (ስላትያል) የጻፈውን የካህኑ ዕዝራ ድርብ ስም ነው። ሱቱኤል ማለት በግእዝ ዘስየት /ናጠጣ/ ማለት ነው።

ይዘቱ፡- ካህኑ ዕዝራ በተማረከበት ሀገር ስላያቸው ራዕይ፣ ለጠየቀው ጥያቄ ያገኘው ምላሽ፣ 40 ቀን ጾም ቅዱሳት መጽሐፍትን እንደጻፈ እና በጸሎት ጸጋና በረከትን ከእግዚአብሔር እንዳገኘ ይተርካል።

አከፋፈል፡- መጽሐፍ ዕዝራ ሴቱኤል 13 ምዕራፎች ሲኖሩት በ 3 ዓበይ ክፍሎች ይከፈላል፡-

ከምዕራፍ 1-3 ዕዝራ ከእግዚአብሔር እና ከመላዕከ እግዚአብሔር ከቅዱስ ዑራኤል ጋር መነጋገሩ

ከምዕራፍ 4-7 ስለ አዕማደ ምስጢራት፣ ጻድቃን እና ስለ ኃጥአን ያየው ራዕይ

ከምዕራፍ 8-13 ዕዝራ መጾሙና ስለተገለጸለት ምስጢር ይገልጻል።

4.2.9.2 መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

ይዘቱ፡- ይህ መጽሐፍ በመጽሐፍ ዕዝራ ቀዳማዊ ከምዕራፍ 7-9 እና በዚና መዋዕል ካልዕ ከምዕራፍ 35 እስከ 36 የተገለጸውን ታሪኮች አብራርቶ ይተነትናል።

አከፋፈል፡-መጽሐፉ 9 ምዕራፎች ሲኖሩት በካህኑና በጻፊው ዕዝራ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።

ከምዕራፍ 1-2 ከምርኮ መልስ ቤተ-መቅድስ ማነጻቸውን

ከምዕራፍ 5-7 በዳርዮስ ፈቃድ ቤተ-መቅድስ መስራቱ

ከምዕራፍ 8-9 የፋርስ ንጉስ እየሩሳሌምን መውረሩ ያትታል።

4.2.10 መጽሐፈ ጦቢት

ጦቢት/ጦቢና/ ማለት ስናይ፣ ጎር ማለት ነው። ይህ መጽሐፍ ስለ ጦቢት እና ጦቢያ በንጉስ ስልምናሶር ዘመን የደረሰባቸው መከራና እግዚብሔር በመልአኩ ሩፋኤል አማካኝነት አንዴት እንደረዳቸው የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።

ይዘቱ፡- መጽሐፈ ጦቢት በንጉስ ስልምናሶር ጊዜ በስደት የነበሩት አይሁድ ሲሞቱ ጦቢት የተባለው ስው ይቀብራቸው እንደነበር፣ ይመክራቸውም እንደነበር ያትታል። ዓይኑ ጠፍቶበት በእግዚብሔር መልአክ አማካኝነት እንዴት እንደዳነ ይገልጻል።

የመጽሐፉ አከፋፈል፡- መጽሐፈ ጦቢት 14 ምዕራፎች ሲኖሩት በ 3 ይከፈላል፡-

ከምዕራፍ 1-3 ጦቢት በበጎ ስራው ያገኘው መከራና የሚራ ጸሎት

ከምዕራፍ 4-12 ጦቢት በመከራው ጊዜ ልጁ ጦቢያን ወደ ወገኖች ቢልከው ቅዱስ ሩፋኤል በስው ተመስሎ እንዴት እንዳዳነው

ከምዕራፍ 13-14 የጦቢት ምስጋና እና ምክር እናገኛለን።

4.2.11 መጽሐፈ ዮዲት

ይህ መጽሐፍ ከታሪክ መጽሐፍት መካከል አንዱ ሲሆን ንጉስ ናቡከደነጾር አሰራኤላውያንን ለመወጋት የላከው ሆሎፎርኒስ የተባለ የጦር መሪ ዮዲት በተባለች እስራኤላዊት ሴት እጅ እንዴት ተላለፎ እንደተሰጠና እንደተገደለ የሚያትት መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ አስራ ስድስት(16) ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

ውድ ተማሪዎች መጽሐፈ ዮዲት እግዚብሔር ልጆቹን ለማዳን እንዴት አንደሚሰራ ያስተምራል።

4.2.12 መጽሐፈ አስቴር

የቀድሞ ሰሟ ሀዲሳ ይባል የነበረው አስቴር የንጉስ አርጤክስ ሚስት ሆና በወገኖቿል ላይ የተቃጣውን የሞት አደጋ በእግዚብሔር ፍቃድ ማስቀረቷን የሚተርክ መጽሐፈ ነው። አስቴር ማለት ‹‹ኮከብ›› ማለት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚብሔር ስም በየትኛው ቦታ ያለተጠቀሰ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ በምርኮ የሚኖሩት እስራኤላዊያን በሚኖሩበት ባዕድ ሀገር የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ታላቅ አደጋ ስለሚያስከተል ነበር።

የመጽሐፉ አከፋፈል

የዚህ መጽሐፍ ጻፊ መርዶክዮስ ሲሆን መጽሐፉ 10 ምዕራፎችን በውስጡ ይዟል።

ከምዕራፍ **1-2** የፋርሱ ንጉስ አርጤክስ ሚስቱን አስጢንን ፈቶ አይሁዳዊቱን አስቴርን ያገባ መሆኑን፣ እናትና አባት የሌላት አስቴር አጎቷመርዶክዮስ እንደ አባት እንዳሳደጋት፣ መርዶክዮስ በንጉሱ ላይ የተቃጣውን የግድያ ሴራ ማጋለጡ ይዘርዝራል።

ከምዕራፍ **3-5** ሐማ የተባለ ሰው ወደ ስለጣን መምጣቱ፣ መርዶክዮስ ለሐማ አልሰግድም በማለቱ ሐማ የአይሁድ ዘርን ሁሉ በአንድ ቀንለማጥፋት ከንጉስ ፍቃድ መቀበሉ ተገልጿል።

ከምዕራፍ **6-10** መርዶክዮስ የአስቴርን እርዳት መጠየቁ፣ አይሁድ በጾምና ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቆማቸው፣ አስቴር ንጉሱና ሐማንግብዣ መጥረቷ፣ የመርዶክዮስ መሾምና የሐማ መሰቀል እንዲሁም አይሁድ ፋሪም በዓል ማክበራቸው ይተርካል።

4.2.13 መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ

ውድ ተማሪዎች መቃቢስ /መቃባ/ ማለት ጸረ-ጠላት፣ ቀስት፣ ጀግኖች ማለት ነው። መጽሐፈ መቃብያን የተለያዩ ታሪካዊና መንፈሳዊ ይዘቶች ያሏቸው ስምንት መጽሐፎች አሏቸው። ነገር ግን ማን እንደጻፋቸው በውል አይታወቁም። ከእነዚህ መጽሐፍቶች ውስጥ ሦስቱ በግዕዝና በአማርኛ ተተርጉመው ይገኛሉ። በፍትሐ ነገስት ውስጥ ስማቸው የተጠቀሱ ግን ወደ አራት የሚሆኑ ስዎች አሉ እነሱም፡-

1. መቃብያን ዘመቃቢስ አልዓዛር
2. መቃብያን ዘመቃቢስ ሞዓብ
3. መቃብያን ዘመቃቢስ ዘብንያም
4. መጽሐፈ መቃብያን ራብዕ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ዜና አይሁድ /ዜና ሥርወ/ ናቸው።

መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ፡-ይህ መጽሐፍ 36 ምዕራፎች አሉት። በዚህ መጽሐፍ ዉስጥ የብንያም ወንድሞች የአይሁድን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ለመጠበቅ ሲባል ከሌሎቹ ነገስታት ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ እንመለከታለን ።

ይዘቱ ፡- አርበኛ የሆኑ 3 ልጆች ለጣኦት አንሰግድም በማለታቸዉ ንጉስ እንዳሰቃያቸዉ፣ ከብሉይ ኪዳን ታሪኮችን ምሳሌዎችን እየጠቀሰ ስለ በረከትና መርገም ይገልፃል ።

መጽሐፉ አከፋፈሉ፡- 36 ምዕራፎች ያሉትን መጽሐፈ መቃቢያን ቀዳማዊ በ 3 ክፍሎች ከፍሎ መመልከት ይቻላል ።

ከምዕራፍ 1-5 ስለ ጲሩዳይዳ ግፍ እና የመቃቢስ ሰማዕትነት

ከምዕራፍ 6-11 ስለ ዳግም ምጽአት

ከምዕራፍ 12-36 በብሉይ ኪዳን ስለ ነበሩ አበዉና እስራኤላዉያን ይናገራል ።

4.2.14 መጽሐፈ መቃብያን ካልዕና ሣልስ

4.2.14.1 መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ

ይህ መጽሐፍ 21 ምዕራፎች አሉት ። በግሪክ ቋንቋ እንደተጻፈ ይታመናል።

ይዘቱ፡- እስራኤላዊያን በድለዉ ሞአባዊ መቃቢስ እንዲነሳባቸዉ እስራኤልን በሰይፍ ገድሎ ሲታበይ እግዚያብሔር በመቃቢስ ስራ ተቆጥቶ ነብይ ልኮ በንስሐ እንዲመለስ ሲነግረዉ በእግዚያብሔር ፊት ራሱን አዋርዶ ምህረት መግኘቱን ።

መጽሐፉ አከፋፈሉ፡- በ 3 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል ።

ከምዕራፍ 1-4 የመቃቢስ ዘሞዓብ የተባለዉን ንጉስ ያደረሰዉን ጥፋት በንስሐ ተመልሶ የሰራዉን በጎ ስራና ዕረፍቱ

ከምዕራፍ 5-12 የመቃቢስ ዘሞዓብ ልጆች በእግዚያብሔር ስላመኑ ጲሩዳይዳ የተባለ የከላዉዲያን ንጉስ ያደረሰባቸዉ መከራ

ከምዕራፍ 13-21 የመቃቢስ ዘሞዓብ ልጆች አብነት አድርጎ ትንሳኤ ሙታን የተሰጠ መልስ የያዘ መጽሐፍ ነዉ ።

4.2.14.2 መጽሐፈ መቃቢስ ሣልስ

አስር/10/ ምዕራፎች ሲኖሩት በዋነኝነት መጽሐፍም የብሉይ ኪዳን ታሪኮች እየጠቀሰ የጽድቅና የኩነኔን፣ የትንሳኤ ሙታንን፣ ዲያቢሎስ የሰዉ ልጆችን የሚያሰናክልባቸዉ መንገዶች የያዘ ነዉ ። በግሪክ ቋንቋ እንደተጻፈ ይታመናል። ይህ መጽሐፍ ከመቃቢያን ሁለት ጋር እንደ አንድ ይቆጠራሉ ።

ይዘት፡- ከአዳም ጀምሮ የነበሩትን አበዉ ለአብነት እየጠቀሰ ሰዉን በዚህ ምድር መልካም ከሰራ በወዲያዉም ዓለም መልካም እንደሚገጥመን መጥፎም ነገር ስንሰራ እንዲሁ እንደሚገጥሙንና ስለንስሐና ስለመንግስተ ሰማያት የገልፃል ።

አከፋፈል:- በ 3 ዓበይት ምዕራፎች ይከፈላል ፡-

ከምዕራፍ 1-3 ስለሰይጣን ስለ አዳምና ሔዋን ዉድቀት

ከምዕራፍ 4-6 ስለ ሰይጣን ዉድቀት ስለ ጌታችን ማዳንና ጻድቃንና ኃጥኣን

ከምዕራፍ 7-10 በእግዚያብሔር ስለ ማመንና ስለ ኢዮብ ይናገራል ።

4.2.15. መጽሐፍ ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን / መቃቢያን ራብዕ /

ዮሴፍ ማለት ይጨምር ይዲገም ማለት ነዉ ። የኮሪዮን ልጅ ዮሴፍ እንደጻፈዉ ይታመናል ። ይህ መጽሐፍ ዜና አይሁድ/ መጽሐፍ ስርዉ / በመባል ይታወቃል ። በጣም ረጅም መጽሐፍ ነዉ ። ከአዳም ጀምሮ እስከ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ያለዉን ታሪክ ይተርካል ።

ይዘት ፦ ከአዳም ጀምሮ 70 ዓ.ም በጥጦስ መሪነት እየሩሳሌም እስከ ጠፋችበት ድረስ ያለዉን አይሁድ ታሪክ ይተርካል ።

የመጽሐፉ አከፋፈል ፦ መጽሐፉ 8 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በ 8 አበይት ክፍሎች ይከፈላል ።

1. ስለ አዳም
2. ስለ ንጉስ እንጥያኮስ ፥ መቄዶናዊ ፥ ስለዮናናዉያን ንጉስ
3. ስለ እስክንድርያ ንግስት የህርቃልና የአስትሮ በሎስ ልጅ
4. የህርቃል ከፋርስ መግባቱና መገደሉ
5. ስለ አስቴር ንግስና ስለ አርኬላኦስ ታሪክ
6. የሄሮድስ ልጅ አደርኬላኦስ ታሪክ
7. ስለ ስምኦን ያረብሃዊ
8. ስለ ቤተ መቅደስ የሮማዉያን ከአይሁድ ጋር መጣላታቸዉ ይተርካል ።

ውድ ተማሪዎች ይህ መጽሐፍ ከትልቅነቱ የተነሳ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ ዉስጥ አይገኝም ።

4.2.16 መጽሐፈ ኩፋሌ ፦

ኩፋሌ ማለት የተከፈለ /መከፈል/ ማለት ነዉ። መከፈሉም ለኦሪት ነዉ። በኦሪት መጽሐፍ ዉስጥ የምናገኝዉን ታሪኮች አስፋፍቶ ይተርካል። ከሥነ-ፍጥረት ጀምሮ እስከ እስራኤላዉያን ከግብፅ መዉጣት ይተርካል ። ይህንን መጽሐፍ የጻፈዉ ነብዩ ሙሴ እንደሆነ ይታመናል ። ኩፋሌ 1 ፥ 1-4 ቦታደዉም ደብረ ሲና እንደሆነ ይነገራል ።

ይዘቱ ፦ ስለ ስነ-ፍጥረት፣ አርስተ አበዉ የነበሩትን በሱባኤ ይገልፃል ። እንዲሁም እስራኤላዉያን ከግብፅ ስለመዉጣታቸዉ ይነገራል።

መጽሐፉ አከፋፈል ፦ መጽሐፉ 34 ምዕራፎች ሲኖሩት በ 4 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል ።

1. ምዕራፍ 1 የሙሴ ከእግዚያብሔር ጋር መገናኘቱን /መነጋገሩን/
2. ከምዕራፍ 2-7 ከአዳም ጀምሮ እስከ አብርሃም ድረስ ያለዉን ታሪክ
3. ከምዕራፍ 8-32 የያዕቆብና የልጆቹ ታሪክ
4. ከምዕራፍ 33-34 የሙሴ አነሳስና በግብጻዉያን ላይ ድል ይገልጻል ።

4.2.17 መጽሐፈ ሄኖክ፦

ይህ መጽሐፍ የአዳም ሰባተኛ ትዉልድ በሆነዉ በሄኖክ የተጻፈ መጽሐፍ ነዉ። በመጀመሪያ የተጻፈዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነዉ። ሄኖክ ማለት አዲስ /ተሐደተሰ/ ማለት ነዉ። ይህ መጽሐፍ በዉስጡ 42 ምዕራፎች የያዘ ሲሆን ስለክርስቶስ ስለ

መልአክት ስለ ፀሐይና ጨረቃ ዑደት ስለ እፅዋት ስለ ጻድቃን እና ኃጥአን በኖህ ዘመን ስለተፈጸመዉ ኃጢያትና ቅጣት ያወሳል።

የመጽሐፈ ሄኖክ አከፋፈል :- 42 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፈ ሄኖክ በ 4 አበይት ክፍሎች ይከፈላል ።

ከምዕራፍ 1-20 ስለ ቅዱሳን መልዕክትና ስለ ጌታችን

ከምእራፍ 21-26 ስለ ፀሐይና ጨረቃ ስለ ከዋክብት ወቅቶች ይናገራል ።

ከምዕራፍ 27-35 ስለ እስራኤል የተነገረ ተንቢት

ከምዕራፍ 36-42 ፃድቃንና ኃጥአን ዋጋና ቦታ ይገልጻል ።

4.3 *የመዝሙርናየጥበብመጽሐፍት* ፦

ውድ ተማሪዎች የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አከፋፈል መስረት በሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የመዝሙር እና የጥበበ መጽሐፍት ይባላል። እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጽሐፍት ቀኖና እና አቆጣጠር መሰረት የመዝሙርና የጥበብ መጽሐፍት የሚባሉት በአጠቃላይ *8* /ስምንት/ መጽሐፎች ሲሆኑ እነርሱም እንደሚከተለዉ ይዘረዘራሉ ፦

1. *መጽሐፈ ኢዮብ*
2. *መዝሙረ ዳዊት*
3. *መጽሐፈ ምሳሌ*
4. *መጽሐፈ ተግሳፅ*
5. *መጽሐፈ መክብብ*
6. *መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን*
7. *መጽሐፈ ጥበብ*
8. *መጽሐፈ ሲራክ ናቸዉ ።*

እነዚህ የመዝሙርና የጥበብ መጻሕፍት የራሳቸዉ የሆነ አከፋፈልና የራሳቸዉ የሆነ ይዘት አላቸዉ ። ወደ አከፋፈላቸዉ ከመሄዳችን በፊት የመዝሙርና የጥበብ መጽሐፍት ምን ማለት እንደሆነ /ትርጓሜዉን/ እንመልከት ።

መዝሙር ፦ ማለት ምስጋና ማለት ነዉ ። ጥበብ፦ ማለት ማስተዋል ፤ መንፈሳዊ እዉቀት ፤ ማንኛዉንም ነገር ለማግኘት የመመርመር ችሎታ ማለት ነዉ ። (መ/ር “ቸሬ አበበ እና ዲ/ን ቴዎድሮስ በየነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ገጽ 49 2001 ዓ.ም)

ስለዚህ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የሚገኙት መጽሐፍት እግዚአብሔር መለመኛ፣ መማፀኛና ማመስገኛጸሎቶችና የእግዚአብሔር ድንቅ ስራ ምስጋና ጥበቡን አካተው ይዘዋል።

ይህንን መጽሐፍ ተከፍሎ ከመተርጎሙ በፊት በዕብራይስጡ የቅኔ መጽሐፍ በመባል ይታወቅ ነበር።በስምና ወርቅ በምሳሌም የተጻፉ በመሆናቸዉ አቀራረባቸዉ ቅኔያዊ በመሆኑ ይህን ስያሜ አግኝቷል ።

1. መጽሐፈ ኢዮብ

ኢዮብ፦ ማለት አበባና ጨረቃ ማለት ነዉ ። በቮልጋታና ሳብዓ ሊቃናት ዮብ/ጆብ/ ይባላል ። ይህ መጽሐፍ 42 ምዕራፎች አሉት። መጽሐፉን በእርግጠኝነት ማን እንደፃፈዉ አይታወቅም ። ሊቃዉንቱ ኤልሁ በሚለዉ ይስማማሉ /ኢዮብ 9፡23/። የተፃፈበት ዘመን ከ

1500 ዓ.ዓ. በፊት /ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነዉ / ተብሎ ይገመታል። የተጻፈበት ቋንቋ ሱርስት ነዉ። መጽሐፉ በስድ ንባብ /ጽሑፍ/ መልክ ከተጻፉት የመጀመሪያዉና የመጨረሻዉ ክፍሎች በስተቀር አብዛኛዎቹ በግጥም መልክ ነዉ።

አጠቃላይ ይዘቱ፦ እግዚአብሔርን በሚወዱና በሚታዘዙ ሰዎች ላይ ሊደርስ እንደሚችልና በትዕግስት ካሳለፉት መከራዉ እንደሚወገድና በረከትንም ከእግዚአብሔር በእጥፍ እንደሚያገኙ የሚያስተምር መጽሐፍ ነዉ ። የዚህ ታሪክ ባለቤትየሆነዉ ጻድቁ ኢዮብ ስለደረሰበት መከራ እና መከራዉን በመታገሱ ስላገኘዉ በረከት በሰፊዉ የሚገልጽ መጽሐፍ ነዉ ።

የመጽሐፉ አከፋፈል፦

መጽሐፉን በ 3 ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ ማጥናት ይቻላል።

1 ኛ. ከምዕራፍ 1 እና 2

- በእነዚህ ምዕራፎች ዉስጥ ኢዮብ 7 ወንዶች እና 3 ሴቶች ልጆቹን የነበረዉን ሃብት ማጣቱ፣ በጎቹን ግመሎቹን በሬዎቹንና አህዮቹን በሞት በመነጠቁ የደረሰበትን ፈተና እናገኛለን /በሰይጣን መፈተኑን/

2 ኛ. ከምዕራፍ 3 እስከ 37

- ከደረሰበት መከራ የተነሳ ምነው ባልተወለድኩ ብሎ ሕይወቱን ማማረሩን
- አልፋዝና በልዳስ ሰፊር በኢዮብ ላይ የደረሰው መከራና ችግር ከኃጢያት ነው በማለት ያቀረቡት ወቀሳ /ያደረጉት ምልልስ/

3 ኛ ከምዕራፍ 38 እስከ 42

- የእግዚአብሔር ትምህርት በዐውሎ ነፋስ ሆኖ ለኢዮብ ስለ ሰዎች ንግግር ከንቱነት የሰጠው መልስ
- እግዚአብሔር የሚያደርገውን ያውቃል ብሎ ከብስጭቱ ስለማረፉ
- ከእግዚአብሔር ቁጣ ይድኑ ዘንድ ስለወዳጆቹ መጸለዩ
- ኢዮብ የጠፋበትን ሃብት በእጥፍ ማግኘቱ ልጆቹን እስከ አራት ትውልድ ድረስ እንዳየና እድሜ ጠግቦ እንደሞተ እናገኛለን።

2. መዝሙረ ዳዊት

ውድ ተማሪዎች መዝሙረ ዳዊት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ከፍተኛ አገልግሎት /አስተዋጽኦ/ አለው። መዝሙረ ዳዊት መዘምራን በዜማ ስልት የሚገለግሉበት መነኮሳትና ካህናት በሌሊት በቤተ-ክርስትያን እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበት ምስባክ ነው። ምእመናን በያሉበት ሁነው እየጸለዩ መላእክት ብርሃንን የሚያቀርቡበት መላእክተ ጽልመትን የሚያርቁበት ሕሙማን የሚፈወሱበት እጅግ ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ ነው።

ዳዊት፦ ማለት ልበ አምላክ፣ ጎሩይ ማለት ነው። መዝሙረ ዳዊት በውስጡ 150 መዝሙር፣ጸሎት፣ ትምህርትና ቅኔ ይገኝበታል። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ያሉት መዝሙሮች በአብዛኛው የእርሱ በመሆናቸው የዳዊት መዝሙር ሲባሉ መዝ. 146 እና 148 ግን የሐጌና የዘካሪያስ ናቸው።

- በቶራ ልጆች ስም የሚጠሩ 11 መዝሙሮች አሉ።
- የአሳፍ መዝሙሮች የሚባሉት 12 መዝሙሮች መዝ 50.73.79.90.96 ወዘተ

- በኢታን የምትደረስ መዝ 93.

መዝሙረ ዳዊት አሁን ባለበት ደረጃ ያዘጋጀው ካህኑ እዝራ ነው። መዝሙሮቹ በተለያየ እንጂ በአንድ ዘመን ብቻ የተዘጋጁ አይደሉም። መዝ. 74.24 መዝ.3.30 እና መዝ 70 የተዘጋጁት ከእስራኤላውያን ምርኮ በኋላ ነው።

አጠቃላይ ይዘቱን ስንመለከት የሰውን የሕይወት ዘመን የሚያሳይ ነው። በሕይወቱ የሚያጋጥሙትን ኃዘንና ደስታን፤ መልካምና ክፉ፤ መውደቅና መነሳትን፤ ችግርና ምቾትን፤ ከእግዚአብሔር መራቅና ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የያዘ መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዳዊት ስለራሱ የተናገረው፣ ስለክርስቶስ፤ ጻድቃንና ኃጥአን በመዝሙር መልክ ይገልጻል።

1 ኛ. አከፋፈሉ

1 ኛ. ከመዝ. 1 እስከ መዝ 40
2 ኛ. ከመዝ. 41 እስከ መዝ.71
3 ኛ. ከመዝ.72 እስከ መዝ 88
4 ኛ. ከመዝ 89 እስከ መዝ. 105
5 ኛ. ከመዝ. 106 እስከ መዝ. 150

2 ኛ. አከፋፈሉ በአስር አርዕስት ሲከፈል

1 ኛ. መዝ. 1፤1 ለሁሉም የሚሆን ተግሳፅና ምክር
2 ኛ. መዝ. 2፤1 ስለክርስቶስ
3 ኛ. መዝ. 3፤1 ስለራሱ (ቅዱስ ዳዊት)
4 ኛ. መዝ. 4፤1 ስለመናኛዊያን
5 ኛ. መዝ. 5፤1 ስለትሩፋት
6 ኛ. መዝ. 13፤1 ስለ ሕዝቅያስ
7 ኛ. መዝ. 34፤1 ስለ ኤርሚያስ
8 ኛ. መዝ 43፤1 ስለ መቃቢያን
9 ኛ. መዝ. 71፤1 ስለ ልጁ ሰሎሞን። የቀሩት 140 ዎቹ በአነዚህ ስር ይካተታሉ።

ከላይ በመጀመሪያው ላይ ያለው አከፋፈል ላይ እያንዳንዱ ክፍል ፍጻሜው የሚታወቀው ከዘላለም እስከ ዘለዓለም እግዚአብሔር ይባረክ አሜን የሚሉ ቃላት ስለተጻፈባቸው ነው።

ቤተ-ክርስትያናችን ደግሞ አስሩን መዝሙሮች በአንድነት እንደ ንጉስ በሚል ስያሜ በአስራ አምስት ትከፍለዋለች። የሰው ልጅ ሲከፋና ሲጨንቀው በሚያጋጥሙት ችግሮችና ተድላዎቹ ምን መጸለይ እንደሚገባው በሚቀጥለው ሰንጠረዥ በመመልከት መረዳት ይቻላል።

በሚጸልዮበት /በሚዘምሩበት/ ሁኔታ	የሚጸለየው /የሚዘመረው/ የመዝሙር ክፍል
▪ ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ	መዝ. 8

	፣29፣33፣46፣89፣94፣103፣104፣105፣106፣111፣118፣138፣145
▪ የእግዚአብሔርን የባሕሪይልዕልና ለመግለጽና ለማወደስ	መዝ. 19፣29፣33፣47፣65፣66፣68፣76፣81፣89፣92፣95፣96፣98፣135፣136፣137፣138፣150
▪ አንድ ኃጢአተኛ ከኃጢአቱ በንስሐ ተመልሶ የእግዚአብሔርን ይቅርታ የሚጠይቅበት	መዝ. 6፣31፣37፣50፣85፣101፣102፣142
▪ጭንቀትን፤ ፈተና፤ ውርደትን፤ ሀዘን ስደትና ጭቆና በሚያጋጥም ጊዜ	መዝ.
▪ ፍርሃትና ፈተና ሲያጋጥም ▪ በእግዚአብሔር ለመተማመን	
▪ ካህናት የቤተ-መንግስትን ደረጃዎች ሲወጡ የሚዘምሯቸው የማዕረግ መዝሙሮች	

ሌሎች ትምህርቶችንና ድርጊቶችን የያዘ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች

▪ መሰረተ እምነትንና የእግዚአብሔር ብቸኛ አምላክነት የሚያመለክቱ	
▪ በመለኮት አንድነት በአካል ሶስትነት የሚያመለክቱ	
▪ ስለ ትንሳኤ ሙታንና ከዚህ በኋላ ስለሚሆነው ፍርድ	
▪ ስለ ክርስቶስ እና ስለክርስትና ዘመን የተነሳ ትንቢቶች	
▪ ስለዳዊትና ስለ ሕዝቡ ታሪክና ድርጊት	

መዝሙረ ዳዊት ከላይ በአስር አርእስት ተከፋፍሎ ካየነው በተጨማሪ በውስጡ ሰባት አቤት ትምህርቶችን ይዟል። እነርሱም፡-

1. ጠላትን መውደድ መዝ. 16፣4
2. ትሕትና መዝ 21፣10
3. ሃይማኖት መዝ 21፣10
4. ተስፋ መንግስተ ሰማያት መዝ. 26፣1
5. ኃጢያትን ማመን መዝ. 37፣4
6. ይቅርታ መዝ 50
7. ምጽአት መዝ. 111፣8 ናቸው

3. መጽሐፈ ምሳሌ

መጽሐፈ ምሳሌ በዕብራይስጡ ማሻል ይባላል። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በጠቢቡ ሰሎሞን ነው።ሰሎሞን ማለት መስተፋቅር መስተሳልም ማለት ነው። ምሳሌ 1፣1

መጽሐፉ በውስጡ 24 ምዕራፎች አሉት። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መፍቀሬ ጠቢቡ ሰሎሞን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት መኖር እንዳለበት በጥበብ ያስተምራል። ይህ መጽሐፍ በ 950 ዓ.ዓ ቅ.ል.ክ ተጽፏል ተብሎ ይገመታል።

አጠቃላይ ይዘቱ ጠቢቡ ከእግዚአብሔር ጋር በመተባበር እውቀትን ማስተዋልን አግኝቶ በስራ ላይ ስለማዋሉ ነው። በሰው የሚመክር በምሳሌ የሚያስተምርነው።

መጽሐፈ ምሳሌ በ 3 አበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ከምዕራፍ 1 እስከ 9

- በዚህ ክፍል ውስጥ ጥበብን መማር እንደሚጠቅም አለመማር እንደሚጎዳ የተነገረበት ነው።

ከምዕራፍ 10 እስከ 22

- በእግዚአብሔር ፈቃድ ልብን ለማቅናትና ጸባይን ለማረም አስተሳሰብን ለማጎልበት በስነ ምግባር ለመታነጽ የሚረዱ ተግሳጽና ትምህርቶችን በምሳሌ የሚገልጽ ነው።

ከምዕራፍ 23 እስከ 24

- በቀላል የስብከት መንገድ ጥበብን ለመማር፤ ትእዛዞች፣ ምክሮችና መመሪያዎች ይገኙበታል።

4. መጽሐፈ ተግሳፅ

ውድ ተማሪዎች ተግሳጽ ማለት ምክር ማለት ነው። ይህ መጽሐፍ 7 ምእራፎች ያሉት ሲሆን በአቀራረቡ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መጽሐፍ ነው። መጽሐፈ ተግሳጽን የጻፉት ጠቢቡ ሰሎሞን፣ አጎርና ሳሙኤል ናቸው። በመጽሐፉ ያሉት ምሳሌዎች በይሁዳ ንጉስ በሕዝቅያስ ዘመን በነበሩ ነብያት የተሰበሰቡ ናቸው። ይህ መጽሐፍት ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር በአንድነት ከምዕራፍ 25 ጀምሮ እስከ ምእራፍ 31 ድረስ የተካተተ ነው። በግእዝ ግን ራሱን የቻለ ትምህርቶች አሉት።

አጠቃላይ ይዘቱ፡- መንፈሳዊ ምክርን የያዘ ፈሪሃ እግዚአብሔርን የሚያስተምር መጽሐፍ ነው።

መጽሐፍ በ 3 ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍላል።

ከምዕራፍ 1-5 የይሁዳ ንጉስ የሆነው ነብዩ ሕዝቅያስ ሰዎች የቀደቸው የሰሎሞን ምሳሌዎችን የያዘ ነው።

ምዕራፍ 6 የማሳ ሀገር ሰው አጉረ ለኢቲኤልና ለኡካል የተናገረው ቃል ይገኛል።

ምዕራፍ 7፣ የማሳ ንጉስ ልመኤል የተናገረውን ትምህርት የያዘ ነው።

5. መጽሐፈ መክብብ

መክብብ፡- ማለት ሰባኪ ወይም አስተማሪ ማለት ነው። በዕብራይስጡ ቆሃልት /አስተማሪ/ሲባል ሰባው/72 ቱ/ ሊቃናት ኤክሊያስተርን ብለውታል። አባ ሐሮኒሞስ /ጂርም/ ደግሞ ኮንስአናቶስ ብሎታል ይህም የመጽሐፉን ይዘት ያመለክታል ምክንያቱም ሰባኪው እንዲህ ይላል በማለት የተለያዩ ትምህርቶችን ያቀርባልና ነው። ይህን የሚሰብክ መጽሐፍ የጻፈው ጠቢቡ ሰሎሞን ነው መክ. 1፣1-12 በ 900 ዓ.ዓ

አካባቢ ተጽፏል ተብሎ ይገመታል። ንጉስ ሰሎሞን በዚህ በመጽሐፍ እግዚአብሔር የሌለበት ሕይወት ከንቱ ነው አይጠቅም ይላል። መጽሐፉ ተቃራኒ ነገሮችን እያነሳ ሁሉም ከንቱ መሆናቸውን ያስረዳል። ለምሳሌ ደስታ እና ሃዘን መኖርና መሞት ማግኘትና ማጣት ወዘተ ሁሉም ከንቱ መሆናቸውን ያሳያል።

አጠቃላይ ይዘቱ፡- ስለሕይወት አስቸጋሪ ነገሮች ሁሉም ከንቱ መሆኑንና ጥበብ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን በዓለም ስላሉ ተቃራኒ ነገሮች እያነሳ ሁሉም ከንቱ መሆኑን ይገልፃል ከንቱ የሚለው ቃል በመጽሐፍ መክብብ ውስጥ 37 ጊዜ ተፅፎአል።

መጽሐፉ 12 ምዕራፎች ሲኖሩት በ 4 ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

ምዕራፍ 1 ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር እንደሌለ ሁሉም ዞሮ እንደሚመጣ ፍፃሜ እንደሌለው፤

ምዕራፍ 2 በዚህ ክፍል በዓለም ላይ ያሉ ደስታዎች ሁሉ እንዳየና ለምሳሌ መጠጥን፣ ጨዋታን ሀብት፣ እውቀት፣ ስልጣን የሴት ፍቅርን ክብርን ወዘተ... እንዳየ ግን ሁሉም ነፋስን እንደመከተል ስለመሆኑ፤

6. መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን

መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን በሙሽራውና በሙሽራይቱ መካከል የተደረገውን ንግግር ምሳሌያዊ ፍቺ የያዘ መጽሐፍ ነው። እንደ ቅድስት ቤ/ክ አስተምህሮ መሰረት ትርጉማዊ ፍቺው እንደሚከተለው ይቀርባል።

1. በብሉይ ኪዳን፡- ሙሽራው የእግዚአብሔር ሙሽሪት የቤተ እስራኤል ምሳሌ ናት ኤር.3፡1 ሆሴዕ 1፣3
2. በሐዲስ ኪዳን፡- ሙሽራው የክርስቶስ ሙሽሪት የቤተክርስትያን ምሳሌ ናቸው። ኤፌ.25፡33
3. በሌላ ትርጓሜ ሙሽራይቱ የእመቤታችን ምሳሌ ሆና በቅዱስ ያሬድ ተዘምሮላታል።

መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን አከፋፈሉ በአራት ክፍሎች ይከፈላል

1. ሙሽሪቱ ለሙሽራው በቅርብ የምታደርገው ንግግር
2. ሙሽሪት ለሙሽራው በሩቅ የምታደርው ንግግር
3. ሙሽራ ለሙሽሪት በቅርብ የሚያደርገው ንግግር
4. በሙሽራውና በሙሽሪት መካከል ያለው ጥያቄና መልስ

መኃልየመኃልየ ዘሰሎሞን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕ. 5፡32 በሙሽሪትና ሙሽራ መካከል መስሎ በክርስቶስና በቤተክርስትያን መካከል ያለውን አንድነት በምሳሌ እየገለጸ መኃልየመኃልየ ዘሰሎሞን በእስራኤልና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ፍቅር በሙሽሪትና በሙሽራው መስሎ ይገለፃል።

7. መጽሐፈ ጥበብ

ይህ መጽሐፍ በጠቢቡ ሰሎሞን የተፃፈ ሲሆን ትርጉሙ በቁሙ ሲፈታ እውቀትን፤ ብልሀትን፤ ፈሊጥን፤ ሕክምናን፤ ምክር ማለት ነው። አጻጻፉ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ከ 900 ዓ.ዓ አካባቢ እንደተጻፈ ይገመታል።

አጠቃላይ ይዘቱ፡- መንፈሳዊ ምክር ስለመናፍቂያንና አይሁዳውያን ይገልፃል እንዲሁም ስለ ጥበብ ጥቅም በመምከር ሰው ጥበብን እንዲፈልግ ይመክራል።

የመጽሐፉ አከፋፈሉ

መጽሐፈ ጥበብ 19 ምዕራፎች ሲኖሩት በ 3 ክፍሎች ይከፈላል።

ከምዕራፍ 1-6 ስለ ነገስታትና ስለክርስቶስ
ከምዕራፍ 7-15 ስለ ሰው ተፈጥሮና /ጣኦት/አምልኮ
ከምዕራፍ 16-19 ስለ ግብፃውያንና ስለ እየሩሳሌም ይናገራል።

8. መጽሐፈ ሲራክ

የስሙን ትርጉም ስንመለከት ሲራክ ማለት ጸሐፊ ማለት ነው። የመጽሐፉ ጸሐፊ እያሱ ወልደ አልአዛር ወልደ ሲራክ ይባላል። የተፃፈበት ዘመን በ 80 ዓ.ዓ.ቅ.ል.ክ. ነው ተብሎ ይገመታል። መጽሐፉ የተፃፈው ጸሐፊው እግዚአብሔርን መንፈሳዊና ስጋዊ ጥበብን ለምኖ ተገልያለት የፃፈው ነው።

አጠቃላይ ይዘቱ ደግሞ ለመንፈሳዊና ስጋዊ ሕይወታችን ጥበብና ምክር የሚሰጥ ነው። አከፋፈሉም በ 5 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ከምዕራፍ 1-10 ስለጥበብና ፈሪሃ እግዚአብሔር ቤተሰባዊ ኑሮ ስለዝምታና ትእግስት ይገልፃል።
ከምዕራፍ 11-20 ስለ ፍርድ ስለ ምጽዋት ስለ ስነ ፍጥረት ይናገራል።
ከምዕራፍ 21-30 ስለ ንስሐ ንጽሕና ስለ ብልህ ሰውና ስለ አምስቱ አእማደ ሚስጥር
ከምዕራፍ 31-41 ስለ መባና ገንዘብ ስለ ምክር ስነ-ምግባርና ሃይማኖት
ከምዕራፍ 42-51 ስለ ታጢያተኞች ስለ ስነ-ፍጥረት ይናገራል።
ይህመጽሐፍመጽሐፈ ሲራክ በመጀመሪያ በዕብራይስጥ ተጽፎ በኋላ በለጅ ልጁ ወደ ግሪክ ተተርጉሟል።

4.4 የነቢያትመጽሐፍትክፍል

ውድ ተማሪዎች አርባ ስድስቱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በአራት አበይት ክፍሎች እንደሚከፈሉ በምዕራፍ አራት ላይ ተመልክተናል። በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ክፍል የነብያት መጽሐፍት ክፍል ይባላል። ከዚህ በታች እንደሚከተለው ከትርጉሙ ጀምሮ አስራ ስድስቱን የነብያት መጽሐፍትን እንመለከታለን።

ነቢይ፡- ማለት ቃልን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለሕዝብ የሚናገር ማለት ነው። ነቢይ ፣የእግዚአብሔር ሰው (ሳሙ 7÷ 6) ባለ ራዕይ (ሳሙ 9÷9) የእግዚአብሔር ባሪያ (2 ነገ 24 ÷ 2) ተብሎ ይጠራል።

ነቢያት ትንቢት በሚናገሩበት ጊዜ ቃሉ ከእግዚአብሔር እንደመጣ ቢረዱም እንዴት እንደመረጣቸው አይገልጡትም ነበር። ብቻ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል›› እያሉ ትንቢቱን ይናገሩ ነበር። (አሞፅ 1 ÷ 3) ቃሉ አንዳንድ ጊዜ በራዕይ፣ በሕልም፣ በመልአክም ይገለጥላቸው ነበር። (ዳን 10 ÷ 11) (ዘት 12÷6)

የነብያት ቃል ስለ ሁለት የተያያዙ ነገሮች የሚያስገንዝብ ነው።ይኸውም፡-

1 ኛ. በእግዚአብሔር ውሳኔ ስለሚፈፀሙ ድርጊቶች ስለመንግስታት፣ ስለሰዎች፣ ስለኃጢያት

2 ኛ. ወደፊት ስለሚሆኑ ድርጊቶች እንዲሁም ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በምሳሌ (ኢሳ 5÷1-7) ወይም በድርጊት ይገልጡ ነበር።

ከ 16 የነቢያት መጽሐፍት ውስጥ ታላላቅ (አበይት) ነቢያት የሚባሉት (ኢሳይያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤልና ዳንኤል) ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ደቂቀ ነቢያት በመባል ይታወቃሉ። ነቢያት ትንቢትን የተናገሩት ከምርኮ በፊት፣ በምርኮ ጊዜ እና ከምርኮ በኋላ ሲሆን የነቢያት መጽሐፍት የተጠራቀሙበት ጊዜ ከ **250-300** ዓመታት ውስጥ ነው። የሚከተሉት ነብያት በሶስቱ ዘመናት ትንቢትን ተናገረዋል።

- "ኢሳይያስ, ኢዮኤል, ሚኪያስ"ኢየሩሳሌም በጥንት በባቢሎን ከመማረኳ በፊት በደቡብ ግዛት ኖረዋል።
- "ኤርሚያስ, እንባቆም, ሶፎኒያስና ዳንኤል"በወረራው ወይንም በምርኮው ወቅት የነበሩ ናቸው።
- "ሐጌ, ዘካርያስና, ሚልኪያስ"ከምርኮ በኃላ በ 538 ይኖሩ ነበር።
- "ዮናስና አሞፅ" ወደ እስራኤል (ወደ ሰሜኑ መንግስት) ተልከዋል። ይህ ግዛት በ 722 ምዕተ ዓመት በሶርያውያን ተወሮ ነበር። "ዮናስና ናሆም" በአሶር ዋና ከተማ ለነነዌ ትንቢት ተናግረዋል።
- "ሕዝቅኤል ይሁዳ በባቢሎን በተወረረች ጊዜ
- "አብድዩ" ደግሞ የእስራኤል የጥንት ጠላት በነበረችው በኤድምያስ ላይ ትንቢት ተናግሯል።

እነዚህ ነቢያት ለተጠሩበት አገልግሎት ሕይወታቸዉን እስከ ሞት ድረስ አሳልፈው ሰጥተዋል። በአጠቃላይ የነቢያቱን መጽሐፍት እንደሚከተለዉ በዝርዝር እንመለከተዋለን።

1. ትንቢተ ኢሳይያስ

ኢሳይያስ፦ማለት <<እግዚአብሔር አዳኝ ነዉ።>>ማለትነው። ነቢዩ ኢሳይያስ በአራቱ የይሁዳ ነገስታት ማለትም በኦዝያን፣ በኢዮአትም፣ በአካአዝና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግስትከ 740-688 ዓ.ዓ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረ ነቢይ ነዉ። ነብዩ ኢሳይያስ በአካአዝ እና በሕዝቅያስዘመነ መንግስት የቤተ መንግስት አማካሪ በመሆን አገልግሏል።አባቱ አሞፅ ይባላል። ይህም ከነቢዩ አሞፅ ሌላ ነው። 2 ነገ 19 ÷ 1 -2

ኢሳይያስ ባለ ትዳር ነቢይ ሲሆን ሚስቱም እንደሱ ነብይት ነበረች። ሁለት ልጆችም ነበሯቸው። የልጆቹም ስም አንደኛው ማሔር ቫላል ሲባል ሌላው ሼያር ያሼር ይባላሉ። ኢሳይያስ የታወቀ ምሁር ሲሆን ትንቢቱንም የተናገረዉ በኢየሩሳሌም ሆኖ ነዉ። መጽሐፉም በዕብራይስጥ ቋንቋ የተፃፈ ከአብይት ነቢያት በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚቀመጥ መጽሐፍ ነዉ። ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ የንጉሱ የሕዝቅያስን ልጅ ምናሴን << ከዚህ ፅኑ የሆነ የጣኦት አምልኮ ውጣ ከፋውን ግብር ሁሉ ተዉ>> በማለቱ በመጋዝ ተሰንጥቆት በሰማዕትነት እንዳረፈ ይነገራል።

መጽሐፈ ኢሳይያስ ከጥንት ጀምሮ 700 ክ.ዘ በነበረዉ ነቢይ በኢሳይያስ የተጻፈ መሆኑን ታምኖበታል። ባለፉት ሁለት መቶ ዓመታት ከተነሱት ዘመናዊያን ሊቃውንት ግን ልዩ ልዩ ሀሳቦች ተገኝቷል። እነርሱም እንደሚሉት ከምዕራፍ 1 -39 በራሱ በኢሳይያስ ተጽፏል። ከምዕራፍ 40--55 በባቢሎን ምርኮ በነበረ በሌላ ነብይ፣ ከምዕራፍ 56-66 ደግሞ ከምርኮ በኋላ በነበረ በሌላ ነብይ ተጽፏል የሚሉ አሉ። ለእነዚህም ሰዎች ሙሉመጽሐፉ በኢሳይያስ እንደተጻፈ ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ተሰጥተዋል።

1ኛ. አንድ ነቢይ በዘመኑ ለሚኖሩ ሰዎች ስለሚናገር ከዘመኑ በኋላ በባቢሎን ምርኮኞች ለሆኑት የጻፈ አይመስልም የሚሉት ሀሳብ አለ። ነገር ግን በነቢያት የሚናገረው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስራ በዚህ አይነት ሀሳብ የሚወሰን አይደለም።

2ኛ ከምዕራፍ 1 -39 እና ከምዕራፍ 40 – 66 መካከል የአጻጻፍና ሌላ ልዩነት ስለሚታይ ነው።ይህን ለሚሉት የትንቢተ ኢሳይያስ መልዕክት በየክፍሉ ስለሚመጣዉ መሲህ ጠለቅ ያለና አንድ አይነት ሀሳብ አለዉ። ሌላዉ ከሌሎች ነቢያት ይልቅ ኢሳይያስ << የእስራኤል ቅዱስ>> በሚል አጠራር ስለ እግዚአብሔር ይናገራል። (ኢሳ 1 – 14፣ 37 ÷ 23፣41 ÷ 16፣ 60 ÷ 14) ሌላዉ ደግሞ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በብዛት በመጽሐፍቶቻቸዉ ላይ መጥቀሳቸውና ስሙም ከ 21 ጊዜ በላይ መወሳቱ ነው። ኢሳ 40÷3፣ ማቴ 3÷3፣ ኢሳ

41÷1፣ ማቴ 12÷17 በማነፃፀር ይመልከቱ። የኢሳይያስ መጽሐፍ በአጠቃላይ 66 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የነቢዩ ዋና መልዕክት ‹‹የእስራኤል ቅዱስ በዓለም ላይ ነግሶ በአመፀኞች ላይ በመፍረድ የሚያምኑበትን የሚያድን ኃይል መሆኑን ማሳየት ነዉ።››

የትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ አከፋፈል

66 ምዕራፍ ያሉት የኢሳይያስ መጽሐፍ በሦስት ክፍል ከፍሎ መመለከት ይቻላል።

- ከምዕራፍ 1-39 በኢሳይያስ ዘመን በሆኑት ድርጊቶች ምክንያት የተፃፈ ነዉ። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ዓመጸኛ በሆነው ሕዝብናበሌሎችም ላይ ፍርድ እንደሚፀቀር ሲገልጥ የመንግስቱን ክብርና በረከት ያሳያል።
- ከምዕራፍ 40–55 ከኢሳይያስ ዘመን በኋላ በሆነው በባቢሎን ምርኮ ምክንያት ተጽፏል።በዚህ ክፍል እግዚአብሔር አዳኝ ነውና ሕዝቡን ወደ አገራቸዉ እንደሚያመጣቸዉ ሲገለጥ ከዚህ የበለጠዉን ማዳን ለዓለም ሁሉ እንደሚያደርስ ያሳያል።
- ከምዕራፍ 56–66 የጽዮንን ዘላለማዊ ክብር ያሳየናል። በዚህ ክፍል ክፋትን የሚመርጡት እንደሚጠፉ እግዚአብሔርም የእርሱ በሆኑት እንደሚደሰት ይናገራል።

የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ሊቃዉንት ዘንድ እንደ ትንቢቱ ይዘት ደረቅሐዲስ ወይም ትንቢቱ ትርጓሜ የማያስፈልገዉ ግለፅ በማለት ይገልጹታል።በሌሎች እህት አብያተ ክርስትያናት ሊቃዉንት ዘንድ ወንጌላዊ ነብይ ተብሎ ይጠራል።

2. ትንቢተ ኤርምያስ

ኤርምያስ፦ማለት “እግዚአብሔር ከፍያደርጋል ማለት ነዉ”። ከእስራኤል ከታላላቅ ነቢያት መካከል አንዱ ነዉ። በአባቱ በኢዮሲያስ ዘመነመንግስት የህግ መጽሐፍትንያገኘው ካህኑ ኬልቂያስእንደሆነ ብዙ ሊቃዉንት ይስማማሉ። የትዉልድ ቦታዉም ከእየሩሳሌም ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል የምትርቅ በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ የምትገኝ ከተማ ነች። ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ ለነብይነት የተመረጠ ነበር። ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም ጭምር ነብይ እንዲሆን በተጠራ ጊዜ ደነገጠ። ‹‹ብላቴና ነኝ›› ለማለት አመነታ። ኤር 1 ÷ 6 የተጠራዉም 626 ዓ.ዓ የይሁዳ ንጉስ ኢዮሲያስ በነገሰ በ 13 ኛዉ ዓመት ነበር።

ለነብይነት ከተጠራ ከ 40 ዓመት በኋላ የኢየሩሳሌምን መማረክ አየ። ህይወቱ በመከራ የተሞላ ስለነበረ የመከራ፣ የለቅሶና የሰቆቃ ነቢይ በመባል ይታወቃል። ነቢዩ ኤርምያስ አገልግሎት በጀመረበት ዘመን የንገሱ የይሁዳ ነገስታት 5 ሲሆኑ እርሱም “ኢዮሲያስ፣ ኢዮአክስ፣ ኢዮአቄም፣ ዮአኪንና ሴደቂያስ” ነበሩ። በእነዚህ ነገስታት ዘመን በነቢይነት አገልግሏል።ኤር 11 ÷ 1 2 ኛነገ 22 የዚህ የትንቢት መጽሐፍ ጸሐፊ ነቢዩ ኤርሚያስ ነው። ኤር 30 ÷ 1–2 በመጽሐፍ ሐዲት ውስጥ ባሮክ ተሳትፏል። የኢዮሲያስ ልጅ ኢዮአቄም በነገሰ በ 4 ኛዉ ዓመት እግዚአብሔር ለኤርምያስ ‹‹ከኢዮሲያስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የተናገርኩትን ቃል ሁሉ በክርታስ /በብራና/ ጻፍ›› አለዉ። ኤር 36÷1–3 ኤርምያስም ከእግዚአብሔር የመጣለትን ቃል ሁሉ እየነገረዉ ባሮክ ይጽፍለት ነበር። ኤር 36÷4 ባሮክም ኤርምያስ በአዘዘዉ መሰረት በጾም ቀን በእግዚአብሔር ቤት ለሕዝቡ ሁሉ አነበበ። የትንቢቱ መጽሐፍ በመሳፍንቱ ዘንድ ሲሰማ ንጉሱ ቀርቦእየቀደደ አቃጠለዉ። ኤር 36÷23 ዳግመኛ ሌላ ክርታስ ወስዶ የቀደመውን ቃል እንዲጽፍ እግዚአብሔር ኤርምያስን አዘዘው።

የትንቢተ ኤርምያስ ዋናዉ መልዕክት እግዚአብሔር ታላቅና ቅዱስ ስለሆነ ህዝቡ ከክፋት ተመልሰዉበፍጹም ልብ ያለ ሐሰት እርሱን እንዲያመልኩት ማስገንዘብ ነዉ። በትንቢተ ኤርምያስ የተገለፀዉ የትንቢቱ ቃል ብቻ ሳይሆን ስለ እራሱ ስለ ኤርምያስ ስለደረሰበትም መከራ ብዙ ነገር ስለተጻፈ ከሌሎች ነቢያት ይልቅ ጸባዩን እና ሁኔታዉን ይገልፃል።

ነብዩ ኤርምያስ ምንም ኢየሩሳሌምንና ህዝቡን ቢወድም ኤር 8 ÷18 9÷ 1 መማረክቸዉ እንደማይቀር 70 ዘመን ለባቢሎን ንጉስ ተላልፈው እንደሚሰጡ እግዚአብሐር የገለጠለትን ቃል ስለተናገረ ተጠላ። ብዙዎቹ ሊገድሉት አሰቡ። ኤር 11÷21 38÷6 ተመታ፣ በእግር ብረት ተያዘ፣ በጭቃ ጉድጓድ ተጣለ፣ ታሰረ፣ ኤር 20 ÷2 አብዷል ተባለ ኤር 29÷26። ከዚህ ሁሉ ጋር ለህዝቡ ምልክት እንዲሆን ሚስት እንዳያገባ ወደ ግብዣ ወይም ወደ ለቅሶ እንዳይሐድ ተከለከለ ኤር 16÷1 ነብዩ ኤርምያስ ኢየሩሳሌም በተወረወረችና በተደመሰሰችበት ጊዜ ከሕዝቡ ጋር ወደ ባቢሎን ተማርኮ በመሄድ ህዝቡን በማፅናናት በባቢሎን ቆይቷል። ለወገኖቹ ሲያለቅስ እያዳፉ አወጡት ከሕዝቡ ጋር እስከ ባቢሎን ድረስ ወሰዱት። ‹‹ተብሎ በተረፈ ኤርምያስ 8÷21 ተጠሷል። ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ግን የኢየሩሳሎም ጥፋት እንዳያዩ እግዚአብሐር 66 ዓመት እንዲተኙ አደረገ። ተረፈ ኤርሚያስ 9 ÷ 1 ›› 70 ዘመን በተጠናቀቀ ጊዜ በኢየሩሳሌም በፍቃደ እግዚአብሐርከምርኮዉ ተሰዉረዉ የቀሩ የነበሩ አቤሜሌክ እና ባሮክበንስር አማካኝነት የተላከ ደብዳቤ ከወገኖቹ አንዱ ሞቶ ለቀብር እንደተሰበሰቡ ኤርምያስ የግዞት ዘመን እንዳበቃ አነበበላቸዉ። ህዝቡንም ከአህዛብ ጋር በጋብቻ የተቀላቀሉትም እንዲለዩ ነገራቸዉ። እየመራቸውም እስከ ኢየሩሳሌም አድርሷቸዋል። ተረፈ ኤረ 11 ÷ 1-36 ከምርኮ ከተመለሱ ወገኖቹ አይሁድን ስለ ልባቸው ክፋትና ስለ ህግ መተላለፋቸዉ ይወቅሳቸው ስለነበር በድንጋይ ወግረው ገደሉት።

የትንቢተ ኤርምያስ መጽሐፍ አከፋፈል።

መጽሐፉ 52 ምዕራፎች አሉት። አከፋፈሉም እንደሚከተለው ነው፡-

ምዕራፍ 1 የነብዩ ከማኅጸን ጀምሮ መመረጥ

ከምዕራፍ 2-20 የእስራኤል ህዝቦች ወደ እግዚአብሐር እንዲመለሱ ነቢዩ ያደረገው ጥሪናየማስጠንቀቂያ መልዕክቶችይገኛሉ።

ከምዕራፍ 21-29 የይሁዳ ንጉስ የነበረው ዮአኪም ወደ ባቢሎን ከተማረከ በኋላ ኤርምያስ ለነገስታት፣ ለህዝቡ ለምርኮኞቹ ያስተላለፈው መልእክት ይዞ ይገኛል።

ከምዕራፍ 30-33 ነብዩኤርምያስ ስለ ሐዲስ ኪዳንና የወንጌል ህግ መምጣት የተናገረበት ሲሆን በተጨማሪም ስለ ኢየሩሳሌም አዲስ ተስፋ የተናገረበት ነዉ፡

ከምዕራፍ 34-39 የኢየሩሳሌም መከበብ እና ዉድቀት

ከምዕራፍ 40-42 ከምርኮ ከተረፉት አይሁድ ጋራ ኤርምያስ በይሁዳ መቅረቱን ይገልፃል።

ከምዕራፍ 43-44 የነብዩ ኤርምያስ የግብፅ ስደት ኑሮና በዚያ ያከናወናቸው አገልግሎቶችን ያትታል።

ከምዕራፍ 45-51 ነብዩ በህዝብ ላይ የተናገራቸው ትንቢቶች ይገኛሉ።

ምዕራፍ 52 በዘመኑ ስለ ተፈፀመዉ የእስራኤል ዉድቀት ጥፋትና የሕዝቧ ስደት እንዴት እንደነበረ ይናገራል።

2.1 ሰቆቃዉ ኤርሚያስ

ሰቆቃ፡- ማለት ሙሾ ለቅሶ ማለት ነዉ። ምንም እንኳን በመጽሐፉ የነብዩ የኤርምያስ ስም ባይገለፅም በሊቃዉንተ ቤተ ክርስቲያን እንደታመነበት የመጽሐፉ ፀሐፊ ነብዩ ኤርምያስ ነዉ። መጽሐፉ ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ አወዳደቋን፣ አጥሮቿን የቤተ መቅደሷን መፍረስን የንብረቷና የህዝቧ መማረክን መነሻ በማድረግ ነብዩ ኤርምያስ ያቀረበዉን ሰቆቃ (የኃዘን እጉርጉሮ) ይዞ ይገኛል።አምስት ምዕራፎች አምስት የሐዘን ሙሾዎች ናቸዉ። በምዕራፍ 1፣2፣4 እያንዳንዱ ቁጥር የሚጀምረዉ በሃያ ሁለቱ የእብራስጥ ፊደላት ሲሆን ፊደሎቹም ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀዋል።

ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ ስትወድቅ እናቶች ልጆቻቸዉን እስከ መብላት ያደረሰዉ አስከፊ ረሀብ፣ የካህናትና የነብያት መገደል እንዲሁም ነብዩ እራሱ በምርኮ የደረሰበትን ችግር በዝርዝር ይዟል። ስለ እግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት፣ ማዳኑን ተስፋ ስለማድረግና ስለምህረቱም ጭምር የተገለጠበት መጽሐፍ ነዉ።

የመጽሐፉ አከፋፈል፡-

- ምዕራፍ 1 የኢየሩሳሌም መከራና ሀዘን
- ምዕራፍ 2 እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ ያመጣዉ ቅጣት
- ምዕራፍ 3 የቅጣት አይነት፣ ንስሐ እና የተሰጠዉ ተስፋ
- ምዕራፍ 4-5 ኢየሩሳሌም ከውድቀት በኃላ እና ምህረት ለማግኘት የቀረበ ጸሎት

2.2 ተረፈ ኤርምያስ

ተረፈ ኤርምያስ ከሰቆቃው ኤርምያስ ምዕራፍ ስድስት ብሎ የሚጀምር ስድስት ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው። በተረፈ ኤርምያስ 11÷63 እንደተገለፀው ፀሐፊው ባሮክ ነው። መጽሐፉ ስለ ጣኦት አምልኮ ከንቱነት በስፋት ስለሚያትት <<አርአያ ኤርሚያስ>> ተብሎ ይጠራል።መጽሐፉ እግዚአብሔር ለባሮክ፣ ለአቤሚሊክና ለኤርምያስ ገልጣላቸዋል። እስራኤላውያን በባቢሎን በምርኮ በነበሩበት ዘመን እንዴት ጠብቆ እንዳሳለፋቸው በኤርምያስ መሪነት ምርኮኞቹ ወደ እየሩሳሌም እንዴት እንደተመለሱ እንዲሁም አምልኮ ጣኦት ከንቱ ስለሆኑ የሚተርክ መጽሐፍ ነው።

2.3 መጽሐፈ ባሮክ

ባሮክ ማለት <<ብሩክ>> ማለት ነው። ባሮክ የነብዩ የኤርምያስ ታማኝ ወዳጅና ጸሐፊም ነበር። ባሮክ በነብዩ ኤርምያስ ትዕዛዝ እግዚአብሔር ለነብዩ ኤርምያስ የተናገረውን ቃል በመጽሐፉ ክፍል ኤር 36÷1-32 ኤርምያስ በንጉስ ሴዴቂያስ ዘመን በታሰረ ጊዜ ባሮክ የንጉሱን ቁጣ ሳይፈራ ነብዩን ይረዳው ነበር። ኤር 32÷ 12-16 ነብዩ ኤርምያስ ከጥቂት አይሁዶች ጋራ ወደ ግብጽ እንዲጓዝ በተገደደ ጊዜ አብሮት ሄዷል። ኤር 43 ÷ 1- 7

መጽሐፉን የፃፈው የኤርምያስ ደቀ መዝሙር ባሮክ ቢሆንም በይዘቱ እና እግዚአብሔር ለኤርምያስ የገለጠለት በመሆኑ መጽሐፉን ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር በመደመር አንድ ሆኖ ይቆጠራል። መጽሐፉም ባሮክ ባቢሎን በምርኮ በነበረበት ጊዜ ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ፅፎ የላከላቸው ነው። መጽሐፉም አምስት ምዕራፎች አሉት።

የመጽሐፉ አከፋፈል፡-

- በምርኮ ስላሉት አይሁድ ኑሮ
- የኃጢያት ኑዛዜ
- ንስሐና ፀሎት
- ለአይሁድ የቀረቡ ልዩ ልዩ ምክሮች ይገኙበታል።

ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ቀኖና ቅዱሳት አቆጣጠር መሰረት ሰቆቃ ኤርምያስ፣ ተረፈ ኤርምያስ እና መጽሐፈ ባሮክ ከትንብተ ኤርምያስ ጋር እንደ አንድ ይቆጠራሉ።

3. ትንቢተ ሕዝቅኤል

ሕዝቅኤል፡- የቃሉ ትርጉም እግዚአብሔር ብርታትን ይሰጣል ማለት ነው። ነገዱ ከሌዊ ወገን ሲሆን ትውልዱም ከአሮን ወገን ነው።አባቱ ቡኤዝ ይባላል። የነበረበትም ጊዜ በ593 ዓ. ዓ አካበቢ ነበር። ከልጅነቱ ጀምሮ የነብዩ ኤርምያስ ደቀ መዝሙር እንደነበረ ይነገራል። በ597 ቅ.ል.ክ በኢኮኒያን (ዮአኪን) በተማረከ ጊዜ ነብዩ ሕዝቅኤልም አብሮ ተማርኳል። ሕዝ 1÷ 1-3 ካህን ሆኖ ከእነ አልአዛር እግር ተተክቶ እስራኤልን ያገለግል ነበር።በምርኮ አገር ከሌሎች እስራኤላውያን ጋር ኮቦር ከተባለው ወንዝ አጠገብ ይኖር ነበር። የአገልግሎት ዘመኑም ከ 20 – 22 ዓመታት ለነብይነት የተጠራው በሰላሳ ዓመት ዕድሜው እግዚአብሔርን በኪሩቤል ላይ እንዳለ በራዕይ አየ ለተማረኩት ለእስራኤል ሕዝብ ቃሉን እንዲናገር ተጠራ። ሕዝ 2÷ 1-4 ሕዝቅኤልና ዳንኤል ይተዋወቁ ነበር።ሕዝ 14÷14 በባቢሎን ምርኮ ሳለ በምርኮኝነት ለነበሩ እስራኤላዊያን ትንቢት ተናግሯል። ሕዝ 29÷17 የሕዝቅኤል የአገልግሎት ዘመን በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ልንከፍለው እንችላለን።

1ኛ ኢየሩሳሌም በ587 ከክ.ል.በፊት በጠላት እጅ ከመውደቋ በፊት አስቀድሞ በባቢሎን ምርኮኞች መካከል የፈፀመው የስብከት አገልግሎት ምዕ 4÷24

2ኛ ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ ከወደቀች በኃላ በባቢሎን የፈፀመው የስብከት አገልግሎት። ምዕ 33-48 ሕዝቅኤል በባቢሎን ለ20 ዓመታት እያስተማረ ቆይቶ እዚያው በምርኮ እያለ በሰማዕትነት ያረፈ ታላቅ ነቢይ ነው።

በአጠቃላይ መጽሐፉ የሚያስተምረን ትምህርት አይሁድ በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸውን ታማኝነት በማጉደላቸውጣአታትን በማምለካቸው እና የተላኩትን ነቢያት እምቢ በማለታቸው ስለተፈረደባቸው ፍርድ መጽሐፉ ያስተምረናል። ሕዝ 14 ÷ 21 ሌላው ሰው በስራው ልክ ዋጋዉን እንደሚያገኝ እንጂ አንዱ በሌላው ኃጢአት ምክንያት እንደማይቀጣ መግለፁ። ሕዝ 18÷20 እግዚአብሔር ሰዎችን ከኃጢያታቸው ተመልሰው እንዲድኑ እንጂ በኃጢያታቸው እንዲሞቱ የማይፈቅድ መሐሪ አምላክ መሆኑን በግልፅ ይናገራል። ሕዝ 18 ÷ 23፣ ስለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝ 1 ÷ 26፣ ስለ እመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና ሕዝ 44 ÷ 1 -2፣ ጥምቀት የሚያነፃ ስለ መሆኑ ሕዝ 36 ÷ 25፣ ስለ ቁርባንና ትንሳኤ ሙታን በምሳሌ ተናገሯል። ሕዝ 2÷8

የመጽሐፉ አከፋፈል

መጽሐፉ 48 ምዕራፎች አሉት

- ከምዕራፍ 1-24 ከኢየሩሳሌም ውድቀት በፊት የተነገሩ ትንቢቶች
- ከምዕራፍ 25-32 ከኢየሩሳሌም ውጪ ባሉ ሕዝቦች ላይ የተነገሩትን ትንቢቶች
- ከምዕራፍ 33–39 የናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ከወረረ በኋላ የተነገሩ ከምርኮ መመለስን ተስፋ የሚያበስሩ ትንቢቶች

- ከምዕራፍ 40–48 ስለ አዲሱ ቤተ-መቅደስ (ስለ ሐዲስ ኪዳን ቤተ-መቅደስ) ስለ መንግስተ ሰማያት የተገለጠ ራዕይ

4. ትንቢተ ዳንኤል

ዳንኤል፡- ማለት እግዚአብሔር ፈራጅ ነው (ዳኛ ነው) ማለት ነው። ዳንኤል በዘመነ ኢዮሲያስ በምድረ ይሁዳ ተወልዷል። ትወልዱም ከነገደ ይሁዳ ሲሆን ቤተሰበቹ ከንጉሳያዊን ወገን ነበሩ። ዳን 1 ÷ 3 606 ከክርስቶስ ልደት በፊት በናቡከደነፆር ተማርኮ ወደ ባቢሎን የተጓዘ ይሁዳዊ ነው። ዳንኤል ጠቢብና አስተዋይ ለቤተ መንግስትም ተልዕኮ ብቁ የሆነ የሃይማኖቱን ስርዓት የሚጠብቅ ሰው ነበር። በባቢሎን ሳለ የነቢይነቱን ከአስተዳዳሪነት ጋር አስተባብሮ ይሄዳል። ዳንኤል በስደት የከልዳዉያንንምትምህርትና ቋንቋ ተማረ። ዳን 1 ÷ 1- 6 ዳንኤል ሕልም የመፍታት ጸጋ የተሰጠው በጾምና በጸሎትም የሚተጋ ሰው ነበር። የአገልግሎት ዘመኑም ከ 606–536 ቅ.ል.ክ ሲሆን በዘመኑ የነበሩ አራቱ የአሕዛብ ነገስታትን አሳልፏል። እነርሱም ናቡከደነፆር፣ ብልጣሶር፣ ዳርዮስና፣ ቂሮስ ናቸው።እርሱም እነዚህን ነገስታት በማስተማር ሕልምን በመፍታት ጽሑፉን በመተርጎም አገልግሏል። ዳንኤል ምንም እንኳን የአሕዛብ የመንግስት ባለሥልጣን ቢሆንም ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ሕዝቡ በአምልኮተ እግዚአብሔር እንዲጸና ያደረገ ነቢይ ነው። ትንቢተ ዳንኤል በዕብራይስጥ በአረማይክ ቋንቋዎች እንደተጻፈ ይነገራል። ምክንያቱም በነበረበት ዘመን የአረማይክና የፋርስ ቋንቋ የበላይነት ይዞ ስለነበረ ነው።

ትንቢተ ዳንኤል ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ዳንኤልና ሠልስቱ ደቂቅ (አናንያ አዛርያ ሚሳኤል) በሃይማኖታቸው በስርዓታቸው በመጸናት በባዕድ ሀገር ለእግዚአብሔር ታማኝ ስለሆኑ መከራ ቢደርስባቸውም እግዚአብሔር የዚህን ዓለም መንግስታትን እንደሚቆጣጠርና የራሱ መንግስት ደግሞ ዘላለማዊ መሆኑ የሚያመላክት ነው።

የመጽሐፉ አከፋፈል

ከምዕራፍ 1-2 የዳንኤል ወደ ባቢሎን መማረክና መሾም እና ዳንኤል አንደኛውን የናቡከደነፆርን ህልም መተርጎሙ

ምዕራፍ 3 ሲድራቅ ሚሳቅ አብነጎር በእሳት እቶን መጣላቸውና መዳናቸው

ከምዕራፍ 4-5 የዳንኤል ሁለተኛውን የናቡከደነፆር ሕልም መተርጎምና የሕልሙ ፍጻሜ እንዲሁም የዳንኤል በግድግዳ ላይ ስለ ብልጣሶር የተፃፈውን መተረጎምና የቃሉ ፍፃሜ

ምዕራፍ 6 የዳንኤል ዳርዮስን እያገለገለ በአንበሳ ጉድጓድ መጣሉንና መዳኑን

ምዕራፍ 7 አራቱ መንግስታት በአራዊት ስለመመሰላቸው ግዛትና መንግስትን የሰው ልጅ ለሚመስል (ለክርስቶስ) መስጠቱ

ምዕራፍ 8 ዳንኤል ያየው ራዕይ ግሪክ ፋርስን ማሸነፉን በመጨረሻም ቤተ መቅደስ ያረከሰ አንጥርያኮስ ይጠፋል ማለቱ።

ምዕራፍ 9 ዳንኤል ከምርኮ መመለስ ስለመጸለዩና መሲህ እስኪመጣ ሰባ ሱባኤ እንደሚያልፍ ትንቢት መናገሩ

ምዕራፍ 10-12 ከታላቁ እስክንድር በኃላ በሶሪያና በግብፅ መንግስታት መካከል ስለሚደረገው ጦርነት ስለ እግዚአብሔርም ህዝብ መከራ ትንቢት መናገሩ።

4.1 የሶስቱ ደቂቅ መዝሙር

የሠልስቱ ደቂቅ መዝሙር ማለት የሦስቱ ልጆች ምስጋና ማለት ነው። እነዚህ ሦስቱ ሕጻናት አናንያ አዛርያ ሚሳኤል የተባሉ ከወላጆቻቸዉ ጋር ወደ ባቢሎን በግዞት ከተወሰዱ በኃላ የጃንደረቦች አለቃ ስማቸውን ቀይሮ ሲድራቅ አብደናንር፣ ሚሳቅ፣ ብሏቸዋል። ሕዝቦቻቸው በምርኮ እያሉ እነርሱ ምቾትን አልመረጡም ከንጉሱ የታዘዘላቸው ምግብና መጠጥ እምቢ ብለው ጥራጥሬ ብቻ ይመገቡና ዘወትርም ይጸልዩ ነበር። በዚያም ንጉስ ናቡከደነጾር ለሰራው ምስል (ጣኦት) እንዲሰግዱ ሲያስገድዳቸው ጊዜ እምቢ በማለት ጸኑ። ንጉሱም እሳት ውስጥም እንዲጣሉ አዘ ተጣሉ። እግዚአብሔርም መላእኩን ልኮ ከእሳት መቃጠል አዳናቸው። እነርሱም በእሳት ውስጥ እያሉ ያመሰገኑት ምስጋና የሰለስቱ ደቂቅ መዝሙር ተብሎ ይጠራል። ይህም መዝሙር በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 3 ላይ በ 68 ቁጥሮች ተቀምጧል።

4.2 መጽሐፈ ሶስና

ሶስና፡- ሹሻና የምትባል ሲሆን ትርጉሙም የአበባ አይነት ማለት ነው። ሶስና የካህኑ የኬልቂያስ ልጅ ነበረች። ካህኑ የኬልቂያስ የእግዚአብሔርን የሕግ መጽሐፍ ከጠፋበት ያገኘው እርሱ ስለነበረ ለልጃቸውም ሙሴ የጻፋቸውን ሕግጋት አስተምረዋታልና። ነቢዩ ኤርምያስም ወንድሟ ነው። ሶስና መልከ መልካም እግዚአብሔርን የምትፈራ ነበረች። ከነቢዩ ዳንኤል ጋር በፋርስ በስደት በምትኖርበት ጊዜ ሁለት መምህራን አይሁድ (ረበናት) የዝሙት ጥያቄ ሲያቀርቡላት ሕገ እግዚአብሔርን በማክበር ፍቃዳቸውን አልፈጽምም በማለቷይባስ ብለው በእርሳ ላይ በሐሰት በዝሙት ወንጀል እንድትከሰስ እና የሞት ፍርድ እንዲፈረድባት አደረጉ። የሞት ፍርድም በድንጋይ ተወግራ ትሙት የሚል ነበር ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሀዘኗን፣ጸሎቷን ተመልክቶ ነብዩ ዳንኤልን ላከላት። መጽሐፉ ነብዩ ዳንኤል የእግዚአብሔርን ጥበብ የተሞላ ስለሆነ ከሞት ፍርድ እንዴት እንዳዳናት ይገልፃል። መጽሐፉ በአንድ ምዕራፍ የተጠቃለለ ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ሲሆን በግእዙ የብራና መጽሐፍ ላይየትንቢተ ዳንኤል መግቢያ ሆኖ ተቀምጧል። ይህንንም ከጲላጦስ ዘርም የተባሉት ሊቅ በዳንኤል የወጣትነት ዘመን የተፈፀመ ድርጊት በመሆኑም በመጀመሪያውምዕራፍ ላይ መፃፍ ተገቢ ነው። በማለት ይገልጸዋል።

4.3 ተረፈ ዳንኤል

ይህ መጽሐፍ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 6 ከቁጥር 4 – 24 ድረስ ያለውን ቃል በስፋትና በጥልቅት የሚተነትን የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ባለ አንድ ምዕራፍ ሲሆን ሁለት አበይት ታሪኮች የያዘ ነው። የመጀመሪያ ንጉስ ቂሮስ መንግስቱን መያዙና ህዝቡ ያመልኩት የነበረውን ቤል የተባለ ጣኦት ደካማነት ነብዩ ዳንኤል ለንጉሱ ያሳየበት የባቢሎን ሕዝብ ለአምልኮታቸው ቀናተኛ በመሆናቸው በእነሱ ጫና ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ እንዲጣል መደረጉ ሲሆን ሁለተኛው ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ ቢጣልም አናብስት ሳይበሉት መቅረታቸው ለሰባት ቀናት በአናብስት ጉድጓድ ሲቆይ የእግዚአብሔር መልአክ ነብዩ ዕንባቆምን ከይሁዳ ወደ ባቢሎን ምግብ አሲዞ እንደላከውና ዳንኤል አመስግኖ መመገቡን ይገልጻል። በአዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ 14 ኛ ምዕራፍ ሆኖ ታትሟል።

ውድ ተማሪዎች መዝሙር ሠለሰቱ ደቂቅ፣ መጽሐፈ ሶስና እና ተረፈ ዳንኤል እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር መሰረት ከትንቢተ ዳንኤል ጋር እንደ አንድ ይቆጠራሉ።

5. ትንቢተ ሆሴዕ

ሆሴዕ የስሙ ትርጉም እግዚአብሔር ያድናል ማለት ነው። የመለኮታዊ ፍቅር መገለጫ ነቢይም ይባላል። በትውልዱ እስራኤላዊ ነው። አባቱ ብኤሪ ይባላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሆሴዕ በሚለው ስም ከነቢዩ ከሆስዕ ሌላ ከሰሜናዊ የእስራኤል ነገስታት (ሰማሪያ) በመጨረሻ የነገሰው ንጉስ ተጠርቶበት ነበር። 2 ኛ ነገ 15 ÷ 30 የነበረበት ዘመን ከ 755 – 725 ሲሆን መልዕክቱ ያዝያን፣ ህዝቅያን፣ ዳግማዊ እዮርአብአምና አክአዝ ዘመን አገልግሎቱ ጎልቶ ይታያል። በጊዜው የነበረው ንጉስ የእምነቱ ሁኔታ በጣም የተበላሸ ስለነበር ማለትም የእስራኤል ነገዶች በሁለት መንግስታት ከተከፋፈሉ በኃላ በ 731 -722 በተለይም እስራኤል በአሦር እጅ ከወደቀች በኃላ የይሁዳና

የእስራኤል ሕዝቦች ስለሆኑ ሆሴዕ በትንቢቱ ስለ ሁለቱ ይናገራል። ሆሴ 2 ÷ 1 ስለ ሰሜናው መንግስት ውድቀት ትንቢት ተናግሮ ነበር። የሆሴዕ የትንቢት መጽሐፍ ዋና መልዕክት የእግዚአብሔርን ፍቅር መግለጽ ነው። በዚያን ዘመን አሞጽ፣ ኢሳይያስ፣ ሚኪያስ ትንቢት ይናገሩ ነበር። ስለ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መምጣት ወደ ግብጽ ስለሚሰደዱና ስለ መመለሱ ስለ ሞቱና ትንሳኤው በምስጢር ተናግራል። ሆሴ 6 ÷ 1 -3 , 11 ÷ 1 – 2

የመጽሐፉ አከፋፈል

ትንቢተ ሆሴዕ 14 ምዕራፎች አሉት። አከፋፈሉን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

- ✓ ከምዕራፍ 1-3 የሆሴዕ ሚስት የጉሜር ማመንዘር ለእስራኤላዊያን አመንዝራነት ጣኦት አምላኪነት ምሳሌ ሆነች። ሆሴዕሚስቱን ወዶ በፍቅር እንዲመልሳት ታዘ ነበር። እግዚአብሔር እስራኤላውያን በፅድቅና በምሕረት በገዛ ፍቃድ እንደወደደ ምሳሌ ነው።
- ✓ ከምዕራፍ 4-13 እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱ ከፍርድና ከውድቀት እንደሚያመልጡ።
- ✓ ምዕራፍ 14 ወደ እግዚአብሔር በመመለስ የሚገኝ ፈውስና በረከት እስራኤላውያን መልሶ ሚቋቋም በውስጡ ይዟል።

6. ትንቢተ አሞፅ

አሞፅ ማለት ሸክም ወይምጭነት ማለት ነው። ይህ ስም ከትንቢቱ ሁኔታ ጋር ይገጥማል። 1ኛ ነገ 17÷2-20 በእግዚአብሔርከመጠራቱ በፊት ላም ጠባቂ የዋርካ ፍሬ ለቃሚ ነበር። ሀገሩ ቴቁሔ የምትባል ከቤተልሔም አስር ኪ.ሜ ያህል እርቃ የምትገኝ ሀገር ናት። የተነበየው ግን በይሁዳ ሳይሆን በእስራኤል መንግስት ውስጥ ነው። አሞፅ 1÷7 7÷14 በዳግማዊ እዮርብአም ዘመነ መንግስት (783-764 ዓ.ዓ ከክ.ል.በ) ሲያገለግል ነበር። በዘመኑ የነበሩ የእስራኤል ህዝቦች ሁኔታ ፈፅሞ የወደቀ በፀፀት የተሞላና በተለይም ካህናት እና ነቢያት ለገንዘብ የሚሰሩ ነበሩ። አሞፅ በምኞትና በግደለሽነት የሚኖሩትን የሰማርያን ሰዎች ግፍንና የጣኦትን አምልኮ ትተዉ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ጽድቁንም እንዲሹ ተናግሯል። ነገር ግን ቢያስጠነቅቃቸውም እንኳን የሰሙት በጣም ጥቂቶች ነበሩ። ምንም እንኳን ባይሰሙትም እስራኤል እንደምትማረክ ተነበየ። ካህኑ አሜሲያስ አሞፅን ተቃዉሞ በንጉስ ፊት ክስ ካቀረበበት በኋላ የሰሜኑ መንግስት ይበቃል። የአሞፅ ትንቢት በአብዛኛዎቹ የፍርድ ቃል ናቸው። ፍፃሜ ዘመን ላይ ግን ለእስራኤልም ሆነ ለአሕዛብ የደኅንነትና የሰላም ጊዜ እንደሚመጣ በመጽሐፉ በመጨረሻ ተናግሯል። ያዕቆብም ፍፃሜውን አይቶ ጠቅሶታል። አሞፅ 9÷11-15 የሐዋ.ሥራ 15÷14-18

የመጽሐፉ አከፋፈል 9 ምዕራፎች አሉት

1. ምዕራፍ 1 ÷ 1 – 2 ፍርድ በእስራኤል ጎረቤት ሀገሮች
2. ምዕራፍ 2 ÷ 6 ፍርድ በእስራኤል
3. ምዕራፍ 3 ÷ 1 – 16 ፍርድ በእስራኤል ኃጢያት ምክንያት
4. ምዕራፍ 9 ÷ 11 በፍፃሜው ዘመን ስላለው የእስራኤል ተስፋ

7. ትንቢተ ሚክያስ

ሚክያስ ማለት የስሙ ትርጉም እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው ማለት ነው። የይምላ ልጅ፣ በአክዓብ ዘመን መንግስት በሰማርያ ትንቢት ይናገር ነበር። ሚክያስ በኢዮአታምና በአካዝ በሕዝቂያስም ዘመን በይሁዳ ነቢይ ነበር። ሚክ 1÷1 የአክአብን ሞት የተነበየ እሱ ነበረ። 1ነገ 22÷8 ፣ 13-28 ሚክያስ ትንቢት መናገር የጀመረው ከሰማርያ ውድቀት በፊት ማለትም ከ 722 ከክ.ል.በ ነበር። በዘመኑ ነቢዩ

አሞፅና ሆሴዕ በሰሜኑ መንግስት ከኢሳይያስ ጋር በኢየሩሳሌም ነበሩ። ለሕዝቂያስ የተናገረው ትንቢት በጊዜው ኤርሚያስን ከሞት አድኖታል። ኤር 26÷16 የእግዚአብሔር ፍርድ በሰማርያና በኢየሩሳሌም እንደሚሆን በኋላ ግን መልሶ እንደሚሰበስባቸው ተናገረ። የይሁዳ ግዛት በሆነችው በቤተልሔም ከእመቤታችን ንጉሰ ነገስት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወለድ ተንብዮ ነበር።ሚክ 5÷2-5 አዛብ ደግሞ እግዚአብሔርን ይፈልጋሉ ይህም የሚፈፀመው በክርስቶስ ነው። ሚክ 4÷2 ፣ 7÷16

የመጽሐፉ አከፋፈል

ትንቢተ ሚክያስ 7 ምዕራፎች አሉት

ከምዕራፍ 1-3 የሰማርያና የኢየሩሳሌም መፍረስ

ምዕራፍ 4 የእግዚአብሔር መንግስት መመስረት

ምዕራፍ 5 ከቤተልሔም የሚወጣው ገዢ እና እረኛ

ምዕራፍ 6 እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ያደረገው ክርክር

ምዕራፍ 7 ተግሳፅ እና ተስፋ

8. ትንቢተ ኢዮኤል

ኢዮኤል፦ ማለት እግዚአብሔር አምላክ ነው ማለት ነው። አባቱ ባቱኤል የሚባል እስራኤላዊ ነብይ ነበር። ያገለግል የነበረው በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም ሲሆን የትንቢቱን መጽሐፍ መቼ እንደፃፈው ዘመኑን በውል ማረጋገጥ አልተቻለም። ትንቢቱም በኢየሩሳሌም እንደተናገረው ይገመታል።ጊዜው አስፈሪ እና አንበጣ የበዛበት ወቅት ስለነበር አንበጣዎቹ ሰራዊቱ አድርጎ በእየሩሳሌም ላይ ይህን ታላቅና ብርቱ ህዝብ የመራ እግዚአብሔር ነው ይላል። ኢዩ 1÷2-27 ከኢዩኤል ትንቢት በጣም የሚታወቀው ክፍል እግዚአብሔር በመጨረሻው ክ/ዘመን በስጋ ለባሹ ሁሉ ላይ መንፈሱን ለማፍሰስ የሰጠውን ተስፋ ነው። ኢዮ 2÷28-30

የመጽሐፉ አከፋፈል ትንቢተ ኢዮኤል 3 ምዕራፎች አሉት።

ምዕራፍ 1 በእስራኤል ኃጢያት ምክንያት በምድሪቱ የሚበቅሉ የእህል ዓይነቶች በሙሉ በመቅሰፍት እንደሚመቱ

ምዕራፍ 2 ንስሐ ለሚገቡ እግዚአብሔር ከማያልቀው በረከቱ ህዝቡን እንደሚጎበኝና በኋለኛው ዘመን /በበዓለ ሃምሳ/ የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ለሁሉ እንደሚታደል የሐዋ.ሥራ 2÷1

ምዕራፍ 3 እግዚአብሔርን ለማያውቁ እና በኃጢያት ለበረቱ ፅኑ ፍርድ እንደሚጠበቃቸው ያትታል።

9. ትንቢተ አብድዩ

አብድዩ ማለትየጌታ አገልጋይ (ታማኝ)ማለት ነው። ይህ ነብይ እግዚአብሔርን የሚፈራ የአክአብ የግቢ አዛዥ ነበር። ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ባስገደለችበት ጊዜ 100 ውን ነቢያት ወስዶ ወደ ዋሻ በመሸሸግ ከሞት አድኗቸዋል። የሚበሉትን እህልና የሚጠጡትን ውሃ እየሰጠ ይመግባቸው ነበር። 1 ነገ 18÷15-19 ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዶኃኒትነትም በምስጢር ተናግሯል።

አብድዩ በኤዶሚያስ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ተንብዮ ነበር። ኤዶማውያን የሚባሉ የኤሳው ዘሮች ሲሆኑ ከጥንት ጀምሮ በያዕቆብ ዘሮች ላይ በእስራኤል ላይ በጠላትነት ይነሱባቸው ነበር። ዘፍ 25÷23 አሞፅ 1÷11 የሚኖሩትም ከሙት ባህር በስተ ደቡብ ተከላማ አካባቢ ነው። ዋና ከተማቸውም ሴልፔትራ የምትገኘው በአንድ ትልቅ ቋጥኝ ላይ ስለሆነ ወደ እርሷ የሚደርሰው መንገድ በጣም ጠባብ ሸለቆ ነው። ከዚህም የተነሳ ብቸኛ ጎረቤት የሌላት ከተማ ናት። አብድዩ በትዕቢታቸውና በትምክህታቸው ፈርዶባቸዋል። በኋላ ላይም እንደሚጠፉተናግሯል።

የትንቢተ አብድዩ አከፋፈል

መጽሐፉ አንድ ምዕራፍ ብቻ አለው።

1. የመጨረሻ ፍርድ በኤዶም ላይ ከቁጥር 1 – 9
2. የኤዶሚያስ ቂምና ጭከናከቁጥር 10 – 14
3. የእግዚአብሔር ፍርድ በኤዶሚያስና በአሕዛብ ላይ ከቁጥር 15 – 21

10. ትንቢተ ዮናስ

ዮናስ ማለት ርግብ የዋህ ማለት ነው። በዳግማዊ ኢዮርብአም ዘመነ መንግስት የነበረ ነቢይ ነው። የዮናስ መኖሪያ በገሊላ በጋት ሐፌር ከተማ ነበር። አባቱም አማቴ ይባል ነበር። በአይሁዳውያን ልማድ እንደሚጠቀሰው 1 ነገ 17÷17 ላይ በሰራፕታ ነቢዩ ኤልያስን ትመግበው የነበረችው መበለቲቱ ልጇ ሞቶ ነብዩ ኤልያስ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ አስነስቶታል።ነብዩ ኤልያስ ከሞት ያስነሳው ልጅ ነብዩ ዮናስ ነው። ምንም የእስራኤል ነብይ ቢሆንም የአስተማረው ግን ከእስራኤል ውጪ በበደላቸው ሊቀጡ የነበሩትን የነነዌ ሰዎችን ነው። የነነዌ ሰዎች በበደላቸውም ምክንያት ከሚመጣባቸው ቅጣት እንዲድኑ እግዚአብሔር ዮናስን አስተምሮ ቢለው “አንተ መሐሪ ነህና ብትምራቸው እኔ ሐሰተኛ ነብይ እባላለሁ።” በማለት ለመሸሽ ቢሞክርም ሶስት ቀንና ሶስት ለሊት በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ አድሯል። በእግዚአብሔር ቸርነት ከአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ወጥቶ ህዝቡን አስተምህሮ በንስሓ እንዲመለሱ አድርጓል። ክርስቶስም የዮናስን ከአሳ ነባሪ ሆድ መውጣት የራሱ ትንሳኤ ምሳሌ አድርጎታል። ማቴ 12 ÷ 39

የመጽሐፉ አከፋፈል 4 ምዕራፎች አሉት።

ምዕራፍ 1 የዮናስ መኮብለልና መገታቱ

ምዕራፍ 2 የዮናስ ጸሎት እና መመለስ

ምዕራፍ 3 በዮናስ ስብከት ከንጉሱ እስከ ህዝቡ በንስሐ መመለስ

ምዕራፍ 4 ስለዮናስ ቁጣና የእግዚአብሔር መልስ

11. ትንቢተ ናሆም

ናሆም ማለት የስሙ ትርጉም “መፅናናት” ማለት ነው። ስለ ነነዌ ጥፋት ራዕይ ያየና ለይሁዳ የምስራች የተናገረ ነቢይ ነው። ይኖርባት የነበረችው ከተማ ስም ከይሁዳ ከተሞች አንዷ በሆነችው ኤልቆሽ በምትባል ቦታ ነበር። ናሆም ትንቢቱን የተናገረው ከክ.ል.በ 663 እና ነነዌ እስከወደቀችበት 662 መካከል ነበር። ነነዌ በዮናስ ዘመን ከክፋቷ ተመልሳ ንስሐ የገባች ብትሆንም ውሎ አድሮ ግን ከጭካኔዋና ከስህተቷ ብዛት ግን ፍርድ የማይቀርላት ሆናለች። 3፣ 1-7

የመጽሐፉ አከፋፈል 3 ምዕራፎች አሉት።

ምዕራፍ 1 እግዚአብሔር የፍርድና የበቀል አምላክ ነው።

ምዕራፍ 2 የነነዌ ጥፋት

ምዕራፍ 3 የነነዌ ጥፋት ምክንያትን ያትታል።

12. ትንቢተ ዕንባቆም

ዕንባቆም ማለት ማቀፍ፣ እቅፍ ማለት ነው። እግዚአብሔር በፀሎት አቅፎታልና። ዕንባቆም ያለገባ ድንግል ነቢይ እንደሆነ ይነገራል። የቤተ መቅደሱ ዘማሪ እንደሆነም ሊቋውንቱ ይመሰክራሉ። ዕንባ 3÷1 እንዲሁም ከሌዊ ወገን የነበረ ካህን ነው። በሌላ ታሪክ ውስጥ ከሀገሩ ተነጥሎ ወደ ባቢሎን በመሄድ ነቢዩ ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ ተጥሎ በነበረበት ወቅት በእግዚአብሔር መልአክ እርዳታ ከነቢዩ ዕንባቆም ጋር እንደተገናኙ ተረፈ ዳንኤል ይናገራል። ዕንባቆም ነብዩ ኤርሚያስ ነብዩ ዳንኤል በነበሩበት ዘመን የነበረ ነው። ትንቢቱም የተናገረበት ዘመን ከ 609 – 606 ከክ.ል.በ ሲሆን በመጀመሪያው የእዩአቄም ዘመነ መንግስት ነበር። መጽሐፉ የአይሁድ ሕዝብ በኃጢያታቸው ስለሚደርስባቸው መከራ ከለዳዉያን በሚገዟቸው ሕዝቦች በአደረሱት ግፍ የሚደርስባቸው ቅጣትና ነብዩ የጸለየውን ጸሎት የያዘ ነው።

የመጽሐፉ አከፋፈል 3 ምዕራፎች አሉት።

ምዕራፍ 1 እግዚአብሔር በግፈኞች ላይ ለምን አይፈርድም ስለሚለው እና ስለከለዳውያን(ቁ 1-11)

ጥያቄ እንዴት እነርሱ ከእኛ የባሱ አይደሉምን? ከም 1 ከቁ. 12 – 17

ምዕራፍ 2 መልስ በተራቸው ከፎዎች ሁሉ ይፈረድባቸዋል። ጻድቅ ግን እግዚአብሔርን አምኖ ይድናል።

ምዕራፍ 3 የዕንባቆም ፀሎትና መዝሙር

13. ትንቢተ ሶፎንያስ

ሶፎንያስ ማለት እግዚአብሔር ሰውሯል ወይም ጠብቋል ማለት ነው። አባቱ ኩሲ ይባል ነበር። በምዕራፍ 3 የተጠቀሰው ሕዝቅያስቅድመ አያቱ ነው። ይህም ስለነበረ በኢዮሲያስ ዘመነ መንግስት ነቢዩ ኤርሚያስ ይኖር በነበረበት ዘመን ከ 640–609 ከክ.ል.በ በኢየሩሳሌም ይኖር የነበረ ነብይ ነው። ኢዮሲያስ መንገስ በጀመረ ጊዜ ኢየሩሳሌም ከምናሴና ከአሞንከፋት የተነሳ በኃጢያት ተሞልታ ነበር።ሶፎ 1÷4–6 ሶፎንያስ በይሁዳ ላይ ብቻ ሳይሆን በምድር ሁሉ ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ትንቢት ተናገረ።ሶፎ 1÷2 ፤ 14–18 እግዚአብሔርን ለሚፈልጉት ትሁታን ግን ተስፋ ሰጣቸው። ሶፎ 2÷3 በመጨረሻም እግዚአብሔር ከምድር ሁሉ እንደሚሰበስባቸው እና ስለ አድሲቱ ኢየሩሳሌም ደስታ ተነበየ። ሶፎ 3÷9

የመጽሐፉ አከፋፈል

ትንቢተ ሶፎንያስ ሶስት ምዕራፎችን በውስጡ ይዟል።

1. በሁሉም ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ም 1÷2 –3
2. በልዩ ልዩ ህዝቦች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ም 2÷4–15
3. በአይሁድ ስለሚመጣው ፍርድ ም 3÷1 –18
4. የእስራኤል መሰባሰብና በረከት ም 3÷19–20

14. ትንቢተ ሐጌ

ሐጌ ማለት የእኔ ደስታ ማለት ነው። የተወለደው በባቢሎን በምርኮ ወቅት ሲሆን ከምርኮ መልስ በሀገረ እስራኤል ለአገልግሎት የተነሳ ነብይ ነው። በ 520 ከክ.ል.በ በኢየሩሳሌም ለነበሩት አይሁድ ትንቢት የተናገረ ነብይ ነው። ከምርኮው በኋላ ስላለው ጊዜ አይሁዶች ደግመው ወደ ሀገራቸው እንዴት ሊመለሱ እንደቻሉ ያሳያል። በስደት ምክንያት የገጠማቸውን የተዛባ ማህበራዊ ኑሮ ከነብዩ ዘካርያስ ጋር በማስተማር ያስተካከለ ነብይ ነው። ስለ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ እንደገና መታነፅ በመስበክ ሕዝቡን በትምህርቱ አትግቷል። ቤተ-መቅደሱን ለመስራት

ቢሞክሩም ከሳምራዉያን መቃወም የተነሳ ስራው ተቋረጠ ሳይፈፅሙትም 16 ዓመት ዘገየ። ምዕ 3 ÷ 4 ከዚህ በኋላ ሐጌ ስራውን እንዲፈፅሙት አነሳሳቸው።

የመጽሐፉ አከፋፈል ሁለት ምዕራፎች አሉት።

ምዕራፍ 1 ‹‹የእግዚአብሔር ቤት ለመስራት ተነሱ።›› የሚል ወቀሳ

ምዕራፍ 2 እግዚአብሔር ይባርካቸዋል የሚል ተስፋና ማበረታቻ፤ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይኖራል፤

እግዚአብሔር ዘሩባቤልን ከፍ ከፍ ያደርገዋል የሚሉትንቢቶች።

15. ትንቢተ ዘካርያስ

ዘካርያስ ማለት እግዚአብሔር ያስታዉሳል ማለት ሲሆን አባቱ ባራኪው ይባላል። እንደ ነብዩ ሐጌ በባቢሎን ተወልዷል። አባቱ በባቢሎን ስለሞተ ከአያቱ ጋርወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል። ነህ 12÷1 -7

በ 520 ከክ.ል.በ ከነብዩ ሐጌ ጋር ተነስቷል። የቤተ መቅደስን ስራ እንዲፈፅሙ አይሁድን ያነሳሳቸው ነብይ ነው። ሕዝ 5÷2 ዘካርያስ ነብይና ካህን ነበር። ከዚህ በፊት የነበሩት ነቢያት መልዕክት በአንድነት አጠቃሎ እና ወደ ፊት የሚሆነውን የሚመጣዉን በሩቅ ተናግሯል ጽፏል። ዘካርያስ አገልግሎቱን የጀመረው ከሐጌ ሁለት ወር ዘግይቶ ነው። ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት፣ በ 30 ብር መሸጡን፣ ህመማተ መስቀል መቀበሉን እና ደግም ምጽአቱን በትንቢት ተናግሯል። ዘካ 9÷9 11÷2 12÷10 13÷6 14÷4

የመጽሐፉ አከፋፈል 14 ምዕራፎች አሉት።

ምዕራፍ 1 ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ የሚል ጥሪ - ም 1÷1-6

በስምንት ራዕዮች የምድር ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር ጽዮንን ለመስራትና ለማነጽ ያለውን ሐሳብ ይገልጣል። ም 1÷76÷15

ከምዕራፍ 7-8 በኢየሩሳሌም መፍረስ ጊዜ የተደነገጉ የጾም ቀኖች ተለውጠው የደስታ በዓላት እንዲሆኑ የተሰጠ ትዕዛዝ

ምዕራፍ 9 እግዚአብሔር ለመፍረድም ሆነ ለማዳን ታላቅና ቅን ስለመሆኑ

ከምዕራፍ 10-13 ስለማይረቡ እረኞች (አለቆች) እና ስለ መልካም እረኞች

ምዕራፍ 14 እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ መንገሱን ይተርካል።

16. ትንቢተ ሚልክያስ

ሚልክያስ ማለት መልዕክተኛዬ ወይም የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ማለት ነው። መጽሐፉ ከ 470 – 430 ባለው ጊዜ ውስጥ ወይንም የኢየሩሳሌም የከተማ አስተዳዳሪ ከነበረው ከነህምያ ቀደም ብሎ እንደነበር ይናገራል። በሐጌ እናበዘካርያስ ወቅት አብረው ለቤተ መቅደሱ ስራ ህዝቡን ያስተባብሩ ነበር።

የትንቢተ ሚልክያስ አከፋፈል

ትንቢተ ሚልክያስ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ይከፈላል፡-

ከምዕራፍ 1-2 የአይሁድ ካህናት እና ህዝብ የተከለከለውን በማድረግ (ትርፍ በማግበስበሳቸውና የክህነት ተግባራቸውን

በማጓደላቸው) የደረሰባቸው ወቀሳ።

ከምዕራፍ 3-4 ስለ መጥመቁ ዮሐንስ መምጣት፣ አይሁድ የዐሥራት ክፍያ በማስታጎላቸው የነገራቸው የወቀሳ ቃል፤

ስለ ክርስቶስ መምጫ ቀን መቃረብና ምልክቱ የተነገሩ የትንቢት ቃላት ይገኙበታል።

መልመጃ አራት

1. ከአስራ ስድስቱ የነብያት መጽሐፍት መካከል የአብይት ነብያት መጽሐፍት ጥቀሱ
2. በመጽሐፈ አስቴር አንድም ቦታ የእግዚአብሔር ስም ያልተጠቀሰበት ምክንያት ምንድ ነው
3. አሪት ዘዳግም ----------፣ ---------- እና ---------- መጽሐፍት በድጋሚ የተጻፀበት መጽሐፍ ነው

ምዕራፍአምስት

የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ዝርዝር ጥናት

ውድ የርቀት ትምህርት ተማሪዎች በቀደመው ምዕራፍ በአራት የሚከፈሉትን አርባ ሰድስቱን/46 ቱን/ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በዝርዝር ለማጥናት ተሞክሯል። በዚህ ምዕራፍ ሰላሳ አምስቱን/35 ቱን/ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ጥናት በዝርዝር ለማጥናት እንሞክራለን። የእግዚአብሔር ቸርነቱ ይረዳን! አሜን!!!

5.1 የቃሉ ትርጉም

ሐዲስ ኪዳን፦ ማለት አዲስ ውል፣ አዲስ ስምምነት፣ አዲስ የመተማመኛ መሐላ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኪዳን የሚለው ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ ሰዎችም በእምነት የሚቀበሉት ውል ማለት ነው። ሐዲስ ኪዳን ስንል ደግሞ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ የድኅነት ውል ማለት ሲሆን ይኸውም በወልደ እግዚአብሔር በወልደ ማርያም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲያገኝ የሚያረጋግጥ ኪዳን ነው። (ማር 16፣16 ዮሐ 3፣36 ዮሐ 6፣47 ...)

የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት የሚባሉት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት(ወንጌል) እና ቅዱሳን ሐዋርያት የጻፏቸው መጽሐፍቶች ናቸው። ሐዲስ ኪዳን ሲባል ፊተኛ ወይም የቀደመ ኪዳን እንደነበረ ያስገነዝባል። ይህ ፊተኛ ኪዳን ብሉይ ኪዳን ተብሎ ይጠራል። የሐዲስ ኪዳን መመሥረት አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በትንቢት የተነገር ነበር።"እንሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል እግዚአብሔር" ትን ኤር 31፣31-34 (ዕብ 8፣6-13)

የሐዲስ ኪዳን የተመሠረተችው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። "...ይህ ጽዋ ስለ እናንት የሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው። "ሉቃ 22፣19-20 1ኛ ቆሮ 11፣ 23-26

እግዚአብሔር ዓለምን የሚያስተዳድረው በቃል ኪዳኑ ስርዓት ነው። ሰዎች ቃልኪዳኑን ተቀብለው ቢታዘዙለት የቃል ኪዳኑን በረከት ይቀበላሉ። ይህንን የቃልኪዳኑን በረከት ለማግኘት ከሰዎች የሚጠበቀው ነገር መታዘዝ ነው። በቃል ኪዳኑ ውስጥ ሰጪ፣ ተቀባይ፣ የአቀባበል ምልክት፣ ተስፋ እና የተስፋ ምልክት አለ።

- የሐዲስ ኪዳን ሲጪ - ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

- የሐዲስ ኪዳን ተቀባይ - በክርስቶስ የባሕሪ አምላክነት የሚያምኑ ክርስቲያኖች
- የሐዲስ ኪዳን ማኅተብ - ጥምቀት
- የሐዲስ ኪዳን ተስፋ - የዘላለም ህይወት / መንግስተ ሰማያት/
- የተስፋው ምልክት - ቅዱስ ቁርባን ነው።

የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት አከፋፈል በምዕራፍ አራት የተመለከትን ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ዝርዝር የሐዲስ ኪዳን ጥናትን እንመለከታለን።

5.2 የወንጌል መጽሐፍት

ወንጌል የሚለው ቃል ኢቫንጌልዮን ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም በግእዝ ብስራት በአማርኛ ምሥራች ማለት ነው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምርህት ወይም ዜና ሠናይ የያዘ ስም ወንጌል ተብሎ ይጠራል። ትምህርቱን ወንጌል ብሎ ለመጀመርያ ጊዜ የጠራው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ማር 1፣15 ማቴ 24፣14 ማቴ 26፣13 ማር 16፣15 ‹‹ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል።›› ማቴ 24፣14

ከዚህ የክርስቶስ ቃል በመነሳት ሐዋርያት ስለክርስቶስ የጻፉት እና ያስተማሩት ሁሉ ወንጌል ይባላል። (ሮሜ 1፣16 ማር 4፣23 ማር 9፣35 ወንጌል እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም እንደተገለጠ፣ ስለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል መከራ መቀበሉን፣ መራቡን፣መጠማቱን፣ መገረፉን፣ በማዕከለ ምድር በቀራንዮ መሰቀሉን፣ መሞቱን፣ መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ሞት ድል አድርጎ መነሳቱን፣ በይባቤ መላዕክት ወደ ሰማይ ማረጉን እንዲሁም ዳግም ዓለምን ለማሳለፍ መምጣቱን የምታስተምር ብርሃናዊት ህግ ናት። የእግዚአብሔርን ሰው መሆን እና የሰው ልጆችን ድኅነት ስለምታበስር ወንጌል ምስራች ትባላለች። በወንጌል የተገለጸ ድኅነት በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ ድኅነት በመሆኑ ያለን ወንጌል አንድ ወንጌል እንጂ የተለያየ ወንጌል አይደለም። ነገር ግን ወንጌላት ብለን በብዙ ቁጥር ስንጠራ በአራቱ ወንጌላዊያን የተጻፉት የወንጌል መጽሐፍት ማለታችን ነው።ሉቃ 1፣1-4

በወንጌል ስለ ክርስቶስ የተጻፈው ሙሉ በሙሉ ክርስቶስ የሰራው የማዳን ስራ ሳይሆን ከሰራው ስራ ጥቂቱን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው አራቱ ወንጌላዊያን ከልደቱ እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ ያለውን አቅማቸው እስከ ፈቀደ ጻፉት። ‹‹ጌታ ኢየሱስ ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ። ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጽሐፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ነበር።›› ዮሐ 21፣25 እንዳለ።

አራቱ ወንጌላዊያን ሁለቱ ከሐዋርያት ወገን ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ከአርድዕት ወገን ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ሐዋርያት ብቻ ጽፈውት ያልሆነስለምን ነው ቢሉ ስለክብረ አርድዕት ነው። አርድዕት ለማስተማር በወጡ ጊዜ አይሁድ እነዚህማ የወጪ /ተሪታ/ ሰዎች ናቸው በማለት ትምህርታቸውን ከመቀበል ይከለከሉ ነበር። አርድዕት ብቻ ያልጻፉት ስለምን ነው ቢሉ ስለክብረ ወንጌል ነው። አርድዕት ብቻ ጽፈውት ቢሆን ኖሮ ‹‹ ይህቺማ ተርታ ህግ ናት ደጊቱ ህግ ምሥጢር ተአምራትን በቤተ ኢያኤሮስ፣ ምሥጢር መንግስትን በደብረ ታቦር፣ ምሥጢር ምጽአትን በደብረ ዘይት፣ ምሥጢር ጸሎትን በጌቴሴማኒ በተመለከቱ አዕማደ ምድር /የምድር ምሶሶዎች/ በተባሉ በሐዋርያት ልብ ቀርታለች ብለው አይሁድ ወንጌልን ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና ሁለት ከሐዋርያት ሁለት ከአርድዕት ወገን ሆነው ጽፈውታል።

5.2.1 የወንጌል ጸሐፊዎች አራት የመሆናቸው ምስጢር

ውድ ተማሪዎች አራት ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ልዩ የሆነ ትርጉም አለው። በዚህ መሠረት የወንጌል ጻፊዎች አራት የሆኑበት ምስጢር እንደሚከተለው ቀርቧል፦

ሀ. በአራቱ እንስሳት ይመሰላል፦ የሥላሴ መንበር የሚሸከሙ አራቱ እንስሳት ማለት የአንበሳ፣ የላህም፣ የንስር እና የሰው ገጽ መልክ ባለቸው በአራቱ እንስሳት ይመሰላሉ።

- ቅዱስ ማቴዎስ በሰው ይመሰላል፦የዳዊት ልጅ ፣ የአብርሃም ልጅ እያለ የጌታን ምድራዊ ልደት በመጻፍ ሰለሚጀምር በሰው ይመሰላል።
- ቅዱስ ማርቆስ በአንበሳ ይመሰላል፦ አንበሳ ኦሮው በምድር በዳ ነው። ከዚህ ሆኖ አንድ ጊዜ ድምፁን ሲያሰማ እንሰሳት ይገሰጻሉ፣ አራዊት ይደነግጣሉ። ቅዱስ ማርቆስ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ተራቁታ ምድረ በዳ በሆነች በግብፅ ምድር ጣዕር ስብከቱን ሲያሰማ ምዕመናን ተገስጸዋል አጋንንት መናፈቃን ደንግጠዋል።አንድም አንበሳ ለላህም ጌታው ነው። ቅዱስ ማርቆስ በትምህርተ ወንጌል አምላኮተ ላህም ከግብፅ ምድር አጥፍቶዋል።
- ቅዱስ ሉቃስ በላህም ይመሰላል፦ ከሌሎች በተለየ መልኩ የጌታን በከብቶች በረት መወለድ ፤እንስሳት እስትንፋሳቸውን መገበራቸው ይጽፋል።
- ቅዱስ ዮሐንስ በንስር ይመሰላል፦ ንስር በእግሩ ይሸከረከራል በክንፉ ይበራል። በእግሩ እንደመሸከረከሩ እንደ ወንደሞቹ የጌታን ከሰማይ ሰማይት መውረዱን ከድንግል ማርያም መወለዱን ይጽፋል። በክንፍ እንደ መብረሩ ንጽሐ ሰጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቦና ተሰጥቶት የሥላሴን የአንድነት እና የሦስትነት የወልደ እግዚአብሔር በቅድምና መኖር ጽፏል።

ለ. በተጨማሪ በአራቱ አፈላጋት፣ በአራቱ ክዋክብት፣በአራቱ ወቅታት ወዘተ...ይመሰላሉ።

5.2.2 የአራቱ ወንጌላውያን ይዘት

ውድ ተማሪዎች አራቱ ወንጌላት ከይዘታቸው አንጻር ሲጠኑ በሁለት ይከፈላሉ። ይህ ማለት አንዳቸው ከሌላቸው የሚለዩበት የታሪክ፣ የትምህርት እና የተአምራት አመዘጋገብ ስላላቸው ነው። እነሱም፦

1. ሲኖፕቲክ ወንጌላት
2. አራተኛው ወንጌል

1 ሲኖፕቲክ ወንጌላት

ሲኖፕቲክ/synoptic/ ከግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ከአራቱ ወንጌላት መካከል ለሦስቱ ወንጌላት ማለት ለማቴዎስ፣ ለማርቆስ እና ለሉቃስ ወንጌል የተሰጠ ስያሜ ነው። ሲኖፕቲክ ማለት በአንድ የሚታዩ /seen together/ ማለት ነው። ሦስቱ ወንጌላት በይዘታቸው ሰለሚመሳሰሉ እና አንዱ ከአንዱ ማስተያየት ስለሚቻል የተሰጣቸው ስያሜ ነው።

2 አራተኛ ወንጌል

አራተኛው ወንጌል የተባለው የዮሐንስ ወንጌል ነው። በዚህ ወንጌል የተመዘገበ እንደ ሌሎቹ ወንጌላት የጌታን ታሪክ እና ትምህርት ቢሆንም በሦስቱ ወንጌላት ያልሰፈሩ የጌታችን ትምህርቶችን ይዞ ይገኛል።

ሦስቱ ወንጌላት፦ ሰለ ጌታ የምድር መዋዕለ ዘመን /የሰውነት ነገር/ አጉልተው ይጽፋሉ። /ማቴ 1፣1-17 ማር 8፣32 ሉቃ 3፣ 23-38/

አራተኛ ወንጌል ፦ የጌታን ከሰማይ መውረድ /መለኮትን ነገር/ አጉልቶ ይጽፋል። /ዮሐ 1፣1-3 3፣13፣6፣41-51 8፣23/

በዚህ ምክንያት ሦስቱ ወንጌላት ወንጌላተ ዘበምድር ***/Earthly Gospels/*** ሲባሉ አራተኛ ወንጌል ደግሞ ሰማያዊ ወንጌል ***/Heavenly Gospel/*** ይባላል።

ውድ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የርቀት ትምህርት ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል ሰላሳ አምስቱን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት በዝርዝር ወደ ማጥናት እንገባለን። የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት ምስጢሩን ይግለጥልን።

1. *የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል*

የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈው በሐዋርያው በቅዱስ ማቴዎስ ነው። በ 325 ዓ.ም በኒቂያ ጉባኤ የተሰበሰቡ 318 የቤ/ክ ሊቃውንት ለመጽሐፍ ቅዱስ ርዕስ፣ቁጥርና ምዕራፍ ሲሰጡ ‹‹ብስራተ ማቴዎስ ሐዋርያ አሐዱ እም ዐሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት... ›› በማለት የወንጌሉ ጸሐፊ ቅዱስ ማቴዎስ እንደሆነ አሰቀምጠዋል። ከሐዋርያት አበው መካከል የሆነው ፓፒዮስ /60-130 ዓ.ም/ ‹‹ማቴዎስ የጌታን ነገር በዕብራይስጥ ቋንቋ ጻፈ።›› በማለት የወንጌሉ ጸሐፊ ቅዱስ ማቴዎስ እንደሆነያስቀምጣል።

የስሙ ትርጓሜ እና መጠራቱ፡-ማቴዎስ ማለት የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው። ቅዱስ ማቴዎስ የቀድሞ ሰሙ ሌዊ ይባል ነበር። ቁጥሩ ከ 12 ሐዋርያት ወገን ነው። /ማቴ 9፣9-13 ማር 2፣13-17/ ማቴዎስ አባቱ ዲቁ እናቱ ከሩትያስ ይባላሉ። በማርቆስ ወንጌል ላይ የማቴዎስ አባት አልፍዮስ አንደሆነተመዝግቧል። /ማር 2፣14/

በእስራኤላዊያን ባህል በሁለት ስም መጠራት ልማድ ሰለሆነ የማቴዎስ አባት ዲቁ ሌላው ስሙ አልፍዮስ ይባላል። ቅዱስ ማቴዎስ ከነገደ ይሳኮር ወገን ሲሆን በገሊላ አውረጃ በምትገኘው በቅፍርናሆም ከተማ ተቀምጦ ለሮማዊያን/ ሄርድስ አንቲጳስ/ ቀረጥ ይሰበስብ ነበር። /ማቴ 1፣1 13/

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዚህች ከተማ በሄደ ጊዜ በመቅርጫው ተቀምጦ አገኘውና ተከተለኝ ብሎ ጠራው። ለጊዜው ጌታችንንበእግር ተከተለው፤ ፍጻሜው ግን በግብር መሰለው። ቅዱስ ማቴዎስ ገንዘቡን ሁሉ ለድሆች በማብላት ጌታችንን እና ደቀ-መዛሙርቱ በቤቱ ጠርቶ የቁም ተስካሩን ያወጣ ሐዋርያ ነው።

ያስተማረበት ሀገር

ቅዱስ ማቴዎስ በበዓለ ሃምሳ መንፈስ ቅዱስጸጋን ከተቀበለ በኃላ ወደ ሐዋርያዊ አገልግሎቱ ተሰማርቷል። በፍልስጤም/ለዕብራዊያን/፣ በፋርስ፣ በባቢሎንና በኢትዮጵያ ወንጌልን እንዳስተማረ የቤ/ክ የታሪክ ጽሐፊው አውሳቢዮስ ዘቂሳርያ እና ሩፊኖስ በመጽሐፍቶቻቸው አስቀምጠዋል። ጥንታዊ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሊቃውንት በምዕራብ ትግራይ በአድዋ አዋራጃ ውስጥ ናዕዴር በተባለ ቦታ እንዳስተማረ ይናገራሉ። /መዝ 71(72)፣40/ በመጨረሻም ጥቅምት 12 ቀን ብስባውሪ በምትባል ቦታ አንገቱን በሰይፍ ተቀልቶ በሰማዕትነት አርፏል። /ስንክሳር ጥቅምት 12/

የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበት ዘመን

የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበት ዘመን በተመለከተ እየሩሳሌም በ 70 ዓ.ም ከመጥፋቷ በፊት የተጻፈ መሆኑን አብዛኞቹ ሊቃውንት ይስማሙበታል። በግእዝ የመጽሐፍ ቅዱስትርጓሜ ላይ ጌታ ባረገ በ 8 ኛው ዓመት ተፈጽሞ የ 9 ኛው ዓመት ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሳር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት እንደሆነ ይነገራል። ይህም በ 41 ዓ.ም ማለት ነው። በአንዳንድ መጽሐፍት ከቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ቀጥሎ በ 58 ዓ.ም እንደተጻፈ ይገለጻል።

ወንጌሉ የተጻፈበት ቦታ፣ ቋንቋ እና የተጻፈላቸው ሰዎች

ቅዱስ ማቴዎስ በምድር ፍልስጤም ከአይሁድ እምነት ወደ ክርስትና ለተመለሱ አይሁዳዊያን/ዕብራዊያን/ ጽፎላቸዋል። ትምህርቱን አስተምሮ ወደ ሌላ ቦታ ለማስተማር በሚሄድበት ጊዜ አባታችን በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል እና ጻፍልን ብለውት ጽፎላቸዋል። ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌሉንስለጻፈበት ቋንቋ ሶስት አይነት አስትምህሮች አሉ፦

ሀ. በዕብራይስጥ፦ የቤ/ክ ሊቃውንትን ጨምሮ አብዛኞቹ ምሑራን የሚስማሙበት ወንጌሉን በዕብራይስጥ ቋንቋ እንደጻፈው ነው። ነገር ግን የዕበራይስጥ ቅጂ እስከ አሁን ድርስ አልተገኝም።

ለ. አረመይክ፦ የአረማይክ ቋንቋ በመጀመራያ መቶ/ክ/ዘመን በፍልስጤማዊያን የሚነገር ቋንቋ ሲሆን ጌታም ያስተማረው በዚህ ቋንቋ ነበር። ይህንን ተከትሎ ወንጌሉ በአረማይክ ቋንቋ ጽፎታል ይላሉ። ፓፒዮስ የተባለ የቤ/ክ አባት በ2ኛ መ/ክ/ዘ እንደአስቀመጠው ሎጂያ ተብሎ በሚጠራው ስብስብ ውስጥ የጌታችን ታሪክ ትምህርት እና ታምራት እንደተመዘገብ ይተርካል። በዚህም ወንጌሉ በአረማይክ ቋንቋ ጽፎታል ይላሉ።

ሐ. በግሪክ፦ አብዛኞቹ የማቴዎስ ወንጌል ቅጅዎች በግሪክ ቋንቋ ይገኛሉ ይህንም በመያዝ ወንጌሉ በግሪክ ቋንቋ ጽፎታል ይላሉ።

የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብርሃም እና ከዳዊት ዘር የተወለደ ፍጽም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ለማጠይቅ። የሰው ልጅ፣ የዳዊት ልጅ እያለ ጌታ እራሱ የተናገራቸውን ይጠቅሳል። /1፣1-17 9፣6 16፣1317፣12.../

2. አይሁድ ጌታን ከነብያት አንዱ ነው ይሉት ነበርና ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን ለማስረዳት። /3፣17 8፣29 11፣25-27..../

3.በሕግና ነብያትስለመሲሁ የተናገሩት ስለጌታ መሆኑን ለማስተማር ጽፎላቸዋል።/ 1፣22-23 2፣4 16፣ 11-25 12፣17-21.../

የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል 28 ምዕራፎች እና 1061 ቁጥሮችን በውስጡ የያዘ ወንጌል ነው። ከ1061 ቁጥሮች ውስጥ 644 የጌታ ትምህርቶችንይዟል። በዚህ ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ሲዛመድ ከሉቃስ እና ከማርቆስ ወንጌል ጋር ይለያል።የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ከ150 በላይ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ይጠቅሳል።

ውድ ተማሪዎች በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ላይ ከ*150* በላይ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መጠቀሱ ወንጌሉ ትንቢት ለተነገረላቸው ሱባኤ ለተቆጠረላችሁ ለአይሁዳዊያን መጻፉን ያሳያል።

የወንጌሉ አከፋፈል

የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል 28 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ይከፈላል፦

ከምዕራፍ 1-4 - የጌታችንመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የትውልድ ሐረጉን፣ልደቱን፣ስደቱን ጥምቀቱን እና በዲያቢሎስ መፈተኑን

ከምዕራፍ 5-7 - የተራራው ስብከት

ከምዕራፍ 8-12 - የኃይል ስራው /ተአምራቱ/፣ 12 ደቀ-መዛሙርቱን መምረጡ፣የሠጣቸውን ስልጣን እና ትዕዛዝ ይዟል።

ከምዕራፍ 13-20 - በደብረ ታቦር የጌታችን ክብር መገለጡ፣ ሐዋርያትን ማስተማሩ

ከምዕራፍ 21-27 - ወደ እየሩሳሌም በክብር መግባቱ፣ ስለ ዳግም ምጽአቱ ማስተማሩ፣ ከአይሁድ መጣላቱ ሕማሙ፣ስቀለቱ ና ሞቱ

ከምዕራፍ 28 - ስለ ጌታችን ትንሳኤና መገለጥ ያትታል።

2. የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል

የማርቆስ ወንጌል የተጻፈው በቅዱስ ማርቆስ ነው። የቤ/ክ የታሪክ ጸሐፊው አውሳቢዮስ ዘቂሳርያ /339/ የቤ/ክ ታሪክ በሚለው መጽሐፉ ላይ ቅዱስ ማርቆስ እንደ ጻፈው ይናገራል። /መጽሐፈ ስንክሳር ሚያዝያ 30/

የሰሙ ትርጉም፡-ቅዱስ ማርቆስ ሁለት ሰሞች እንዳሉት ቅዱሳት መጽሐፍት ይናገራሉ። ዮሐንስ ና ማርቆስ። ዮሐንስ አይሁዳዊ ስሙ /ዮሐ 12፣12-25 13፣5-13/ ሲሆን ማርቆስ ደግሞ የሮማዊ ስሙ ነው።ማርቆስ /የሐዋ 15፣19 2 ጢሞ 4፣11 1 ጴጥ 5፣13/ ማርቆስ ማለት ታላቅ መዶሻ ወይም ካህን ማለት(ልዑክ) ማለት ሲሆን ዮሐንስ ማለት ፍስሃ ወይም ደስታ ማለት ነው።

የቅዱስ ማርቆስ ቤተሰቡ፡- የማርቆስ እናቱ ማርያም ከ 36 ቱ ቅድሳት አንስት መካከል የምትቀጠር ናት። ቤቷን ለሐዋርያት መሰብሰቢያ፣ ጸሎት ማድርጊያ፣ ስርዓት መሠራያ ሰለሰጠች ቤ/ክ ተብሎ ተጠረቷል። /የሐዋ 12፣5/ ጌታም የመጨረሻውን እራት የበላው በማርቆስ እናት ቤት ነው። /የሐዋ 1፣26/ ቅዱስ ማርቆስ በልጅነቱ በእየሩሳሌም ውስጥ የተፈጹምት ድርጊቶች ያወቃል አብሮ ነበርና። /ማር 14፣51-52/ ጌታ በተያዘ ጊዜ እርቃኑ የሸሸው እሱ ነበር።

ወንጌል ያሰተማረበት ሀገር

ቅዱስ አውሳቢዮስ ዘቂሳርያ ማርቆስ በሮም ውንጌልን እንደሰበከና ወደ እስክንድርያ ሄዶ እንዳስተማር የመጀመርያ የእስክንድርያ ጳጳስ እንደሆነ ጽፏል። አንዳንድ ሊቃውንት በአፍሪካ ሀገራት ተዘዋውሮ እንዳስተማረ ይገልጻሉ።

ውንጌሉ የተጻፈበት ቦታ፣ ቋንቋ እና ዘመን

ውንጌሉን ለሮማዊያ ሮም ላይ ሆኖ በሮማይስጥ/ላቲን/ ቋንቋ ጽፎታል። እንደ ቤ/ክ አስተምሮ ውንጌሉን የጻፈበት ዘመን ጌታ በዐረገ 11 ኛው ዓመት ተፈጽሞ 12 ኛው ዓመት ሲጀመር ቀላውዲዎስ ቄሳር በነገሰ በአራተኛው ዓመት ነው። 44 ዓ.ም አካባቢ ጽፎታል።

ውድ ተማሪዎች ቅዱስ ማርቆስ ውንጌሉ የጻፈላችው ሮማዊያን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት እውቅት ስለሌላቸው በውንጌሉ ውስጥ ስለአይሁዳ ባህልና ስለዕብራዊያን አንዳንድ ቋንቋ በመተርጎም አሰቀምጧል። /3፣17 5፣41 7፣12 7፣34 14፣36.../በወቅቱ አብዛኛው ዓለም ያስተዳድሩ የነበሩት ሮማዊያን ከእነሱ በላይ ኃያል እንደሌለ አድርገው ይመኩ ሰለነበር የጌታችን የመድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነትና ሁሉ ማድርግ የሚችል አምላክ መሆኑ ለማስተማር የጌታን ታምራት በውንጌሉ ውስጥ ከሌሎቹ ወንድሞቹ በተለየ ተቀሳቸዋል።

ወንጌሉ የተጻፈበት ዓላማ

1. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለሮማዊያን ለማስረዳት/ለማስተማር/። (1፣1-11 3፣11 9፣7 12፣35-37)

2. ጌታችን ካስተማራችው ትምህርት ይልቅ የሰራቸውን የኃይል ሥራ/ታምራት/ አብዝቶ በመግለጥየጌታችን አምላክነት፣ሁሉቻይነት እና ኃያልነት ለማስተማር።

የማርቆስ ወንጌል አጠቃላይ ይዘቱ ስንመለከት 16 ምዕራፎች እና 678 ቁጥሮች ያሉት ከወንጌላዊያ ሁሉ ትንሽ ምዕራፍ ያለው ወንጌል ነው።ወንጌሉ ሲጻፍ የሚጀመርው በማስተማር ዘመኑ የተፈጸሙ የጌታ ትምህርትና ታምራት በመጥቀስ ነው። በዚህ ከሌሎችን ወንጌላዊያን ወንድሞቹ ይለያል። ማቴዎስና ሉቃስ ከልደቱ ሲጀምሩ ዮሐንስ ከቀዳማዊነቱ ይጀምራል። ማርቆስ ግን በማስተማር ዘመኑ ይጀምራል።

የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል አከፋፈል

ከምዕራፍ 1-6 የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት፣ የጌታ ጥምቀት፣ ሽባውን ስለመፈወሱ፣ ጌታ በገሊላ ተመስግኖ እንዳስተማረ

ከምዕራፍ 7-9 ሰውን ስለሚረክሱ ስራዎች፣ እንጀራን አበርክቶ ሰለመመገቡ፣ በደብረ ታቦር ክብሩን ሰለመግለጹ

ምዕራፍ 10 የጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ፣ በይሁዳ ስለማስተማሩ፣ በኢያሪኮ ዓይነ ስውር ስለመፈወሱ

ከምዕራፍ 11-13 ወደ ኢየሩሳሌም በክብረ ስለመግባቱ፣ ስለወይን ቦታ ስራተኞች፣ ሰለዓለም ፍጻሜ ማስተማሩ

ከምዕራፍ 14-16 ስለ ጌታ እራት፣ ስለ ጌቴሴማኔ ጽሎት፣ ስለ ጌታ መያዝ፣ መሰቀል፣ መሞትና መቀበር፣ ሰለትንሣኤው ያትታል።

3. *የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል*

ሉቃስ ማለት ሊባኖስ /ሉካኖስ/ ማለት ሲሆን ትርጉሙም መብራት ማለት ነው። በትርጓሜ ወንጌል ላይ ዐቃቤ ሥራይ/ሐኪም/ ትንሣኤ ማለት ነው ይላል። ሉቃስ ሰሙ በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ሶስት ጊዜ ተጠቅሷውል። / ቆላ 4፣14 2ኛ ጢሞ 4፣11 ፊል 2፣4 / ቅዱስ ሉቃስ ሀገሩ አንጾኪያ ሲሆን የሁለት ሞያዎች ባለቤት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገል።

ሀ. ባለመድኃኒት ሉቃስ"የተወደደው ባለመድኃኒት ሉቃስ..." / ቆላ 4፣14/

ለ. ሠዓሊ ሉቃስ ፦ በአብዛኞቹ ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያን ትውፊት የቅዱስ ሉቃስን ሰዓሊነት ያሳያል። ምስለ ፍቁር ወልዳ /የእመቤታችን ልጇን ታቀፋ የተሳለው ስዕል/ ቅዱስ ሉቃስ እንደሳለው ይታመናል። የቅዱስ ሉቃስ ሰዓሊነት በጻፋቸው ወንጌልና የሐዋርያ ስራ መመልከት ይቻላል። በአጻጻፉ ቀደም ተከተልን ጠብቆ የጻፈው የሰዓሊነቱ መገለጫ ነው። ቅዱስ ሉቃስ የተማረ/ጥበበኛ/ አባት ነው። ይህንን ትምህርት የተማረው ጠርሴስ አካባቢ እንደሆነና ቅዱስ ጳውሎስን ለትምህርት በሄደበት ወቅት እንደተዋወቅ ይንገራል።

ያሰተማረበት ሀገረና ዕረፍቱ

ቅዱስ ሉቃስ ከዮሐንስ ጋር በመሆን ወደ ጸዕር/ግሪክ/ በመሄድ ዮሐንስ ከፍሎ በሰጠው በመቄዶንያ ወንጌል አስተማሯል። በተጨማሪ የሮሜ የዳረች ወደ ሆኑት ሀገራት በመሄድ ወንጌልን አስተምሯል።

በኔሮን ቄሣር ዘመን መንግስት ወንጌልን እያስተማር እያለ የጣኦት ካህናት ከሰው ወደ ቄሣር አመጡት። ንጉሱምእጁእንዲቆረጥ አዘዘ ቀኝ እጁን ከቆርጡት በኃላ ወደ ቀደመው አድርጎ መልሶታል። በዚህ ዕለት አንገቱን ተቆርጦ ጥቅምት 22 ቀን በ 84 ዓመቱ በሰማዕትነት አርፏል።

ወንጌሉ የተጻፈበት ዘመን፣ቦታ፣ እና ቋንቋ

ቅዱስ ሉቃስ ወንጌሉ የጻፈበት ቦታ መቄዶንያ በምትባል ሀገር ነው። በዚያች ሀገር ገቹ ለነበረው ቴዎፍሎስ ለተባለ ሰው እንደጻፈለት የወንጌሉ መግቢያ ምዕራፍ ይናገራል።/ሉቃ 1፣1/ ወንጌሉ የተጻፈበት ቋንቋ ዮናኒ የሚባል የግሪክ ቋንቋ ነው፥ ወንጌሉ የተጻፈበት ዘመን ጌታ ባዐረገ 21 ኛው ዓመት ተፈጽሞ 22 ኛው ዓመት ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሳር በነገሰ በ 14 ኛው ዓመት ነው።

ወንጌሉ የተጻፈበት ዓላማ

የሉቃስ ወንጌል የተጻፈበት ዓላማ በመግቢያ ላይ በግልፀ ተቀምጧል። ‹‹ስለተማርከው ቃል እርግጡን እንዲታወቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትሎ በተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ።›› በማለት አሰቀደሙ ለመኮንኑ ቴዎፍሎስ ያስተማርውን ወንጌል በጥልቀት እንዲረዳው ብሎ እንደጻፈለት ያስተመራል። በተጨማሪ፥-

1. ከድንግል የተወለድ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማሰረዳት /1፣35-43 2፣49 3፣22-38 4፣3-4 10፣22 23፣43/
2. ጌታ ለደኅነት እንደተገለጠ ለማስተማር
3. ስለመዝሙርና ስለጸሎት የተለያዩ ማስረጃዎች በማቅረብ ያስተምራል/1፣46-55 2፣14፣29-34 3፣21 5፣16 6፣12/

የሉቃስ ወንጌል የሚጠራባቸው መጠሪያዎች፥-

- ስለ ሴቶች /እመቤታችን፣ ኤልሳቤጥ .../ ስለሚጽፍ ወንጌል አንስት ተብሎ ይጠራል። /ሉቃ 8፣1-3/
- ስለመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ደጋግሞ በመጻፉ “ ሰባኬ መንፈስ ቅዱስ” ይባላል። / 1፣35 4፣1 11፣13 12፣12 /
- ለአሕዛብ ክርስቶስ የፍቅር አባት እንደሆነ ስለተጻፈ “ወንጌለ አሕዛብ” ተብሎ ይጠራል።/15፣16/

የወንጌሉ አከፋፈል

የሉቃስ ወንጌል 24 ምዕራፎች እና 1151 ቁጥሮችን በውስጡ ይዟል።

ምዕራፍ 1 መግቢያ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ልደት፣ የእመቤታችን ብስራት

ከምዕራፍ 2-3 የጌታችን ልድትና የሕጻንነት ታሪክ

ከምዕራፍ 4-8 ጌታች የማስተማርና የተአምራት ስራውን በገሊላ ስለመጀመሩ እና የደቀ-መዛሙርቱ መጠራት

ከምዕራፍ 9-19 እየሩሳሌም ስለመጓዙና በይሁዳ ሐገረ ስለፈፀመው ስራ፣ ስለ እምነት የሰጠው ትምህርት

ከምዐራፍ 20-23 እየሩሳኤል ገብቶ ስለማስተማሩ፣ ለስው ልጆች ስለተቀበለው መከራ

ምዕራፍ 24 ስለ ትንሣኤና ዕረገቱ ይተርካል።

4. *የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል*

አራተኛው ወንጌል የተጻፈው በሐዋርያ በቅዱስ ዮሐንስ ነው። በወንጌሉ ላይ ዮሐንስ ጻፈ የሚል ባይኖርም ጌታ ይወደው የነበረ ሐዋርያ ጻፈው ተብሎ ተጠቅሷል። /20፣24/ ጌታ ይወደው የነበረ ሐዋርያ ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ ነው።

የቅዱስ ዮሐንስ ስሞች

ቅዱስ ዮሐንስ ከሚጠራበት ዮሐንስ ከሚለው ሰሙ በተጨማሪ ሰባት የተለያዩ ስሞች አሉት።

- ወንጌላዊ ፡- የአራተኛው ወንጌል ጻፊ ስለሆነ
- ፍቁረ እግዚእ ፡- ጌታ ይወደው የነበረ ሐዋርያ
- አብሎቀለምስስ ፡- ባለ ራዕይ
- ቁጽረ ገጽ ፡- /ፊቱ በሀዘን የደመነ/ የጌታን ስቀለት የተመለከት በመሆኑ በህይወት ዘመኑ ፊቱ ሳይፈታ የኖረ በመሆኑ ቁጽረ ግጽ ተብሏል።
- ታኦሎግስ ፡- ነባቤ መለኮት ማለት ነው።
- ወልደ ነጎድጓድ /ቦአኔርጌስ/ ፡- ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር የሚጠራበት ሰሙ ነው። ይህንን ስያሜ ያወጣለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። /ማር 3፣17/
- ወልደ ዘብዴዎስ ፡- የዘብዴዎስ ልጅ ተብሎ ይጠራል።

የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቤተሰቦዎች

አባቱ ዘብዴዎስ እናቱ ማርያም ባውፍልያ ይባላሉ። አሣ በማጠመድ ላይ የተሰማሩ ደና ገቢ ያላቸው ቤተሰቦዎች ነበሩ። አሰቀድሞ ከእድርያስ ጋር በመሆንየመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር። /ዮሐ 1፣35-43/ ዮሐንስ ማለት ደስታ ፍሣሃ ማለት ነው። /ማቴ 10፣3 ሉቃ 1፣13-14/

የቅዱስ ዮሐንስ ጥሪ

ቅዱስ ዮሐንስ ከወንድሙ ያዕቆብ ጋር በመሆን አሳ በማጥመድ ላይ ሳለ ጌታችን ወደ ገሊላ ባህር ለማስተማር በመጣ ጊዜ እርሱና ወንድሙ እንዲሁምስሞኦን ጴጥሮስ እና ወንድሙ እንድርያስ ጥርቷቸዋል።/ማቴ 4፣21-22 ማር 1፣19-20 /

ቅዱስ ዮሐንስ የምሥጢር ሐዋርያት ከሚባሉት ወገን ነው። /ጴጥሮስ፣ያዕቆብ ና ዮሐንስ/ በዚህ ምክንያት ጌታችን ምሥጢረተአምራትን በቤተ ኢያኢሮስ፣ ምሥጢር መንግስትን በደብረ ታቦር፣ ምስጢር ምጽአትን በደብረ ዘይት፣ምስጢረ ጸሎትን በጌቴሴማኒ በገለጸ ጊዜ አብሮ የተመለከተ ሐዋርያ ነው።

ያስተማረበት ሀገረ

ቅዱስ ዮሐንስ የማስተማረ ስራው በኢየሩሳሌምና በአካባቢያም በመጀመረ ከዚህ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በመሆን በአንጾኪያ አስተምሮል። በዋነኝነት ግን ያስተማረው በእስያ አህጉር በኤፌሶን ከተማ ነው። በኤፌሶን ከተማ ብዙ ታምራትን በማድርግ ወንጌል አስተምሯል። ከኔሮን ቄሣር በመቀጠል የነገሰው ድምጢያኖስ የእራሱን ምስል አስርቶ ወደ ከተማይቱ በመላኩ ህዝቡ እንዲሰግድለት አዋጅ አስንገሯል። ይህ ድርጊት ቅዱስ ዮሐንስ በመቃውሙ ምክንያት ወደ ሮም ተውስዶ በዚህ መንግስት ላይ ያመጹ ስዎች በእስር ወደ ሚቀመጡበት ወደ ፍጥሞ ደሴት በግዞት ተውስዶዋል። በዚያም ሳለ ራዕይ ተገልጦለት ራዕይ ዮሐንስ ጽፏል። ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ለሰባት ዓመታት ያል ከታሰረ በኃላ ንጉሱ ሲሞት ነጻ ወጧል።

ስለ ቅዱስ ዮሐንስ ዕረፍት

ስለ ቅዱስ ዮሐንስ የመጨረሻ ህይወት የተለያዮ አስተምሮዎች አሉ።

1.እንደ ሄኖክ እንደ ኤልያስ ሞተ ስጋ አልቀመሰም። የሚለው የመጀመሪያ አስተምሮ ነው። ጌታችን በውንጌል “እኔ እስከመጣ ድረስ በህይወት ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ?” /ዮሐ 21፣20-25/

‹‹እውነት እላችኃለሁ የስው ልጅ በመንግስቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድርስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ እንዳንድ አሉ።›› /ማቴ 16፣28/ እነዚህ ዮሐንስ መስወሩን የሚያለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸው።

2. በማቴ 20፣22-23 እና ማቴ 10፣38-39 የተጻፈውን በመጥቅስ ሞቷል የሚሉ አሉ።

ወንጌሉ የተጻፈበት ቦታ፣ቋንቋ ና ዘመን

የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል የተጻፈብት ቦታ ኤፌሶን ሲሆን የተጻፈበት ቋንቋ ደግሞ የግሪክ /የዕርዕ/ ቋንቋ ነው።ወንጌሉ የጻፈበት ዘመን ጌታ ባዐረገ በ 30 ዘመን ኔሮን ቄሳር በነገሰ በ 7 ኛ ዓመት ነው። ይህ ማለት በ 63 ዓ.ም ተጽፏል ማለት ነው። ወንጌሉ የተጻፈላቸው ህዝቦች የኤፌሶን ህዝቦች ናቸው።

ቅዱስ ዮሐንስ ስለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምርማንነቱ በመግለጥ ላይ ያተኩራል። በዚህ ምስክሮችን አንስቷል። ካነሳቸው ምስክሮች መካከል፡-

1. የአባቱን ምስክርነት /5፣34 8፣18/
2. የራሱ የወልድ ምስክርነት /8፣18-58/
3. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት / 15፣36 10፣25/
4. የሥራዎቹ ምስክርነት /5፣36 10፣25/

5. የቅዱስን መጽሐፍት ምስክርነት / 5፣39-46/
6. የመጥምቁ መለኮት ዮሐንስ ምስክርነት /1፣7 5፣33-35/
7. የተማሪዎቹ ምስክርነት /15፣27 19፣35/ ናቸው።

ጌታችን የእሱን ማንነት ያስታወቀባቸው ሰባት ቃላት በዚህ ወንጌል ውስጥ ይገኛል። እነርሱም "እኔ ነኝ" በመባል የታወቃሉ

1 የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ /6፣35/
2 የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ /8፣12/
3 የበጎች በር እኔ ነኝ /10፣7/
4 መልካም እረኛ እኔ ነኝ /10፣11/
5 ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ /11፣25/
6 መንገድና ህይወት እኔ ነኝ /14፣6/
7 እወነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ /15፣1/ የሚባሉት ናቸው።

5.3 የታሪክ መጽሐፍ ክፍል

ውድ ተማሪዎች በሐዲስ ኪዳን ቅዳሳት መጽሐፍት ጥናት አከፋፈል መሰረት ከወንጌል መጽሐፍት ክፍል ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የታሪክ መጽሐፍት ክፍል ነው።

ከጌታ ዐረገት በኃላ የመጀመሪያቱ የቤ/ክ ታሪክ የሚናገር ክፍል ከ 34 ዓ.ም እስከ 64 ዓ.ም ድርስ ያለው የቤ/ክ ታሪክ የሚናገረው የሐዲስ ኪዳን የመጽሐፍ ክፍል "የሐዋሪያት ስራ" የሚባለው ነው። በይዘቱ ከክርስቶስ ዕረገት በኃላ ሐዋርያት ያደርጉት የወንጌል ትምህርት እና ሐዋርያዊ ገዞ የሚተርክ በመሆኑ የሐዲስ ኪዳን የታሪክ መጽሐፍ ወይም የቤ/ክ ታሪክ ተብሎ ተጠርቷል።

ሐዋርያ፡- ማለት የተላከ፣መልክተኛ፣ደጃዝማናች፣ቀላጤ፣ምጥውጋ፣ፈንው፣ሐያጅ ማለት ነው። ይህ ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጣቸው ለ 12 ቱ ሐዋርያት ነው። ከእነሱ ውጪ

ሀ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ /ዕብ 3፣1/

ለ. በርናባስና ጳውሎስ በአንድነት /ሐዋ 14፣4/

ሐ. ጳውሎስ /ሮሜ 1፣1 1 ቆሮ 9፣1-2 15፣9 /

1.የሐዋርያት ስራ

የሐዋርያት ስራ በግእዝ ግብረ ሐዋርያት በመባል ይጠራል። ለመጽሐፉ የተሰጠው ሌላው ስም መጽሐፍ ግብረ ልቡካን፣ዜና ሐዋርያት ይባላል። ይህ መጽሐፍ እውነተኛ የክርስትና ጠባይን ስለሚገልጥ የተለየ የክርስትና መጽሐፍ ይባላል።

የሐዋርያት ስራ ጻፊና የተጻፈለት ሰው

የሐዋርያት ስራ ጽሐፊ ቅዱስ ሉቃስ ሲሆን የተጻፈለት ሰው ወንጌሉን ለጻፈላት ለቴዎፍሎስ ነው። ይህንን የሚደገፉ ነጥቦች

- ቴዎፍሎስ የተባለ ሰው በመገለጡ /ሐዋ 1፣1/
- የሉቃስ ወንጌል መድምደሚያ ቃላትና የሐዋርያት ስራ መነሻ ቃላት በብዛት አንድ መሆናቸው። /ሉቃ 24፣44-53 ሐዋ 1፣1-2/
- በመጽሐፈ ስንክሳር ይንን የሚደግፍ/የሚመሰክር/ ቃል መገለጹ። ጥቅምት 22

የተጻፈበት ዘመን፣ ቦታና ቋንቋ

የሐዋርያት ስራ ቅዱስ ሉቃስ በሮም ከተማ ሆኖ በግሪክ ቋንቋ እንደጻፈው ብዙዎች ይስማማሉ። ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት ዘመን ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ በሮም ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሰረበት ወቅት ስለኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ እናዳስተማረ በመጨረሻ ክፍሉ ላይ ይገልጻል። ይህም ዘመን 62-64 ዓ.ም ድረስ ያሉት ሁለት ዓመታት ናቸው። በዚህ መሰረት የተጻፈበት ዘመን 64 ዓ.ም መጨረሻ 65 ዓ.ም መጀመሪያ ሊሆን ይችላል።

የሐዋርያት ስራ ይዘት፡- ጻፊ ቀድሞ ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ ዕረገቱ ከጻፈ በኃላ ከጸራቅሊጦስ ጀምሮ የመጀመሪያውን የቤ/ክ መሠረትና ጎብረት፣ የቤ/ክ ተአምራት፣ የመጀመሪያውን ጥምቅት፣ ስደት፣ እንዲሁም መጀመሪያዎቹ ሰማዕታት... በማንሳት ቤተ-ክርስቲያን ከምን ተነስታ ከምን እንደደረሰች የሚያስገነዝብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ አከፋፈል

የሐዋርይት ስራ 28 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ይከፈላሉ

ምዕራፍ 1 የጌታ ዕረገት፣በይሁዳ ምትክ ሐዋርያ ቅዱስ ማትያስመተካቱ

ከምዕራፍ 2-7 በበዓለ ሃምሳ የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ለሐዋርያት መወረዱን፣ በአንድ ስብከት ሶስት ሺ ሰዎችን ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳሳመነ፣ቅዱስ ጴጥሮስ ለ 40 ዓመት ሙሉ ሽባ የሆነን ሰውማዳኑን፣ የመጀመሪያ የቤ/ክ አንድነት እና አኗኗር፣ የሰባቱ ዲያቆናት ምርጫ እንዲሁም ሰለ ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ

ከምዕራፍ 8-12 የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በፊሊጶስ መጠመቁ ፣የሳውል መጠራት፣የአንጾኪያ ቤ/ክመመሠረትና ማደግ፣ የሐዋርያ ቅዱስ ያዕቆብ ስማዕትነት

ከምዕራፍ 13-18 የቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያ ጉዞና ስራዎቹ፣ የመጀመሪያበኢየሩሳሌም የተደረገ ጉባኤ፣50 ዓ.ም

ከምዕራፍ 19-28 የቅዱስ ጳውሎስ በቂሣርያ ለሁለት ዓመት ታስሮ መቆየቱ ወደ ሮም በይግባኝመመለሱ፣ ጳውሎስ ታስሮ ሳለ ስለክርስቶስ ማስተማሩ ይተረካል።

5.4 የሥርዓት መጽሐፍት ክፍል

ውድ ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ስር ስለ ሥርዓት ምንነት እና ስለ ስምንቱ የሥርዓት መጽሐፍት እንመለከታለን። ወደ እርሱ ከሚሄዳችን በፊት የሥርዓትን አስፈላጊነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?

እግዚአብሔር አምላክ ያለ ሥርዓት እንዲሁን የፈጠረው ፍጥረት የለም ። ብሉይና ሐዲስ ኪዳን የሚያወሱት እግዚአብሔር ሁሉ በአግባብና በሥርዓት የሚከናውንና ያከናወነ አምላክ መሆኑን ነው። "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይ እና ምድር ፈጠረ" ዘፍ 1፣1 ይህ የሥነ-

ፍጥረት መጀመሪያ ቃል በዘፍጥረት ላይ እንደተመዘገበ እግዚአብሔር ስድስት ቀናት ውስጥ ፍጥረታትን ሲፈጥር ሁሉ በሥርዓት እንዳከናውነ የሚሳይ ቃል ነው።

የሰው ልጅ ለመዳን ከጉስቁልና የጸዳ ህይወት እንዲኖርው እግዚአብሔር ባስቀመጠለት ሥርዓት መጓዝ እንደሚገባው ቅዱሳት መጽሐፍት ይመሰክራሉ።

“ከሥርዓት የሚርቁትን አጎሳቀልካቸው” መዝ 118፣118

“ምድር ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች ሕጉን ተላለፈዋልና ሥርዕቱንም ለውጠዋልና።” ት ኢሳ 24፣5

“ያለሥርዓት የሚሆዱትን ገስጹአቸው ።” 1 ተሰ 5፣14 2 ተሰ 3፣6

5.4.1 ሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው

ሥርዓት ማለት “ሠርዐ” ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ሕግ፣ደንብ፣አሠራር ማለት ነው። ሥርዓት ማለት የመንፈሳዊ አገልግሎት ሕግና ደንብ ወጥቶለት የአስራር ሂደቱን የተስተካከለ፣ መሻሻና መደረሻ ያለው እንዲሁም ሊጠበቅ፣ እንከብካቤ ሊደረግለት የሚገባ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የተቀደሰ አሠራር ማለት ነው።በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ “ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ተብሎ ይጠራል።” ሲኖዶስ ማለት የአባቶች ጉባኤ ማለት ነው።

5.4.2 የሥርዓት መጽሐፍት በማን፣መቼና በምን ቋንቋ ተጻፉ

የሥርዓት መጽሐፍት ከትንሣኤ እስከ ዕረገት በነበረው ወቅት ጌታ ያስተማረውን ትምህርትና ሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያን፣ጳጳሳትና ምዕመናን አንዴት መመራት እንዳለባቸው ያስተምራል። የሥርዓት መጽሐፍት የተጻፉት በሐዋርያትና በሐዋርያን አበው ነው። የተጻፉበት ዘመን ከትንሣኤ በኃላ (ከክርስቶስ ዕርገትና ከርደተ መንፈስ ቅዱስ በኃላ) ባሉት ወቅታት ነው። የተጻፈበት እናት ቋንቋ የሱርስት ቋንቋ(ጥንታዊ የሶርያ ቋንቋ) ሲሆን አንዳንዶች የጽርዕ(የግሪክ ቋንቋ) ቋንቋ ነው ይላሉ።

5.4.3 የሥርዓት መጽሐፍት አከፋፈል እና ይዘት

የሥርዓት መጽሐፍት በሶስት አቤት ክፍሎች ይከፈላሉ። እነሱም፦

ሀ. የቤተ-ክርስቲያን አመሠራረት፣ አወቃቀር፣አጠቃላይ የአገልግሎት ሥርዓትና ትምህርት ክፍል የሚያተኩሩ ናቸው።

በዚህ ስር የሚካተቱ መጽሐፍት አራት ናቸው። እነሱም ዲዲስቅልያ፣ግጽው፣ አብጥሊስና ሥርዓተ ጽዮን ናቸው። እነዚህ 85 ቱ የሐዋርያት ቀኖናዎች ተብለው የሚጠሩት ናቸው።

ለ. ኪዳን ክፍል

በዚህ ስር የሚገኙት ሁለቱ የኪዳን መጽሐፍት (መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊና መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ) የሚባሉት ጌታ ከትንሣኤ እስከ ዕርገት ያስተማራቸው ትምህርት የያዙ ናቸው።ጌታችን ከትንሣኤ በፊት ያስተማራቸው ትምህርት፣ ታምራት እና ታሪክ ወንጌል ተብሎ ሲጠራ ከትንሣኤ እስከ ዕርገት ያለውኪዳንተብለው ይጠራል።

ሐ. የአገልጋዮች አበው ነብያት፣ሐዋርያትና አርድዕት ወ.ዘ.ተ የሚመለከት ክፍል ነው። አገልጋዮች በሥርዓት መዝዝ እንደሚገባቸው ይተነትናል።

ውድ ተማሪዎች 8 ቱ የስርዓት መጽሐፍት ከ 81 ቅዱሳት መጽሐፍት እንዲካተቱ የወሰኑት 318 ሊቃውንት በኒቃያ ጉባኤ ተሰብስበው ባለበት ውቅት ነው።

1. መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ

መጽሐፉ 59 አንቀጾች ያሉት ሲሆን በዮሐንስ፣በጴጥሮስና ማቴዎስ እንደተጻፈ ይንገራል። ሌላው 11 ዱ ሐዋርያት እንደጻፉትም ይንገራል። ኪዳን የሚለው ቃል በዚህ አገባብ ትምህርት፣ ምስጋና ማለት ሲሆን ጌታችን ለሐዋርያት ከትንሣኤ በኃላ ለ 40 ጊዜ እየተገለጠ ያስተማራቸው ትምህርት ማለት ነው።

የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ይዘት ሥርዓት ጸሎትና ሥርዓት ቅዳሴ ነው። ሶስቱ ኪዳን ዘዘወትር በቤ/ክ የሚደረሱ የምስጋና ጸሎቶች ናቸው። አጠቃላይ በውሰጡ የሚገኙት፡-

- ኪዳን ዘዘወትር (ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት፣ ኪዳን ዘንግህና ኪዳን ዘሠርክ)
- ቅዳሴ እግዚእ- በእንተ ቅዳሳት
- ትምህርት ኅቡአት - ፍተሐት ዘውልድ
- በሰማይ ይሐሉ ልብክሙ - እግዚአብሔር ዘብርሃናትናቸው።

2. መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ

ሁለተኛ መጽሐፍ ኪዳን በስድ ንባብ መልክ የተጻፈ ነው። አጠቃላይ ይዘቱ ስለ ዳግም ምጽአት፣ ስለሐሳዊ መሲሕ፣ ስለ ካህናት ከፍተኛ ና ዝቅተኛ ሹመት/አገልግልት/፣ ስለ ምዕመናን ንዑስ ክርስቲያን ሥርዓት ጥምቅትና ምሥጢረ ቁርባን የሚናገረ ነው። በዚህ ይዘቱ ከራዕይ ዮሐንስ ጋር ይመሳሰላል። እንደአባቶቻችን አስተምሮ ሁለቱ ኪዳናት 60 አንቀጾች በጋራ ያለቸው ሲሆን 59 አንቀጾች ኪዳን ቀዳማዊ ሲባሉ 1 አንቀጽ በስድ ንባብ መልክ የተዘጋጀ ኪዳን ካልዕ ነው።

3. ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ

ጽዮን ማለት አንባ መጠጊያ ማለት ነው። ሐዋርያት የመንፈስቅዱስን ጸጋ ከተቀበሉ በኃላ በጽርሐ ጽዮን ተሰባሰብው ባለበት ውቅት ስለ ሶስቱ የክህነትማዕረጋት፣ ስለአገልግሎትና ሥነ-ምግባር፣ ስለበዓላትአከባበረ፣ ስለስግዕታት መታሰቢያ፣ ስለ ቅድመ ፍሲካ ላለውጾም ፣ስለ ቅዱስ ቁርባን፣ ስለቅዱሳት መጽሐፍት ምንባብ ወዘተ ሥርዓት የደነገጉበት መጽሐፍ ነው።

የዚህ መጽሐፍ መሪ ምልክቱ “ዓይን” ይባላል። የሥርዓተ ጽዮን ሌላው ስያሜ”ሲኖዶስ ቀኖናት ዘጽዮን” ወይም “መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት” ተብሎ ይጠራል። ይህ መጽሐፍ ትዕዛዛቱ የሚፈጸሙት በዘመን ሐዋርይት ብቻ ሳይሆን ከእነሱ በኃላ ለሚመጣው ዘመን የተደነገገ ነው። በመጨረሻ ቅዱሳን ሐዋርያትና አረድዕት ተከፋፍለው ያስተማሩበትን ሀገረ በዝርዝር ያሰቀምጣል።

4. አብጥሊስ ሲኖዶስ

ይህ መጽሐፍ 82 ቀኖናት/አንቀጾች/ያለበት የመጽሐፍ ሲኖዶስ ክፍል ነው።

አብጥሊስ ማለት አፖስቶሊ ከሚለው የግሪክ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም "የሐዋርያት ቀኖናት" ማለት ነው። መጽሐፍ በ 1ኛ መ/ክ/ዘመን ሐዋርያት ስለቅዱስ ሲኖዶስ ድንጋጌዎች ይናገራል። የሲኖዶስ ስብስባ ክርስቲያን ሁለት ወይም ሶስት ኤጵስ ቆጶሳት በተገኙበት ይደረጋል ይላል።

በተጨማሪ ስለ 81 ቅዱሳት መጽሐፍት ይዘረዝራል፣ ሌላ ስለ ካህናት ጋብቻ፣ ስለአርብና ረቡዕ ጾም ፣ስለሐሰተኛ መጽሐፍ ወዘተ የሚወስንና የሚከለከሉ ቀኖናት አሉት። ቅዱስ ቀሌምንጦስ በኩሉ ለአሕዛብ የላኩት መጽሐፍ ነው።

መጽሐፈ አብጥሊስ መሪ መልክቱ "ረስጠአ" የሚል ምሳጻረ ቃል ነው። ረስ ማለት በአረብኛ "ሐዋርያ" ማለት ሲሆን ጠ "ቀኖና ትዕዛዛት፣ አ "አንድኛ ቀዳማዊ" ማለት ነው።

5. ትዕዛዘ ሲኖዶስ

ይህ መጽሐፍ 72 ቀኖና /አንቀጽ/ያለበት የሲኖዶስ መጽሐፍ ክፍል ነው። ትዕዛዝ ማለት በቁሙ ከሥራ አስቀድሞ የሚሰጠ ደንብ፣ሥርዓት ወይም ሕግ አድርግ አታድረግ የሚል ፈቃድ ማለት ነው። ይህም መጽሐፍ በቀሌምንጦስ እጅ ሐዋርያት ህገ ቤ/ክን ለአሕዛብ ለማሳወቅ ጽፈውታል።

ውድ ተማሪዎች መጽሐፉ(ትዕዛዘሲኖዶስ) ስለ ሚመቱ መላዕክት፣ ዐሥረት፣ መባዕ፣ ሥርዓተ ቁርባን፣ጸሎት ና ሰንበት በሰፊው ያትታል።

የዚህ መጽሐፍ መሪ ምልክቱ "ረስጠብ" ሲሆን ትርጉሙ እንደቀደመው ነው። በግብጽ ቋንቋ "ሁለተኛ፣ ዳግማዊ" ማለት ነው። "ሐዋርያት ቀኖናት ቀሌምጦንስ ዳግማዊ" ማት ነው።

6. ግጽው ሲኖዶስ

ይህ መጽሐፍ 57 ቀኖና /አንቀጽ/ ያለበት መጽሐፍ ነው። ግጽው ማለት የታየ፣የተገለጠ፣ ጉልሕ፣ ሥዕል ማለት ነው።

ስለሚመተ ክህነት ሲያብራራ ቢያንስ ለአንድ ኤጵስ ቆጶስ በሠመቱ ጊዜ መገኘት አንዳለባቸው ያሰረዳል። 81 ዝርዝር መጽሐፍት አምላካዊት/ቅዱሳት መጽሐፍት/ ያስቀምጣል።

በተጨማሪ ስለ ህዝባዊያን ተልዕኮ፣ስለ ትህትና፣ ስለ 10ቱ ቃላት፣ ስለ ዐሥራት፣ስለ ሰንበት፣ ስለሙታን ተዘክር፣ስለ ቁርባንና ጋብቻ በዝርዝር የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው።

መሪ ምልክቱ "ረስጠጅ" ሲሆን ይህ ማለት ሐዋርያት ለቀሌምጦንስ የሰጡት ሦስተኛ መጽሐፍ ማለት ነው።

7. መጽሐፈ ዲዲስቅልያ

ዲዲስቅልያ ማለት ትምህርት ማለት ነው። ይህንን ስያሜ ያገኘው ከመጽሐፉ ይዘት አንጻር ነው። በ 43 አንቀጾች የተከፈለ ትምህርቶች እናተግሳጾችን የያዘ መድብል ነው። በሌላ አጠራር "ዲዲስቅልያ ዘሐዋርያት" ይባላል። ዲዲስቅልያ በአጠቃላይ ይዘቱ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ስለ ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር ትምህርቶች ያዘ የሚገኝ መጽሐፍ ነው። የዚህ መጽሐፍ መሪ ምልክቱ "ድስቅ" ይባላል።

8. መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

ይህንን መጽሐፍ የጻፈው ቅዱስ ቀሌምንጦስ ሲሆን ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ጌታ የተናገረው በመመስረት የጻፈው ነው። ቅዱስ ቀሌምንጦስ በ 90 ዓ.ም የሮም ሊቀ ጳጳስ ሆኖ የተሾመ ቅዱስ አባት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በህይወት መጽሐፉ ላይ ስሙ መጻፉን በፊልጵስዮስ መልእክቱ ላይ ጠቅሷል። (ፊል 4፣3)

መጽሐፉ ከአዳም ጀምሮ ስለነበሩ አበው ቅዱሳን ይዘረዝራል። እንዲሁም ስለገነትና ከገነት ወጥተው ደብረ ቅዱስ ስለገቡ ሰዎች ሁኔታ ይተነትናል። በተጨማሪም ይዘቱ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ እና ቀኖናዊ ቅርጽ ያለው ነው።

አዲስ ቤ/ክ የሚባረክበት ሥርዓት አንዲሁም በሰሞነ ሕማማት ምዕመናን ከሥጋዊ ስራዎች ማረፍ እንደሚገባቸው ያትታል። በስተ መጨረሻም ቅዱስ ቀሌምንጦስ ስለአየው ራዕይ ይናገራል።

የመጽሐፉ ልዩ ምልክት "ጽጥ" ነው። ይህም ጽጥሮስ ማለት ነው።

ማጠቃለያ

እነዚህ ስምንቱ የሥርዓት መጽሐፍት መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ጥራዝ ሲታተም ያልተካተቱበት ምክንያት የሥርዓት መጽሐፍት በመሆናቸው የአብያተ ክርስቲያናት መሪ ቅዱስ ሲኖዶስ ጨምሮ አገልጋይ ካህናት ስለሚመለከት ነው። በተጨማሪም ስምንቱ የሥርዓት መጽሐፍት በውስጣቸው በያዟቸው ምስጢራት ምክንያት ከካህናት በስተቀር ለምዕመናን እንዳይሰራጩ የሚል ትዕዛዝ ይገኝበታል። (መጽ ሲኖዶስ ገጽ 90 ረስጠአ 81፣55) ሌላው ምክንያት አንዳንዱ መጽሐፍት በይዘታቸው ትልልቅ በመሆናቸው አንድ ጥራዝ ውስጥ ለማካተት አስቸጋሪ ሆነዋል።

ተ.ቁ	የመጽሐፍ ስም	መሪ ምልክት	አንቀጽ
1	መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ	፩ ኪዳን	59
2	መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ	፪ ኪዳን	1
3	ሥርዓተ ጽዮን	ዓይን	30
4	አብጡሊስ	ረስጠአ	82
5	ትዕዛዝ ሲኖዶስ	ረስጠብ	72
6	ግጽው	ረስጠጀ	57
7	ዲዲስቅልያ	ድስቅ	43
8	ቀሌምንጦስ	ጴጥ	60

5.5 የመልዕክት መጽሐፍት ክፍል

ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች በቀደሙት የትምህርት ርስቶች ስር የወንጌል ክፍል፣ የታሪክ ክፍል ፣ የሥርዓት መጽሐፍት ክፍሎች በእግዚአብሔር ቸርነት ተመልክተናል። በዚህ የትምህርት ርዕስ ውስጥ ከሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት መካከል በብዛቱ በአከፋፈል አንደኛ የሆነው የመልዕክት ክፍል እንመለከታለን። እግዚአብሔር ይገለጥልን!!! አሜን!!!

ሐዋርያት በአይን ላልተመለከቷቸው እና ለተመለከቷቸው ምዕመናን መልዕክት እየጻፉ ይልኩላቸው ነበር። ከሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ አብዛኛቹ የመልዕክት ይዘት ያላቸው መጽሐፍት ናቸው። ከ 35 ቱ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ 21 የመልዕክት መጽሐፍት ሲሆኑ ከእነዚህ(ከ 21) ውስጥ 14 ቱ የቅዱስ ጳውሎስ፣ 3 ቱ የቅዱስ ዮሐንስ፣ 2 ቱ የቅዱስ ጴጥሮስ 1 የቅዱስ ይሁዳ እና 1 የቅዱስ ያዕቆብ መልዕክታት ናቸው። እነዚህ 21 መልዕክታት ከተቀባዮቹ አንጻር በሁለት ይከፈላሉ።

ሀ. ለማኅበረ የተላኩ መልዕክታት /ለአማኝ ምዕመናን/ ሲሆኑ በቁጥራቸው 15 ናቸው። እነርሱም ሮሜ፣ 1 ኛ ና 2 ኛ ቆሮንጦስ፣ ገላቲያ፣ ኤፌሶን፣ ፊልጵስዮስ፣ ቆላሲስ 1 ኛና 2 ኛ ተሰሎንቄ፣ዕብራዊያን፣ 1 ኛ ና 2 ኛ ጴጥሮስ እና 1 ኛ የይሁዳ መልዕክት ናቸው።

ለ. ለግለሰብ የተላኩ መልዕክታት። እነርሱም በቁጥር 6 ሲሆኑ 1 ኛ ና 2 ኛ ጢሞቲዮስ፣ቲቶ፣ ፊልሞና፣ 2 ኛና 3 ኛ ዮሐንስ ናቸው።

5.5.1 የመልዕክት መጽሐፍት አጠቃላይ ይዘት

ሃያ አንዱ መልዕክታት በዋነኝነትትኩረት አድርገው የተጻፉት የሃይማኖት፣የሥርዓተ ቤ/ክ እና የስነ-ምግባር ትምህርቶች ላይ ነው።
በተጨማሪ በሌሎች አካላት የሐሰተኛ መምህራን/የተማሩት የስህተት ትምህርትና የስነ ምግባር እርምት ላይ ትኩረት አድርጓል።

5.5.2 የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት

ቅዱስ ጳውሎስ አይሁዳዊ ስሙ ሳውል ይባል ነበር። ሳውል የሚለው ስም ሰኦል ከሚለው ስም ጋር በትርጉም ተመሳሳይነት ሲኖረው በእግዚአብሔር የተለመነ ማለት ነው። ጳውሎስ የሚለው ስም በቤተ ክርስቲያን ብርሃን ተብሎ ይተረጎማል።

ቅዱስ ጳውሎስ ነገዱ ከአይሁዱ ወገን ከነገደ ብንያም ነው። ሮሜ 11፡1 ፊል 3፡5 የተወለደው ኪልቅያ ዋና ከተማ በጠርሴስ ነው። ሐዋ 9፡11 21፡39፤22፡3 ነገር ግን የሮሜ ዜግነት ነበረው። ሐዋ 16፡3፤22፡25፤23፡37 ትምህርቱንም ፈሪሳዊ ሆኖ እንደነበር ተገልጧል። ሐዋ 23፡6፤26፡5 ፊል 3፡5

ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ ከማመኑ በፊት ክርስትያኖችን ያሳድድ ነበር። ይህንንም ያደርግ የነበረው ባለማወቅ ነበር። ሐዋ 26፡9 1 ኛ ጢሞ 1፡13 ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት በሞተ ጊዜ በእርሱ መወገር ተስማምቶ የገዳዮቹን ልብስ ይጠብቅ ነበር። ሐዋ 7፡60 22፡20 ከእስጢፋኖስም ሞት በኋላ በእየሩሳሌም ቤተ-ክርስቲያን ላይ በነበረው ስደት ዋነኛው አሳዳጅ ነበር። ሐዋ፡8፡3

ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ክርስትና የተጣራው በሐዋርያት ወንጌል ተሰብኮለት ሳይሆን በራሱ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ገላ 1፡11 ሐዋ 9

የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞዎች

ውድ ተማሪዎች የክርስቶስን ወንጌል በዓለም ለመስበክ ያደረጋቸው ሐዋርያዊ ጉዞዎች በሐዋርያት ስራ ውስጥ የተመዘገቡት የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞዎች ሦስት ናቸው።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ *14* መልእክታት ጽፏል።

1. የመጀመሪያ ጉዞው በደሴቱ ቆጵሮስና በታናሽ ኢስያ ውስጥ በቋንቋልያ እንዲሁም በደቡባዊ ገላትያ በሚገኙ ከተሞች ነበር።
2. ሁለተኛ ሐዋርያዊ ጉዞው መቄዶኒያ እና አካያ በተባሉት አውራጃዎች ነበር።
3. በሦስተኛው ሐዋርያዊው ጉዞው በእስያ መቄዶኒያና አካያ አስተምሯል።

1. የሮሜ መልእክት

ቅዱስ ጳውሎስ የሮሜ መልእክት የጻፈው በቆሮንጦስ ከተማ ሲሆን በሦስተኛው ሐዋርያዊ ጉዞ መጨረሻ በቆሮንጦስ ለሦስት ወራት በተቀመጠበት ወቅት ነው።

መልእክቱ የፃፈበት ምክንያት ሁለት ሲሆን፡- የመጀመሪያው በሮሜ ቤተ-ክርስትያን ውስጥ ቢጸ ሐሳውያን አይሁድና ከአሕዛብ ክርስቶስን ባመኑ ወገኖች መካከል ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት በትምህርት ለማስወገድ። ሮሜ 1፡16፤2፡9፤3፡9/31 ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በወቅቱ ጳውሎስ ቅድሚያ ወደ ሮሜ ከዚያም ወደ እስጳንያ ለመሄድ የነበረው ዕቅድና የጉዞውን አስፈላጊውን ትብብር እንደሚያደርጉለት የነበረውን ተስፋ አስቀድሞ ሊጽፍላቸው ስለወደደ ነው። ሮሜ 1፡19/15

የሮሜ የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት ስንመለከት በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት የተደገፈ ጥልቅ መረጃ የያዘ መልእክት ነው።

የመልእክቱ አከፋፈል

የሮሜ መልእክት 16 ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን ይህንንም በ 7 ከፍሎ መመልከት ይቻላል

1. መግቢያ ሮሜ 1፡1/11
2. የእግዚአብሔር ጽድቅ ለአይሁድም ለአሕዛብም የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የጻፈው ትምህርት ሮሜ 1፡16/4፡23
3. ጽድቅን ያገኙ ሰዎች ለጽድቅ እንጂ ለኃጢያት መገዛት እንደሌለባቸው የጻፈው ትምህርት ሮሜ 5፡1/6፡23
4. በክርስቶስ ስለተገኘው አርነት የፃፈው ትምህርት ሮሜ 7፡1/8፡39
5. መዳን ለእስራኤልም ለአሕዛብም እንደሆነ የፃፈው ትምህርት ሮሜ 9፡1/11፡36
6. ስለ ክርስትያናዊ ሥነ-ምግባር የፃፈው ትምህርት ሮሜ 12፡1/13፡5
7. ማጠቃለያ ሮሜ 15፡1/16፡27

2. የመጀመሪያይቱ የቆሮንቶስ መልእክት

በአጠቃላይ ወደ ቆሮንጦስ የተላኩት መልእክታት ሁለት ሲሆኑ እነዚህ መልእክታት የተፃፈላቸው ክርስትያኖች በሚኖሩበት የቆሮንጦስ ከተማ በግሪክ ሀገር ውስጥ ያለችው የአካያይ አውራጃ ዋና ከተማ ናት። በዚህ ከተማ ወንጌልን የሰበከውናቤተ-ክርስትያኒቱን የመሰረተው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የሰበከው በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው ወቅት ሲሆን መልእክቱ የተፃፈው በኤፌሶን በ 3 ኛ ሐዋርያዊ ጉዞው ላይ ሳለ በኤፌሶን ነው። ይህም በ 55 ዓ.ም ገደማ ነው።

መልእክቱ የተፃፈበት ምክንያት ሁለት ሲሆን፡- አንደኛው በቆሮንጦስ ቤተ ክርስትያን ምዕመናን ዘንድ እኔ የጳውሎስ ነኝ እኔ የአጵሎስ ነኝ እኔ የኬፋ ነኝ እኔ የክርስቶስ ነኝ የሚል መለያየት ተፈጥሮ ስለነበር ይህም ልዩነት እንዲያስወግዱ ለመግለጽ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከቆሮንጦስ ምዕመናን በጽሑፍ ተልከው ለነበሩ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ነበር።

የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት ሥነ-ምግባርን ሥርዓትንና ሃይማኖትን ያጠቃለለ የተግሳፅ ትምህርት ነው።

የመልእክቱ አከፋፈል

1 ኛ. የቆሮንጦስ መልእክት 16 ምዕራፎች ሲኖሩት እነዚህ በስድስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡-

1. መግቢያ 1፡1/9
2. በመካከላቸው ስለነበረው ክርክርና መለያየት የጻፈላቸው ተግሳጽ 1፡9/4፡/21
3. ከዝሙት ርቀው በድንግልና ወይንም በጋብቻ እንዲኖሩ የጻፈው ትምህርት 5፡1/7፡40
4. ለጣዖት የተሰዋን መስዋእት መብላት እንደማይገባ የፃፈላቸው ትምህርት 8፡1/10፡33
5. በማኅበር ሲሰበሰቡ ለሚያደርጓቸው ነገሮች የደነገገላቸው ሥርአት 11፡1/15፡58
6. መደምደሚያ 16፡1/24

3. ሁለተኛይቱ የቆሮንቶስ መልእክት

ሁለተኛይቱ የቆሮንጦስ መልእክት የተፃፈው ከመቄዶንያ ሲሆን ጊዜውን በ 3 ኛው የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ ወቅት የመጀመሪያይቱ መልእክት የተፃፈው ከዓመት በኋላ ነው። ይህም በ 56 ዓ.ም ገደማ ነው። ሁለተኛይቱ የቆሮንጦስ መልእክት ተፃፈችበት ምክንያት ሦስት ሲሆን፡- አንደኛው ምክንያት የቆሮንጦስ ክርስትያኖች ከስህተታቸው ተመልሰው ንስሐ በመግባታቸው የተሰማውን ደስታ ለመግለጽ ንስሐ ያልገቡትንም ንስሐ እንዲገቡ ሊመክራቸው ስለፈቀደ 2 ቆሮ 5፡6/7 12፡19/21 ሁለተኛው ምክንያት በመካከላቸው ገብተው ልዩ የሐሰት ትምህርት ያስተምሩ ከነበሩ ሐሰተኛ መምህራን እንዲጠበቁ ለማስጠንቀቅ 1፡ 1/15 እና ሦስተኛው ምክንያት ቀደም ሲል ለኢየሩሳሌም ክርስትያኖች እንዲሰጥ ጀምረውት የነበረውን የአስተዋፅኦማሰባሰብ አጠናቀው እንዲጠብቁት ስለ ልግስና ስጦታ ሊጽፍላቸው ስለወደደ 8፡1 9፡7

የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት ስነ ምግባርን ሥርዓትንና ሃይማኖትን ያጠቃለለ ጳውሎስ ስለራሱ ሕይወት በመግለጥ የፃፈላቸው ትምህርት ነው።

የመልእክቱ አከፋፈል

ሁለተኛይቱ የቆሮንጦስ መልእክት በአጠቃላይ 13 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ይህንንም በአምስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1/7
2. የቅዱስ ጳውሎስና የባልንጀሮቹ አገልግሎት በመከራ ውስጥ 1፥8/7፥16
3. ስለጀመሩት የልግስና ስጦታ አገልግሎት የግፈላቸው ማበረታቻ 8፥15
4. ሐሰተኞች ሐዋርያትን ያለ አግባብ በመታገላቸው የግፈላቸው ተግሳፅ 10፥1 13፥4
5. ማጠቃለያ 15፥5/14

4. የገላትያ መልእክት

የገላትያ መልእክት የተግፈችው በ 50 ዓ.ም (አንዳንድ መጽሐፍት በ 48 ዓ.ም ተፅፏል ይላሉ) በአንጾኪያ ሲሆን የተግፈበት ምክንያት በመካከላቸው የገቡት የሐሰት ወንድሞች ጳውሎስ ክርስቶስን አላየውም ቁጥሩም ከክርስቶስ ሐዋርያት አይደለም ስለዚህትምህርቱን ልትቀበሉት አይገባም ብለው አስተምረው ስለነበር ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ የሆነው በሰው ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ሊያስረዳቸው ስለፈለገ ነው። 1፥1 11፥15

የመልእክቱ አከፋፈል

የገላትያ መልእክት በአጠቃላይ ስድስት ምእራፎች ያሉት ሲሆን እነዚህንም በአምስት ከፍሎ መመለከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-5
2. ጳውሎስ ሐዋርያነቱን እያስረዳ ሐሰተኞችን እየተቃወመ ስለ ጻድቅ የጻፈላቸው ትምህርት 1፥6 2፥21
3. ስለ ሕግና ስለ ክርስቶስ ያቀረበው ትምህርት። 3፥1 4፥31
4. ስለ ክርስትያናዊ ስነ-ምግባር የግፈው ትምህርት 5፥1 6፥10
5. ማጠቃለያ 6፥11 6፥10

5. የኤፌሶን መልእክት

የኤፌሶን መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ እስራት ወቅት በሮም እስር ቤት ሆኖ ከጻፋቸው መልእክቶቹ አንዱ ነው። የጳውሎስ የመጀመሪያ የሮም እስራቱ ከ 62-64 ዓ.ም ሲሆን መልእክቱ የተግፈው በ 62 ገደማ ነው።

የኤፌሶን መልእክት የተጻፈበት ምክንያት ሁለት ሲሆን የመጀመሪያው የኤፌሶን ክርስትያኖች አሕዛብ ቢሆኑም ከእስራኤል ጋር አንድ ሆነው በክርስቶስ ጸጋ መዳናቸውን እና ክብር ማግኘታቸውን አውቀው በእምነታቸው እንዲጠነክሩ ለማድረግ 1፥3/9 2፥11-12 3፥10-19 ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በክርስትና ሕይወታቸው እንዲያድጉ እንጂ ወደ ፊተኛው ኑሮአቸው እንዳይመለሱ ከጨለማ ስራ ጋር እንዳይተባበሩ ሊያሳስባቸው ነው። 4፥13/16 17፥5

የመልእክቱ አከፋፈል

የኤፌሶን መልእክት ስድስት ምዕራፎች ሲኖሩት እነዚህንም ምዕራፎች በአራት ከፍለን መመለከት እንችላለን።

1. መግቢያ 1፡1/4
2. እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳናቸው የጻፈላቸው ትምህርት 1፡5 3፡21
3. ስለ ክርስትያናዊ ምግባር የጻፈላቸው ትምህርት 4፡4 6፡20
4. ማጠቃለያ 619/24

6. የፊልጵስዮስ መልእክት

ቅዱስ ጳውሎስ የፊሊጵስዩስን መልእክት የጻፈው እስር ቤት በነበረበት ወቅት ሲሆን 1፡7 13፡14 ጊዜውን ከእስር ሊፈታ በቀረበበት ወቅት ነበር። 2፡19 23፡24

የፊሊጵሲዮስ መልእክት የተጻፈበት ምክንያት

1. በመከራ ውስጥ ላሉ በመጽናናታቸው የተሰማውን ደስታ እየገለጠ እነርሱምደስ እንዲላቸው መምከርና ከሐሰተኞች ወንድሞች እንዲጠበቁ ለማሳሰብ። 1፡18 2፡17 3፡2
2. በመካከላቸው በትህትና አለመኖርንና በሐሳብ አለመስማማትን እንዲያስወግዱ ለመምከር 2፤2 4፤2
3. ቅዱስ ጳውሎስ ታሞ ስለነበር በዚህ ተጨንቀው ለነበሩ ከሕመሙ መዳኑን አይተው እንዲጽናኑ ለማድረግ ስለላኩለትም ስጦታ ምስጋና ለማቅረብ።

የመልእክቱ አከፋፈል

የፊሊጵስዩስ መልእክት አራት ምዕራፎች ሲኖሩት ይህንንም በስድስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፡1-11
2. በእስራት ላይ ሆኖ ስለነበረ ደስታ እና መታመን ለማሳወቅ 1፡12-30
3. በመልካም ኑሮ እየኖሩ ደስታውን እንዲፈጽሙለት የጻፈው ትምህርት 21-18
4. ስነ-ምግባርንና የላኩለትን ስጦታ በተመለከተ የጻፈው ቃል 4፡1-20
5. መደያምደሚያ 4፤21-23

7. ቆላስይስ መልእክት

የቆላስያስ መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ እስራቱ ወቅት በሮም እስር ቤት ሆኖ ከጻፋቸው መልእክቶቹ መካከል አንዱ ነው።4፡3-11

የተለከውን ከኤፌሶንና ከፍልሞና መልእክት ጋር በቲቶ እጅ ነው። 4፡7 መልእክቱ በአጠቃላይ የሐሰት አስተማሪዎች ለሚያስተምሩት ትምህርት በጥንቃቄ የተሰጠ መልስ ነው።

የቆላስያስ መልእክት የተጻፈት ምክንያት

1. በመካከላቸው በፍልስፍና የተመሰረተ የሐሰት ትምህርት ግሮስቲሲዝም ገብቶ ስለነበር በዚያ ተማርከው እንዳይሳሳቱ ለማሳሰብ። 2፡8

2. በመንፈስ ስለሚሆን ስለፍቅራቸው ሊያመሰግናቸው ሊያበረታታቸው ስለወደደ። 1፥3-7

የመልእክቱ አከፋፈል

የቆላስያስ መልእክት አራት ምእራፎች ሲኖሩት እነርሱንም በአምስት ክፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-8
2. በክርስቶስ ሰው መሆን የተሰወረው የእግዚአብሔር ምስጢር ስለመገለጡ የጻፈው ትምህርት። 1፥9 2፥7
3. ሐሰተኞች በፍልስፍና እንዳይማርኳቸው የጻፈው ማሳሰቢያ 2፥8-23
4. ስለ ስነ-ምግባር የጻፈላቸው ትምህርት 3፥1 4፥6
5. ማጠቃለያ 4፥1-18

8. የመጀመሪያይቱ የተሰሎንቄ መልእክት

የመጀመሪይቱ የተሰሎንቄ መልእክት የተፃፈው ጢሞቴዎስ ስለ ተሰሰሎንቄ ክርስትያኖች ሁኔታ ለቅዱስ ጳውሎስ ከነገረው በኋላ ሲሆን ይህም በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው ወቅት በ 51 ዓ.ም ገደማ ቆሮንጦስ ነው። መልእክቱን ወደ ተሰሎንቄ የወሰዱት ጢሞቴዎስና ሰልዋኖስ ናቸው።

የመጀመሪያው የተሰሎንቄ መልእክት የተፃፈው ስለ ሁለት ነገር ነው።

ሀ. በእምነታቸውና በፍቅራቸው በመጽናታቸው የተሰማውን ደስታ መጽናናት ለመግለጥ። 1፥2 3፥13-16 31፥1-10

ለ. የጌታ ምጽአት ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ በድንገት መሆኑን በማስተማር ከጨለማ ስራ ተነጥለው ነቅተው እንዲጠብቁ ለማሳሰብ። 3፥ 11-13 5፥1-8

የመልእክቱ አከፋፈል

የመጀመሪያው ተሰሎንቄ መልእክት አምስት ክፍሎች ሲኖሩት እነዚህንም በአምስት ክፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-4
2. ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስትያኖች የነበረው ፍቅርን ለማሳወቅ 1፥5 3፥13
3. ስለ ክርስትያናዊ ስነ ምግባር የጻፈላቸው ትምህርት 4፥1-12
4. ስለ ዳግም ምጽአት የጻፈላቸው ትምህርት 4፥13 5፥11
5. ማጠቃለያ 5፥12-24

9. ሁለተኛይቱ የተሰሎንቄ መልእክት

ሁለተኛይቱ የተሰሎንቄ መልእክት የተጻፈው በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው ወቅት የመጀመሪያው መልእክት ከተጻፈበት ከጥቂት ጊዜ በኋላ በ 51 ዓ.ም ገዳም በቆሮንጦስ ነው። አጠቃላይ ይዘቱም ከመጀመሪያው መልእክት ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ሁለተኛው የተሰሰሎንቄ መልእክት የተጻፈው ስለ ሁለት ነገር ነው።

1. በመጀመሪያው መልእክቱ ስለ ዳግም ምጽአት ያልገለጠላቸውውን ነገር ሊገልጥላቸው 2፥2
2. በተሰሎንቄ ክርስትያኖች መካከል ስራ የማይሰሩ ነገር ግን በሰው ነገር እየገቡ ያለ ስርአት የሚሄዱ አንዳንድ ሰዎች ስለነበሩ። 3፥ 11 እነርሱም ለመምከርና ከማይታዘዙትም እንዲለዩ ለመሳሰብ 3፥12።

ሁለተኛው የተሰሎንቄ መልእክት ሶስት ምእራፎች ሲኖሩት እነዚህንም በአራት ክፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-4
2. ስለ ዳግም ምጽአት የጻፈው ትምህርት 1፤5 2፥12
3. ያስተማራቸውን ወገን ሥርዓት እንዲጠብቁ የጻፈላቸው ትእዛዝ 2፥13 3፥14
4. ማጠቃለያ 3፥16-18

10. የመጀመሪያይቱ የጢሞቲዎስ መልእክት

ውድ ተማሪዎች የሐዲስ ኪዳን የመልዕክት መጽሐፍት ከተጻፉላቸው አካላት ምክንያት ለማኅበረሰብ እና ለግለሰብ ተብለው ይከፈላሉ። የመጀመሪያቱ የጢሞትዎስ መልዕክት ለግለሰብ ከተጻፉ የመልክዕት ክፍሎ ጋር ይመደባል።

የመጀመሪያይቱ የጢሞቲዎስ መልእክት የተጻፈው በ 66 ዓ.ም ገደማ በሎዶቅያ ሲሆን መልእክቱ የተጻፈው ስለ ሶስት ነገር ነው።

1. ጳውሎስ ወደ እርሱ ሊመጣ አስቦ ስለዘገየ የቤተክርስትያንን አስተዳደር እንዲያውቅ ለማድረግ። 3፥4-5
2. በኤፌሶን ገብተው ከነበሩት የሐሰት መምህራን ምእመናንን እንዲጠበቁ ሊያሳስበው። 1፥18-20 4፥1-6
3. ጢሞቲዎስ ወጣት በመሆኑ ማንም እንዳይንቀው ለራሱና ለትምህርቱ እንዲጠነቀቅ ሊመክረው። 4፥16 20፥20

የመልእክቱ አከፋፈል

የመጀመሪያይቱ የጢሞቲዎስ መልእክት ስድስት ምዕራፎች ሲኖሩት እነሱም በሶስት ክፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-2
2. ስለ ቤተክርስትያን አስተዳደር የጻፈለት። 1፥3 6፥19
3. ማጠቃለያ 6፤20-21

11. ሁለተኛይቱ የጢሞቲዎስ መልእክት

ሁለተኛይቱ የጢሞቲዎስ መልእክት የተጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ በእስር ቤት በነበረበት ወቅት ሲሆን ጊዜውም በሰማዕትነት ከማለፍ ጥቂት ቀደም ብሎ በ 68 ዓ.ም ገደማ ነው።

ሁለተኛ የጢሞቲዎስ መልእክት የተጻፈው ስለ ሁለት ነገር ነው።

1. በጊዜው እንደ ጳውሎስ ሁሉ ጢሞቲዎስም በመከራ ውስጥ ስለነበረ በተረዳው ነገር እንዲጽናና መከራን የተቀበለ የወንጌል አገልግሎት እንዲፈጸም ለመምከር 1፥8 3፥10
2. ጳውሎስ ጢሞቲዎስን ለማየት ስለናፈቀ በቶሎ እንዲመጣለት ለማሳሰብ። 1፥4፥4፥9-11

የመልእክቱ አከፋፈል

ሁለተኛው የጢሞቲዎስ መልእክት አራት ምእራፊች ሲኖሩት እነዚህም በአራት ክፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ፥ 1፥1-7
2. ከጢሞቲዎስ የተጻፈለት የአገልግሎት ትምህርት 1፥8 4፥5
3. ከመሞቱ በፊት እንዲመጣለት የጻፈው 4፥6 4፥18
4. ማጠቃለያ 4፥19-22

12. የቲቶ መልእክት

የቲቶ መልእክት የተፃፈው ስለ ሦስት ነገር ነው

1. በየከተማው ቀሳውስትንና ኤጲስ ቆጶሳትን የሚሾምበት መመዘኛዎች ሊያሳውቀው። 1፥5-9
2. ሕዝቡን የሚጠራበት ስርአት ሊጽፍለት ስለፈለገ 1፥10-14 2፥1-10 2፥15 3፥8-11
3. ወደ እርሱ እንዲመጣ ሊጠራው ስለፈለገ። 3፥12

የመልእክቱ አከፋፈል

የቲቶ መልእክት ሦስት ምእራፎች ያሉት ሲሆን እነዚህም በአራት ክፍሎች መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-4
2. የቤተ ክርስትያን አስተዳደር የሚመለከት ትምህርት 1፥5 2፥10
3. ስለ መዳን የጻፈው ትምህርት 2፥11 3፥11
4. ማጠቃለያ 3፥12-15

13. *የፊሊሞና መልእክት*

የፊሊሞና መልእክት የተጻፈው በሮም እስር ቤት ሲሆን ጊዜውን በ 1 ኛው እስራቱ ወቅት በ 62 ዓ.ም ገዳመ ቆላስያስና የኤፌሶን መልእክት በተፃፈበት ጊዜ ነው። በአጠቃላይ ትምህርቱ ስነ ምግባር ይዘት አለው።

የፊሊሞና መልእክት የተፃፈው ስለ ሁለት ነገር ነው። እነርሱም፥-

1. አናሲመስን ‹የፊሊሞና አገልጋይ የነበረውን› ከጌታው ጋር ለማስታረቅ ቁ 11-12
2. ወደ እነርሱ የመሄድ ተስፋ ስለነበረው ማረፊያ እንዲዘጋጅለት ለማሳሰብ ቁ›22

የመልእክቱ አከፋፈል

1. መግቢያ ቁ. 1-7
2. ስለ አናሲመስ ጳውሎስ ለፍሊሞና ያቀረበው ልመና። ቁ. 8-17
3. ማጠቃለያ ቁ. 23-25

14. *የዕብራውያን መልእክት*

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው በኢጣሊያ ውስጥ ሲሆን ጊዜውም ከእስረት ከተፈታ በኋላ ከኢጣልያ ሳይወጣ ነው። ይህም በ 64 ዓ.ም ገደማ ነው

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው ምክንያት ስንመለከት እብራውያን ክርስትያኖች ወደ ኦሪት እየተመለሱ ስለነበር ብሉይንና ሐዲስን በማነፃጸር ለማስተማር። 3፥12-15 6፥1-12 10፥19-39 12፥12-13

የመልእክቱ በከፋፈል

የዕብራውያን መልእክት 13 ምዕራፍ ያለው ሲሆን እነዚህንም በስድስት ክፍሎች መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-3
2. ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ባሕሪ ልጅ ስለሆነ ከመላእክት እና ከነብያት እንደሚበልጥ ለማስተማር። 1፥4 4፥16
3. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት የጻፈው ትምህርት 5፥1-1
4. ስለ እምነት የጻፈው ትምህርት 11፥1-2
5. ክርስትያናዊ ምግባር እንዲኖራቸው የጻፈው ትምህርት 13፥1-17
6. ማጠቃለያ 13፥18-25

ውድ ተማሪዎች ቅዱስ ጳውሎስ የጻፋቸው *14* መልዕክታት ከላይ ለመመልከት ሞክረናል። ከዚህ በታች ድግሞ የተቀሩትን የመልዕክታት እንመለከታለን።

5.5.3 የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

ቅዱስ ጴጥሮስ ከ 12 ሐዋርያት አንዱ ሲሆን በመጀመሪያ ስሙ ስምዖን ይባል ነበር። በኋላ ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኬፋ ብሎ ሰየመው። በአርማይክ ኬፋ በግሪክ ጴጥሮስ ማለትሲሆን ትርጉሙ ዐለት ማለት ነው። ማር፣ 3-16 ዮሐ.1-43 የትውልድ ቦታው ቤተሳይዳ ነበር ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ አይሁድ ሊቃውንት ብዙ ትምህርት አልተማረም። ማር.14፥10 ዮሐ.1-45 የሐዋ.ሥራ 4፥13 ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር አሳ እያጠመደ በቅፍርናሆም ይኖር ነበር።ሚስትም ነበረችው ማር 1-29 በመጀመሪያ ከጌታችን ጋር ያስተዋወቀው እንድርያስ ነው። ዮሐ. 1-14 በኋላም ኢየሱስ ሰዎችንእንዲያጠምድ ጠራው። ማር 1-16 ሉቃ 5-1

1. የመጀመሪያይቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

1ኛ ጴጥሮስ የተጻፈው በባቢሎን ሲሆን 5-13 በ 67 ዓ.ም ገደማ እንደተፃፈ ይገመታል። መልእክቱ በአጠቃላይ በሃይማኖትና በስነ-ምግባር ትምህርትን የያዘ ነው።

መልእክቱን የፃፈው ስለ ሁለት ነገር ሲሆን

1. በወቅቱ የመልእክቱ ተቀባዮቹ በልዩ ልዩ ፈተና አዝነው ስለነበር ለጊዜው መከራን ቢቀበሉም ታላቅ ክብርና ጸጋ እንደሚያገኙ በመንገድ ሊያጽናናቸው። 2፥20 ፥12-14 5፥10-12
2. በአሕዛብ መካከል ሲመላለስ ከቀድሞ ሥራቸው ተለይተው ኑሮአቸው መልካም እንዲሆን ሲመክራቸው። 2፥12 1፥15-15 4፥3-6

የመልእክቱ አከፋፈል

1ኛው የቅዱስ የጴጥሮስ መልእክት አምስት ምዕራፍ ያለው ሲሆን እነዚህንም በአምስት ክፍሎ መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1-2
2. ስለ መዳን የጻፈላቸው ትምህርት 1፥3-25
3. በአሕዛብ መካከል ሲኖር ሊያሳዩት ስለሚገባ መልካም ኑሮ። 2፥1 3፥22
4. በሚቀበሉት መከራ ክብር እንዲያገኙ 4፤1 5፥11
5. ማጠቃለያ 5፥12-14

2. ሁለተኛይቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

ሁለተኛይቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት የተፃፈው በ 68 ዓ.ም ገደማ ቅዱስ ጴጥሮስ ከመሞቱ ቀደም ብሎ በሮም እያለ ነው። መልእክቱ የተፃላቸው ሰዎች የመጀመሪያው መልእክት የተፃፈላቸው ሰዎች ሲሆኑ በዚህኛው መልእክት ግን በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ያገኘው ተብለው ተገልጸዋል። 1፥1

1. በክርስትና ህይወታቸው የፀኑ ቢሆኑም ከፊት ይልቅ እንዲተጉ ለማሳሰብ ስለፈለገ። 1፥10-15 3፥1-2
2. የኑፋቄን ትምህርት አሾልከው ከሚያስገቡ ሀሰተኞች መምህራን እንዲጠበቁ ለማስጠንቀቅ 2፤1 3፥3

የመልእክቱ አከፋፈል

ሁለተኛው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ሦስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በአምስት ክፍሎች መመልከት ይቻላል።

1. መግቢያ 1፥1-3
2. የተሰበከላቸው ትምህርት እውነተኛ እንደሆነ ስለማስገንዘብ 1፥4-21
3. በመካከላቸው የነበሩት የሐሰት መምህራን ማንነት ማሳወቅ 2፥1 2፥22
4. ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የጻፈው ትምህርት 3፥1-16

5. ማጠቃለያ 3፥17-18

5.5.4 የቅዱስ ዮሐንስ መልዕክታት

ቅዱስ ዮሐንስ አባቱ ዘብድዮስ ሲባል እናቱ ማርያም ባውፍልያ ትባላለች። ቅዱስ ዮሐንስ የሐዋርያ የቅዱስ ያዕቆብ ወንድም ነው። ስለ ቅዱስ ዮሐንስ የስሞቹ ትርጉም በወንጌል ክፍል የዮሐንስ ወንጌል በተመለከትንበት ክፍል የተጠቀሰ በመሆኑ በዚህ ክፍል ስለሣፋቸው መልእክታት እንመለከታለን።

1. የመጀመሪያይቱ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

1ኛ የዮሐንስ መልእክት ቅዱስ ዮሐንስ በኤፌሶን በሚኖርበት ወቅት በ 90 ዓ.ም ገደማ እንደ ጻፈው ። የጻፈውም እስያ በሚባለው ሀገር ነው። መልእክቱም በአጠቃላይ የሃይማኖትና የምግባር ትምህርት ይዟል።

1ኛ የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው ስለ ሁሉም ነገር ነው። በእስያ አውራጃ ለነበሩት ክርስትያኖች የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው እንዲያውቁ 5፥13 ለማስተማር እና በዚያን ዘመን ከተነሱ የሐሰት መምህራን እንዲጠበቁ ለማሳሰብ ይቻለል።

1. መግቢያ 1፥1-4
2. ከኃጢአትና ከዓለም ምኞት ተለይተው በብርሃን እንዲኖሩ የጻፈው ትምህርት 2፥18 3፥24
3. የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ከሆኑት ሀሰተኞች እንዲጠበቁ የጻፈው ትምህርት 2፥18 3፥24
4. ስለ ፍቅር የፃፈው ትምህርት 4፥7-21
5. በእግዚአብሔር ልጅ ስለማመን የፃፈው ትምህርት 5፥21

2. ሁለተኛይቱ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

2ኛ የዮሐንስ መልእክት እንደመጀመሪያው መልእክት ሁሉ በሐዋርያው ዮሐንስ የተፃፈ ሲሆን በኤፌሶን ከተማ በ 90 ዓ.ም ገደማ እንደጻፈው ይገመታል። ቅዱስ ዮሐንስ ይህንን መልእክቱን የላከው ወደ አንዲት የተመረጠች እመቤትና ወደ ልጆቿ ነው። ቁ.2

2ኛ ዮሐንስ መልእክት የተፃፈበት ምክንያት በመጀመሪያይቱ መልእክት ላይ ከተጠቀሱት መናፍቃንና ትምህርታቸው እንንዲጠበቁ ለማስጠንቀቅ ነው። ቁ.1-1

2ኛ ዮሐንስ መልእክት 1 ምእራፍ 13 ቁጥር ያለው ሲሆን በአራት እንመለከታል።

1. መግቢያ ቁ. 1-2
2. እርስ በእራሳቸው እንዲዋደዱ የፃፈላቸው ትምህርት ቁ. 4-6
3. ከክርስቶስ ተቃዎሚዎች እንዲጠበቁ የፃፈላቸው ቁ.7-11
4. ማጠቃለያ ቁ. 11-12

3. ሦስተኛይቱ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

3ኛ የዮሐንስ መልእክት ጸሐፊና የተፃፈበት ዘመን የተላከበት ከተማ እንደ ሁለቱ መልእክት ነው። መልእክቱን ዮሐንስ ጋይድስ ወደ ተባለው አማኝ ሰው የተፃፈ ሲሆን እንግዶችን ስለሚቀበል ያመሰግነውና ቁ.8 በጎ የሆነውን እንጂ ክፉ የሆነውን እንዳይመስል ለማሳሰብ ጽፎለታል። ቁ.10

መልእክቱ 1 ምዕራፍ 15 ቁጥር ያለው ሲሆን ይህንንም በአራት ከፍሎ መመልከተት ይቻላል።

1. መግቢያ ቁ. 1-3
2. ስለ ጋይዮስ እንግዳ ተቀባይነት 5-8
3. የዲዮጥራጥስ መወቀስና የዲሜጥሮስ መመስገን 9-12
4. ማጠቃለያ 13-15

5.5.5 የያዕቆብ መልእክት

ይህ መልእክት የጌታ ወንድሞች ከተባለት በአንዱ በያዕቆብ የተፃፈ ነው። ያዕቆብ ይህ መልእክት የፃፈው ተበትነው ለነበሩት አሁን ግን ክርስትና የተቀበሉት አይሁድ ነው። ያዕቆብ በ62 ዓ.ም በኢየሩሳሌም በሰማዕትነት እንደሞተ ይነገራል። መልእክቱ በ50 ዓ.ም ገደማ ሳይጻፍ እንዳልቀረ ይታመናል።

መልእክቱ የተፃፈው ስለ ሦስት ነገር ነው

1. በየሀገሩ ተበትነው የነበሩ አይሁድ ብዙ መከራ ደርሶባቸው ስለነበር በትግል እንዲቀበሉት ለመምከር። 2፥2-4 5፥7-12
2. እምነትን ከመልካም ስራ ለይተው የያዙ ሰዎች ስለነበሩ እምነት ያለ ስራ ከንቱ እንደሆነ ለማስተማር። 1፥22 5፥19-22

የመልእክቱ አከፋፈል

የሐዋርያው የቅዱስ ይሁዳ መልእክት 5 ምዕራፍ ያለው ሲሆን ለማጥናት እንዲረዳን በስድስት ከፍለን እንመለከታለን፥-

1. መገቢያ 1፥1
2. በእምነት ምክንያት የሚደርሰውን ፈተና ጸንቶ መታገስ እንደሚገባ 1፥2-21
3. ስለ ምግባር የጻፈው ትምህርት እና ምክር 1፥22 2፥26
4. ከተለያዩ ስህተቶች እንዲታረሙ የፃፈው ትምህርት 3፥1-4
5. በመከራ ጊዜ ትእግስትና ጸሎት እንደሚያስፈልግ 51-20
6. ማጠቃለያ 5፥19-20

5.5.6 የይሁዳ መልእክት

እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ሁሉ ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳም የጌታ ወንድሞች ከተባሉት አንዱ ነው። ማቴ፥ 13-5 የመልእክቱ የተላከላቸው ህዝቦች ይኖሩበት የነበረው ስፍራ ባይታወቅም መልእክቱን ግን ለምእመናን የተላከ ነበር። ቁ. 1 ጴጥሮስ በ2ኛው መልእክቱ እንዳደረገው ሁሉ ይሁዳም ሐሰትን የሚያስተምሩ ሰዎች አንባቢዎቹን ለማስጠንቀቅ ጽፏል። መልእክቱ በ65 ዓ.ም ገደማ ሳይፃፍ እንዳልቀረ ይገመታል።

መልእክቱ 1 ምዕራፍ 25 ቁጥር አለው።

5.6 የራእይ መጽሐፍ ክፍል

ውድ ተማሪዎች የሐዲስ ኪዳን የቅኖና መጽሐፍት አከፋፈል መሰረት በአምስተኛ ደረጃ ላይ የምናገኘው የራእይ ወይም የትንቢት ክፍል ነው። ከ 35 ቱ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት በይዘቱ የራእይ ወይም የትንቢት መጽሐፍ የሆነው የዮሐንስ ራእይ በዚህ የቀኖና መጽሐፍት ክፍል ውስጥ የሚካተት ብቸኛው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ነው።

1. የዮሐንስ ራእይ

ወንጌላዊው ዮሐንስ ከዚህ ቀደም በነበሩት ክፍሎች የጻፋቸውን የአንድ የወንጌልና ሶስት የመልዕክታት መጽሐፍት ተመልክተናል። የቅዱስ ዮሐንስ ራዕይ በግእዝ ራእየ ለዮሐንስ አቡቀለምሲስ፣ በአማርኛ የዮሐንስ ራዕይ፣ በግሪክ አፖካሊፕሲስ፣ በእንግዚኛው ረቨሌሽን የሚባል ሲሆን ትርጉሙም መግለጥ፣ የተሸሸገውን ማሳወቅ ማለት ነው። የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ በግሪክ 9830 ቃላት የያዘ ሲሆን በውስጡ የያዛቸው ወደ 300 የሚጠጉ ተምሳሌቶችና እንዳንዳቸው በውስጣቸው የያዙት ትርጓሜ፣ መጽሐፉን ከሌሎች የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ልዮ ያደርገዋል። ቅዱስ ዮሐንስ ንጉስ ድምጥያኖስ ላሰራው የጣኦት ምስል አልሰግድም በማለቱ በወቅቱ በመንግስት ላይ ያመጹ ሰዎች ወደሚታሰሩበት ወደ ፍጥሞ ደሴት በግዞት ተወስዷል።

የፍጥሞ ደሴት፡- በመጽሐፈ ዮሐንስ እንደገለጠው/ 1፣9/ ራእዩን ያየውም የጻፈውም በፍጥሞ ደሴት ነው። የፍጥሞ ደሴት በኤጅያን ባሕር የምትገኝ ድንጋያማ ደሰት ናት። ከታናሿ እስያ /ቱርክ/ በስተ ምዕራብ ጠረፍ 40 ማይልስ፣ ከኤፌሶን ከተማ በስተ ደቡብ 50 ማይልስ ርቀት ላይ የምትገኝ ስትሆን በአሁኑ ጊዜ መጠሪያዋ ፓትሞስ ተብላ የምትጠራ ከ 3000 ሺ በላይ ሰዎች የሚኖሩባት ደሴት ናት። / ራዕይ ዮሐንስ ዳንኤል ክብረት/

ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በታሰረበት ወቅት እንደወንድሞቹ ሐዋርያት ዓለምን ዞሮ ወንጌል ባለማስተማሩ ያዘን ይተክዝ ነበር። እግዚአብሔር አምላክም ታላቅ ምስጢር ገልጦለት እንደ አባቶቻችን አጠራር ዘመን ይፍታው የተባለ የራእይ መጽሐፍ ለመጻፈ በቅቷል።

የመጽሐፉ ይዘት

- የመጽሐፉ ይዘት ስንመለከት ሁል ጊዜ ቢሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃትን ቤ/ክእንደማይለይ የሚያትት መጽሐፍ ነው።
- በኦሪት ዘፍጥረት የተገለጠ የሰው ልጅ ውደቀት በጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ቤዛነት የተሰጠን/ የተዘጋጀ/ ክብር በዮሐንስ ራእይ እንመለከታለን /የተከፈተ በር፣ መንግስተ ሰማያት/።
- በኦሪት ዘፍጥረት ወደዚህ ዓለም የመጣው የሰው ልጅ በራእይ ዮሐንስ የምድር ኑሮ ፍጻሜውን እናያለን።
- ራእይ ዮሐንስ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ልዮ፣ ፍጹምና ተመን የማይገኝለት ፍቅር የገለጠበት መጽሐፍ ነው።
- በአጠቃላይ የዮሐንስ ራእይ የድል፣ የሰማያዊ ምስጋናና ቅዳሴ፣ በተስፋ የተሞላ እና መንግስተ ሰማያትን የሚሳይ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ የተጻፈበት ዘመን

አብዛኞቹ ሊቃወንት ዮሐንስ በደሴተ ፍጥሞ የሚመለከተውን ራእይ ለደቀመዝሙሩ አብሮኮሮስ እየነገረው በ 95/96 ዓ.ም እንደተጻፈ ይታመናል።

የመጽሐፉ አከፋፈል

ራእይ ዮሐንስ 22 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ይከፈላል።

ከምዕራፍ 1-3 ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ስለተጻፈው መልእክታት
ከምዕራፍ 4-5 በሰማያት ስለሚሆኑ ነገሮች የመጀመሪያ ገለጻ
ከምዕራፍ 6-11 ስለ ሰባቱ ማኅተሞችና ሰባቱ መልእክቶች
ከምዕራፍ 12-13 ስለ ዘንዶው ስለ አውሬውና ስለ ሐሰተኛ ነቢያት
ከምዕራፍ 14-16 በሰማያት ስለሚሆኑ ነገሮች የሁለተኛ ገለጻ፣ ስለ ሰባቱ ጽዋዎች
ከምዕራፍ 17-19 ስለ ባቢሎን መፍረስ
ከምዕራፍ 20-22 ስለ እግዚአብሔር መንግስት ይተርካል።

መልመጃ አምስት

1. የወንጌል መጽሐፍት ከይዘታቸው አንጻር ---------- እና ---------- በመባል ይከፈላሉ።
2. የሥርዓት መጽሐፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ ውስጥ ያለተካተቱበት ምክንያት ምንድ ነው
3. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያደረጋቸው ጉዞዎች ---------- ናቸው።

<u>ዋቢ መጽሐፍት</u>

1. መጽሐፍ ቅዱስብርሃን ና ስላም ማተሚያ ቤት *1980* ዓ.ም አዲስ አበባ
2. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት - 1መ/ር ቸሬ አበበ እና ዲ/ን ቴዎድሮስ በየነ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የሰ/ት/ቤቶች ማድራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን አዲስ አበባ *1996* ዓ.ም
3. መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ መ/ር ቸርነት አበበ አዲስ አበባ 2003 ዓ.ም
4. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የርቀት መማርያ መጽሐፍ የጊቢ ገብርኤል አምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት አዲስ አበባ
5. **Introducation of Bilbe study***Fissehatsion Demoz /M.Th/ Addis Abeba*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወወላዲቱ ለድንግል ለመስቀሉ ክቡረ አሜን***!!!***